السلي

የሐጅ አድራጊ ስንቅ



ዝግጅት: ኡስታዝ ጀማል ሙሐመድ
አርታዒ: ዳዒ አብዱልመናን መንዛ


حساب التبرعات بمصرف الراجحي: SA2280000296608010070509
حساب التبرعات بمصرف الإنماء: SA9605000068200517913002

كتب الجاليات
209
11

مكتب الدعوة بالسلي
هاتف | ٠١١٢٤١٤٤٨ تحويلة | ٥٥٥ - فاكس | ٠١١٢٤١١٧٣٣ تحويلة | ٢٣٢

السلي

زاد الحاج



إعداد
قسم الجاليات بالمكتب

1201817

أمهري
Sulay1417@gmail.com
www.islamnewlife.com

زَادُ الْحَاجّ

የሐጅ አድራጊ ስንቅ

جمع وإعداد: جمال محمد

ዝግጅት: ኡስታዝ ጀማል ሙሐመድ

አርታዒ: ዳዒ አብዱልመናን መንዛ

ማውጫ

ርዕስ **ገፅ**

መቅድም.....5
የሐጅ ህግ (ብይን).....7
የሐጅ ትሩፋት.....7
የሐጅ መስፈርቶች (ደንቦች).....9
ስለ ሐጅ ስራ አፈፃፀም ስርዓቶችና ስለኢህራም ክልሎች....19
በኢህራም ወቅት የሚከለከሉ ነገሮች.....32
የዑምራ አፈፃፀም ስርዓት.....40
የዑምራ አፈፃፀም ስርዓቱ ጠቅለል ባለ መልኩ.....51
የሐጅ ሥርዓተ-አምልኮ አፈፃፀም.....52
የሐጅ አፈፃፀም ጠቅለል ባለ መልኩ.....69
የሐጅ ማዕዘናትና ግዴታዎች.....74
አንዳንድ ሑጃጆች የሚፈፅሟቸዉ ስህተቶች.....77
ሐጅ ላይ ያለ ሰው በምን አይነት ሥራ ይጠመድ?.....83
የሐጅ ስርዐተ ምስጢራት በጥቂቱ.....85
የነቢዩን ﷺ መስጊድ ጉብኝት የሚመለከት ድንጋጌ.....87
ዝያራንና ኣዳቡን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች.....89

በዚያራ ውስጥ የሚከሰቱ ስህተቶችና ማሳሰቢያዎች.....92
ለጎብኚዎች የሚፈቀዱ ሱናዎች.....93
አሥሩ የዚልሂጃ ቀናት- ከዱኒያ ቀናቶች ሁሉ በላጮች.....94
ኢስላም፣ ኢማንና ኢህሳን.....112
የእስልምና መሠረቶችና ታላላቅ ምሰሶዎች.....120
የኢማን ትርጉምና አስፈላጊነት፡ምሰሶዎች..... 126
የኢህሳን ትርጉም.....135
የላኢላህ ኢለላህ ትርጉም እና መስፈርቶች..... 136
ሶላት በእስልምና ውስጥ ያለው ደረጃ.....142
የሶላት ትሩፋት..... 143
ሶላትን የሚመለከት ድንጋጌ.....144
የሶላት ማእዘናት ግዴታዎችና ሱንናዎች.....146
በሶላት ውስጥ የተፈቀዱ የተጠሉና ሶላትን የሚያበላሹ ነገሮች
.....151
ሶላትን የተወ ሰው የሚመለከት ድንጋጌ.....155
የትንሽ ልጅ ሶላት.....156

بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ

መቅድም

ለ ውድ ሀጅ አድራጊ ወንድሜ /እህቴ

እንኳን አላህ ለዚህ አበቃህ!

ውድ ወንድሜ ሀጅ ከአምስቱ የኢስላም መሠረቶች አንዱ እና ከታላላቅ መገለጫዎቹ ነው፡፡ ታዲያ ይህን ታላቅ ኢባዳ አላህ እንዲቀበልህ ሀጅህ በእውቀት የታገዘ መሆን አለበት፡፡ እነሆ ይህች ((የሀጅ አድራጊ ስንቅ)) ተብላ የተሰየመች መጽሀፍ እንደስሟ ሀጅ አድራጊው የሀጅ አፈጻጸም ሥርዐት እንዴት እንደሆነ የታላቁን ነብይ ሙሐመድ ﷺ መስጅድ እንዴት እንደሚዘይር እንዲሁም አንድ ሙስሊም ስለ እምነቱ ማወቅ የሚያስፈልገውን ነገር በውስጧ አካትታለች ::

እናንተም ሀጃችሁን በተሳካ መልኩ ፈጽማችሁ ከአላህ ሱ.ወ ትልቅ ምንዳ አግኝታችሁ በሰላም ወደ ቤተሰቦቻችሁ ትመለሱ ዘንድ አላህን እለምነዋለሁ፡፡

ለአላህ ጥሪ አቤት ብለህ

ሚስትና ልጅ ንብረት ጥለህ

መጥተሀል የጌታህን እዝነት ከጅለህ

ታዲያ በከንቱ የምትመለስ መሰለህ?

የአላህ መልዕክተኛ በርግጥ አበሰረህ

አልሀጁል መብሩሩ ለይሰ ለሁ ጀዛኡን ኢልለ ጀናህ

ሀጅህን አላህ በሚወደው መንገድ ከፈጸምህ

ምንዳህ ጀነት መሆኑን አበሰረህ

አላህ ይወፍቀን!

ጀማል ሙሐመድ
ሱለይ የዳዕዋ ቢሮ: ሪያድ : ሳዑዲ አረቢያ
ጀማደል ኣኺር 1438(March 2017)
+966551053797
Email:abumoh15@gmail.com

የሐጅ ህግ(ብይን)

ሐጅን በሕይወት አንድ ጊዜ መፈፀም(ማድረግ) ለአካለ መጠን በደረሰና ችሎታ ባለዉ ሁሉ ግዴታ ነዉ ። ከኢስላም ማዕዘናት አንዱ ሲሆን ግደታነቱ በቁርዓን፣ በሀዲስና በዐሊሞች ስምምነት(ኢጅማዕ) የተረጋገጠ ነዉ ።



የሐጅ ትሩፋት

1. ሐጅ ያለፉ ወንጀሎችን ይሰርዛል።

አቡ-ሁረይራ አላህ ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዳስተላለፉት ረሱል ﷺ እንዲህ ብለዋል ፡-ሐጅ ያደረገ ከሚስቱ ጋርም ያልተገናኘና (ሌሎች ከሴቶች የሚከጀሉ ስሜታዊ ጉዳዮችን ያልፈፀመ) እንዲሁም ወንጀል ያልሠራ እናቱ እንደወለደችዉ ዕለት ሆኖ (ከኃጢአት ፀድቶ) ይመለሳል። (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት)

2. ሐጅ ከእሳት ነፃ ለመሆን ሰበብ ነዉ።

አሚሻ ስራዋን አላህ ይውደድላትና እንዳወሳችዉ ረሱል ﷺ እንዲህ ብለዋል ፡-አላህ ባሪያዉን ከእሳት ነፃ የሚያወጣበትና የቀረበ ሆኖ መላይኮችን (ሙባሃ የሚያደርግበት) እንደ አረፋ ቀን የለም ፡፡ (ሙስሊም የዘገቡት)

(ሙባሃ) ማለት አላህ ለመላኢኮች የሁጃጆችን በላጭነት የሚገልፅበት ሁኔታ ነው።

3. ሐጅ ዋጋዉ ጀነት ብቻ ነዉ፡፡

አቡ-ሁረይራ ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዳስተላለፉት ረሱል (ሶ.ዐ.ወ)እንዲህ ብለዋል፡- የዑምራ (ሥነ-ሥርዓት መፈፀም)ከአንድ ዑምራ እስከ ቀጣዩ ዑምራ በመካከላቸዉ የሚፈፀመዉን ወንጀል ያስፍቃል ተቀባይነት ያገኘ ሐጅ ዋጋዉ ጀነት ብቻ ነዉ፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት)

4. ሐጅ ትልቅ ትሩፋት ካላቸዉ ስራዎች አንዱ ነዉ፡፡

አቡ-ሁረይራ ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ)ከስራዎች ሁሉ ትልቅ ትሩፋት ያለዉ ስራ የትኛዉ ነዉ በማለት ተጠየቁ፡፡ በአላህና በመልዕክተኛዉ ማመን ነዉ ሲሉ መለሱ፡፡ በመቀጠልስ ምን ? በአላህ መንገድ ላይ መዋጋት አሉ:: በመቀጠልስ ምን ? ተቀባይነት ያገኘ ሐጅ ብለዉ መለሱ፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት)

የሐጅ መስፈርቶች(ደንቦች)

ማንኛዉም የኢስላም ህግ የመጣዉ ሚስጥሮችን ሁሉ ጠንቅቆ አዋቂና ጥበበኛ ከሆነዉ (ከአላህ) ዘንድ ነዉ፡፡ ስለዚህ ከጥበቡና ከፍትሁ ጋር የሚስማማን ፣ የሚዘመድን ህግ እንጅ አይደነግግም ለዚህም ነዉ ዋጅባትና ፈራኢዶች(ግዴታዎች) መሟላት ያለባቸዉ ደንቦች ካልተሟሉ በሰዎች ላይ ግዳጅ የማይሆኑት ግዳጅ የሆነዉ ነገር እቦታዉ ላይ ማረፍ ስላለበት፡፡ የሐጅን ግዴታ ብንመለከት በሰዎች ላይ ግዴታ የሚሆነዉ ደንቦች ሲሟሉ ብቻ ነዉ፡፡

1. የመጀመሪያዉ መስፈርት ሙስሊም መሆን ነዉ :: ከሃዲ ከመስለሙ በፊት ሐጅ ግዴታ አይሆንበትም :: መጀመሪያ ኢስላምን እንዲቀበል ይታዘዛል ከዚህ በኃላ ኢስላም ግደታ ያደረጋቸዉን በሙሉ መፈፀም እንዳለበት እናስረዳዋለን :: ምክኒያቱም ህጎች ያለ ኢስላም ተቀባይነት ስለሌላቸዉ፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿وَمَا مَنَعَهُمۡ أَن تُقۡبَلَ مِنۡهُمۡ نَفَقَٰتُهُمۡ إِلَّآ أَنَّهُمۡ كَفَرُواْ بِٱللَّهِ وَبِرَسُولِهِۦ وَلَا يَأۡتُونَ ٱلصَّلَوٰةَ إِلَّا وَهُمۡ كُسَالَىٰ وَلَا يُنفِقُونَ إِلَّا وَهُمۡ كَٰرِهُونَ﴾ التوبة ٥٤

(የለገሱት (ሃብት)ተቀባይነት እንዳይኖረዉ እንቅፋት የሆነዉ በአላህና በመልዕክተኛዉ በመካዳቸዉ፣ ሶላትን

እየተሰላቹ እንጅ የማይሰግዱ፣ እየጠሉ እንጅ የማይለግሱ በመሆናቸዉ ነዉ) (አት-ተዉበህ54)።

2. ሁለተኛዉ መስፈርት ጤናማ አዕምሮ ነዉ ። የአዕምሮ ችግር ያለበት ሰው የሐጅ ግዴታ የለበትም። ሐጅ ቢያደርግ ተቀባይነት የለዉም ምክኒያቱም ሐጅ ኒያ ያስፈልገዋል ኒያ ደግሞ የአዕምሮ ችግር ካለበት ሊገኝ አይችልም።
3. ሶስተኛዉ መስፈርት ለአካለ መጠን መድረስ
4. አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿وَإِذَا بَلَغَ ٱلۡأَطۡفَٰلُ مِنكُمُ ٱلۡحُلُمَ فَلۡيَسۡتَـٔۡذِنُواْ كَمَا ٱسۡتَـٔۡذَنَ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡۚ﴾ النور ٥٩

ሕጻናት ለአቅመ አዳም በደረሱ ጊዜ እነዚያ ከነርሱ በፊት የነበሩት (ታላላቆች) እንዳስፈቀዱት እነርሱም ያስፈቅዱ) (አን-ኑር59) ። ነቢዩም (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- (ጁሙዓ ቀን መታጠብ ላቅመ አዳም በደረሰ ሰዉ ሁሉ ላይ ግዴታ (ዋጅብ) ነዉ) ። (ቡኻሪና ሙስሊም)

2.**የብልት ፀጉር ማብቀል** ፡- ዐጢያ አልቁረዚ ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዲህ ብለዋል፡- የቁረይዚ ቀን ነቢዩ ዘንድ ቀረብን አካለ መጠን የደረሰ ወይም ብልቱ ላይ ፀጉር ያበቀለ ተገደለ ግን ከዚህ ሌላ የሆነ ይቅርታ ተደረገለት።

3. **አስራ አምስት ዓመት መሙላት፡-** አብደላ ኢብኑ ኡመር ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዳወሱት የዑሁድ ዕለት ነቢዩ ዘንድ እንዲቀርብ ታዘዝኩኝ የአስራ አራት ዓመት ልጅ ስለነበርኩ ከለከሉኝ ኸንደቅ ጦር ላይ ግን የአስራ አምስት አመት ወጣት ስለነበርኩ ፈቀዱልኝ ብሏል፡፡

4. ሴት ልጆች አካለ መጠን ለመድረስ ለወንዶች የተሰጡ ምልክቶችና ተጨማሪ አራተኛ ምልክት አለ እሱም **የወር አበባ ማየት** ነዉ የወር አበባ ባየች ጊዜ አስር ዓመት ባይሞላትም እንኳ ለአቅመ ሔዋን በእርግጥ ደርሳለች ፡፡ ስለዚህ አካለ መጠን ያልደረሰ ዕድሜዉ ዝቅተኛ ስለሆነና የሐጅ ግዴታዎችን መሸከም (መተግበር) ስለማይችል ሐጅ ግደታ አይሆንበትም፡፡ ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- (ብዕር ከሶስት ነገሮች ላይ ተነስቷል የተኛ ከእንቅልፉ እስከሚነሳ፣ ህፃን አካለ መጠን እስከሚደርስ እና ያበደ ከበሽታው እስከሚድን ድረስ)፡፡ ነገር ግን የህፃን ልጅ ሐጅ ተቀባይነት አለው፡፡ ኢብኑ አብባስ ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዳወሱት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) አንድ ጊዜ ረውሃዕ እሚባል አካባቢ ላይ ሰዎችን አገኙ እናንተ እነማን ናችሁ አሏቸዉ ? እነሱም እኛ ሙስሊሞች ነን አሉ፡፡ እነሱም ለመሆኑ አንተ ማነህ ብለዉ ጠየቁ ? እኔ የአላህ መልእክተኛ ነኝ በማለት መለሱ ከመካከላቸዉ አንዲት ሴት ህፃን ልጇን ከፍ አድርጋ በመያዝ ይህ ህፃን ሐጅ ቢያደርግ ሐጁ ተቀባይነት ይኖረዋልን በማለት ጠየቀች፡

፡ መልዕክተኛዉም አዎ እንዴታ ሐጁ ትክክል ነዉ አንቺም ከአላህ አጅር ታገኛለሽ በማለት መልስ መለሱላት፡፡(ሙስሊም የዘገቡት)

4. *አራተኛዉ መስፈርት ከባርነት ነፃ መሆን ነዉ፡፡ ከባርነት ነፃ ካልሆነ አቅም ስለሌለዉ ሐጅ ግዴታ አይሆንበትም ፡፡

5. *አምስተኛዉ መስፈርት አካላዊ እና ቁሳዊ አቅሙ የተሟላለት ሐጅ ለማድረግ ሲሄድና ሲመጣ እንዲሁም ለተለያዩ ወጮች የሚያወጣዉ በቂ ገንዘብ ያለዉ መሆን፡፡ እዳዎች ካሉበት እዳዎቹን ከከፈለ በኃላ ከተለያዩ ግዴታ ከሆኑ ወጮችና አስፈላጊ ጉዳዮቹ የተረፈ መሆን ለምሳሌ፡- ከሚመገብበት፣ ከሚጠጣበት፣ ከሚለብስበት

ከሚያገባበት፣ ከሚቀመጥበት፣ ከሚጋልበዉ የተረፈ እንዲሁም እዉቀትን ያዘሉ መፅሀፎችና ሌሎችም አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮቹን ካሟላ በኃላ የሚተርፍ ገንዘብ መኖር አለበት፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡

﴿وَلِلَّهِ عَلَى النَّاسِ حِجُّ الْبَيْتِ مَنِ اسْتَطَاعَ إِلَيْهِ سَبِيلًا ۚ﴾ آل عمران ٩٧

(ቤቱን ወደርሱ መጓዝ ለሚችሉ ሁሉ ይነበኙ ዘንድ አላህ በሰዎች ላይ ግዴታ አድርጓል) (አሊ ዒምራን 97) ፡፡

ሴትን በተመለከተ አብሮአት የሚሄድ ዘመድ (መህረም) መኖሩ መጓዝ ለሚችሉ ከሚለዉ ይገባል፡፡ ዘመድ የሌላት ሴት በኢስላም ህግ (ሸሪዓ)መሰረት መንገድ መጓዝ ክልክል ስለሆነ ሐጅ ግዴታ አይሆንባትም፡፡ ሴት ሐጅ ለማድረግም ይሁን ለሌላ፤ ጉዞዉ አጭርም ይሁን ረዢም፤ ከሷ ጋር ሴቶች ቢኖሩም ባይኖሩም; ዉበት ያላት ወጣት ብትሆንም ዉበት የሌላት አሮጊት፡ በአዉሮፕላን ቢሆንም በሌላ ነገር ያለዘመድ ጉዞ አይፈቀድላትም ፡፡ ኢብኑ አብባስ ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዳወሱት ረሱል(ሶ.ዐ.ወ) ሲመክሩ (ኹጥባ) ሲያደርጉ ሰምቻለሁ (ማንኛዉም ወንድ ከዘመዷ ጋር ካልሆነ በስተቀር ከሴት ጋር ማግለል አይፈቀድለትም ፡፡ ሴትም ከዘመዷ ጋር ካልሆነ በስተቀር ማንኛዉንም ጉዞ መጓዝ አትችልም ብለዉ ሲናገሩ አንድ ሰዉ ቆመና የአላህ መልእክተኛ ሆይ ባለቤቴ(ሚስቴ) ሐጅ ለማድረግ ከቤት ወጥታለች እኔ ደግሞ ለጦር (ለጂሃድ) ተመዝግቢያለሁ ሲል አማከራቸዉ ፡፡ የአላህ መልዕክተኛም ከባለቤትህ ጋር ተጓዝና ሐጅ አድርግ በማለት መልስ መለሱለት)፡ ፡ (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት) ከሴቶች ጋር ነዉ የምትጓዘዉ ወይስ ብቻዋን ፤ ዉበት ያላት ቆንጆ ናት ወይስ አይደለችም ፤ ታማኝ ናት ወይስ አይደለችም ብለዉ የአላህ መልዕክተኛ በዝርዝር የጠየቁት ነገር የለም፡፡

ኢስላም ሴትን ያለ ዘመድ ጉዞ ከመጓዝ የከለከለበት ጥበቡ(ሚስጥሩ) የተለያዩ ወንጀለኞች፣ አመፀኞች፣የብክለትና የተንኮል ባለቤቶች እንዳይዳፈሯት(የነርሱ ስሜት ማራገፊያ እንዳትሆን)ክብሯንና ደህንነቷን ለመጠበቅ ነዉ ። ሴት በተፈጥሮዋ ግንዛቤ ላይ እና ለህይወቷ በመከላከል ዙሪያ ድክመት ስላለባት ። ወንዶችም በጣም ስለሚፈልጓት ልትታለልና ልትሸነፍ ትችላለች ። እሚጠባበቃትና እሚከታተላት ዘመድ ሳይኖራት ጉዞ የተከለከለችበት ምክንያቱና ጥበቡ ይህ ነዉ፡ ፡ ለዚህም ነዉ አብሯት የሚጓዘዉ ዘመድ ለአካለ መጠን የደረሰና የአዕምሮ ባለቤት መሆን አለበት ተብሎ መስፈርት የተደረገዉ ። ለአካለ መጠን ያልደረሰ ዘመድና ቂል (ሞኝ) መህረም ለመሆን በቂ አይደለም ።

*ዘመድ የሚባሉት ባለቤቷና የስጋም ሆነ የጡት ዘመድ ወይም በጋብቻ ምክኒያት ምንጊዜም እሷን ማግባት ክልክል የሚሆንበት ሰዉ ማለት ነዉ።።

<u>የስጋ ዘመድ የሚባሉት ሰባት ናቸዉ</u>

1. መሰረት የሆኑ ዘመዶች አሉ እነሱም፡- አባቶችና አያቶች ደረጃቸዉ ከፍ ሚልም፡- በአባትም በእናትም በኩል ያሉት

ተመሳሳይ ናቸዉ::ደረጃቸው ከፍ ያለ ማለት አባት አያት ቅድመ አያት እያለ እየጨመረ መሄድ ማለት ነው::

2. ቅርንጫፍ የሆኑ ዘመዶችም አሉ እነሱም፡- ወንድ ልጆችና የወንድ ልጆች ወንድ ልጆቻቸዉና የሴት ልጆች ወንድ ልጆቻቸዉ ናቸዉ ደረጃቸዉ ዝቅ ቢልም (ደረጃቸው ዝቅ ያለ ማለት ልጅ የልጅ ልጅ የልጅ ልጅ ልጅ እያለ መሄድ ማለት ነው)

3. ወንድሞች በአባትና በእናት የሚገናኙ ቢሆኑም ወይም በአባት ብቻ እንዲሁም በእናት ብቻ ::

4. የአባት የሆኑ አጎቶች አጎትነታቸዉ በአባትና በእናት የሚገናኙ ቢሆኑም ወይም በአባት ብቻ እንዲሁም በእናት ብቻ አጎትነታቸዉ ለሴቷ ቢሆኑም ወይም ለአባቶቿና ለእናቶቿ ተመሳሳይ ነዉ ምክኒያቱም ለአንድ ሰዉ አጎት ከሆነ ለዝርያዎቹ በሙሉ ደረጃቸዉ ዝቅ ቢልም አጎታቸዉ ይሆናል::

5. የእናት የሆኑ አጎቶች አጎትነታቸዉ በአባትና በእናት የሚገናኙ ቢሆኑም ወይም በአባት ብቻ እንዲሁም በእናት ብቻ አጎትነታቸዉ ለሴቷ ቢሆኑም ወይም ለአባቶቿና ለእናቶቿ ተመሳሳይ ነዉ ::ምክኒያቱም ለአንድ ሰዉ አጎት ከሆነ ለዝርያዎቹ በሙሉ ደረጃቸዉ ዝቅ ቢልም አጎታቸዉ ይሆናል::

6. የወንድሞች ወንድ ልጆቻቸዉና እንዲሁም ወንድ ልጆቻቸዉ ፤ የወንድሞች ሴቶች ልጆቻቸዉ ወንዶች ልጆቻቸዉ ደረጃቸዉ ዝቅ ቢልም ወንድምነታቸዉ በአባትና በእናት ብቻ የሚገናኙ ቢሆኑም ወይም በአባት ብቻ እንዲሁም በእናት ብቻ ::

7. የእህቶች ወንድ ልጆቻቸዉና የወንድ ልጆቻቸዉ ወንድ ልጆች ፤ እንዲሁም የእህቶች ሴቶች ልጆቻቸዉ ወንዶች ልጆች ደረጃቸዉ ዝቅ ቢልም እህትነታቸዉ በአባትና በእናትብቻ የሚገናኙ ቢሆኑም ወይም በአባት ብቻ እንዲሁም በእናት ብቻ::

የጡት ዘመዶች ከስጋ ዘመዶች ጋር ተመሳሳይ ናቸዉ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ)እንዲህ ብለዋል ::-(በስጋ ዘመዶች ላይ ክልክል የሆነ ማንኛዉም ነገር በጡት ዘመዶች ላይ ክልክል ነዉ)::

<u>በጋብቻ ምክኒያት ዘመድ ሊሆኑ የሚችሉት አራት ናቸዉ</u>

1. ሚስት የባሏ ወንድ ልጆች ፣የወንድ ልጆቹ ወንድ ልጆች እንዲሁም የሴት ልጆቹ ወንድ ልጆች ደረጃቸዉ ዝቅ ቢልም

2. ሚስት የባሏ አባቶችና አያቶች በአባት ወይም በእናት በኩል ቢሆኑ እንዲሁም ደረጃቸዉ ከፍ ቢልም

3. ማንኛዋም ሴት የሴት ልጆቿ ባሎች፣ የወንድ ልጆቿ ሴት ልጆች ባሎች እና የሴት ልጆቿ ሴት ልጆች ባሎች ደረጃቸዉ ዝቅ ቢልም እነኝህ ሶስት ዘርፎች በሚስት ላይ ትክክለኛ የሆነ ጋብቻ በመፈፀሙ ብቻ

ባል ከሚስቱ ጋር ከማግለሉና ግንኙነት ከመፈፀሙ በፊት ቢፈታትም እንኳ ዝምድናቸዉ ይፀድቃል

4. ሴቶች የእናቶቻቸዉ ባሎች ፣የአያቶቻቸዉም ባሎች በደረጃ ከፍ ቢሉም በአባት በኩል ቢሆኑም እንዲሁም በእናት ነገር ግን እነዚህ ላይ ትክክለኛ በሆነ ጋብቻ መልክ ግንኙነት የፈፀሙ ካልሆነ ዝምድናቸዉ አይፀድቅም ስለዚህ አንድ ሰዉ ሴት ቢያገባ ነገር ግን ግንኙነት ሳይፈፅም ቢፈታት ለሴት ልጆቿ ደረጃቸዉ ዝቅ ቢልም ዘመድ ሊሆን አይችልም

በቂ ገንዘብ የሌለዉ ሀጅ ማድረግ ግደታ አይሆንበትም ነገር ግን በቂ ገንዘብ እያለዉ የአቅም ድክመት ካለበት ድክመቱ ምን እንደሆነ መመልከት አለብን ፡፡ ድክመቱ ሊወገድ የሚችል ከሆነ ይወገዳል ተብሎ ተስፋ የሚደረግ በሽታን ይመስል ከበሽታዉ እስከትድን ድረስ ጠብቅ(ታገስ) ይባላል፡፡ ከዚያም ከበሽታዉ ሲድን የሀጅን ስራዎች ራሱን ችሎ መስራት አለበት፡፡ ድክመቱ ይወገዳል ተብሎ የማይታሰብ ከሆነ እርጅናና ይድናል ተብሎ

ተስፋ የማይደረግለት በሽታን ይመስል ግዴታ የሆነበትን ሐጅ እሱን ወክሎ የሚሰራለትን ሰዉ ይተካ። ኢብኑ አብባስ ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዳወሱት ኸስአም ከሚባል ጎሳ አንድት ሴት የአላህ መልዕክተኛ ሆይ እግመሉ ጀርባ ላይ ተስተካከሎ መቀመጥ በማይችልበት ሁኔታ በጣም ትልቅ ሽማግሌ በሆነበት ሰዓት አባቴን የሐጅ ግዴታ አገኘዉ ምን ማድረግ አለበት በማለት ጠየቀች። መልዕክተኛዉም እሱን (አባትሽን)ተክተሽ አንቺ ሐጅ አድርጊ በማለት መልስ መለሱላት።

እነኝህ መስፈርቶች ሐጅ ግዴታ ይሆን ዘንድ መሟላት ያለባቸዉ ናቸዉ። እነኝህ መስፈርቶች መገምገማቸዉ ከአላህ ጥበብ ፣ እዝነትና ፍትህ ጋር የሚስማማ ነዉ አላህ እንዲህ ብሏል:

﴿وَمَنۡ أَحۡسَنُ مِنَ ٱللَّهِ حُكۡمٗا لِّقَوۡمٖ يُوقِنُونَ﴾ المائدة ٥٠

(ፅኑ እምነት ላላቸዉ ሰዎች በፍርድ ከአላህ የተሻለ ማን ነዉ?) (አል-ማኢደህ 50)



ስለ ሐጅ ስራ አፈፃፀም ስርዓቶችና ስለ ኢህራም ክልሎች

የኢሕራም ክልሎች በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ጊዜን የሚመለከት እንዲሁም ቦታን የሚመለከት ፡፡

1. ጊዜን የሚመለከተዉ ከሐጅ ጋር ብቻ የተሳሰረ ነዉ ዑምራ ለማድረግ የጊዜ ገደብ የለዉም፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-(የሐጅ ጊዜ የታወቁ ወራት ናቸዉ) እነሱም ሶስት ናቸዉ ሸዋል፣ ዙል ቂዕዳና ዙል ሒጃ በመባል ይታወቃሉ፡
2. ሌላዉ ቦታን የሚመለከት ነዉ እነሱም፡- አምስት/5/ ናቸዉ ነቢዩ ﷺ የከለሏቸዉ የሆኑ ኢብኑ አብባስ ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዳወሱት ረሱል ﷺ ለመዲና ህዝቦች ዙል ሑለይፋህ፡ ለሻም ህዝቦች አልጁህፋህ ፣ ለነጅድ ህዝቦች ቀርነል መናዚል እና ለየመን ህዝቦች የለምለምን የኢህራም ክልል አድርገዋል ፡፡ እነኝህ ክልሎች አሁን ስማቸዉ ለተጠቀሱት ህዝቦችና ሐጅ ወይም ዑምራ ለማድረግ በነሱ በኩል አቋርጠዉ ለሚመጡ ህዝቦች ኢሕራም የሚያደርጉበት ክልሎች (ሚቃቶች)ናቸዉ፡፡ መኖሪያቸዉ ከሐረም ክልል ዉጪ ከሚቃት ክልሎች ዉስጥ ያሉ ከተሞች(እንደ ጅዳ የመሳሰሉት አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች)

ኢሕራም የሚያደርጉት ባሉበት ቦታ ሲሆን ሚቃታቸዉ መኖሪያቸዉ ነዉ።። የመካ ከተማ ነዋሪዎች ሐጅ ለማድረግ ከቤታቸዉ ኢህራም ያድረጉ ።።(ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት) አዒሻ አላህ ይዉደድላትና ነቢዩ ﷺ ለኢራቅ ህዝቦች ዛቱ ኢርቅ የሚባል ክልል አድርገዋል ።።(አቡዳዉድና ነሳዒ የዘገቡት)

1. **የመጀመሪያዉ ዙል ሑለይፋ (አብያር አሊይ) ተብሎ ይጠራል** ።። በመካ ከተማና በዙልሑለይፋ መካከል አሥር መራሂሎች ይገኛሉ (450 ኪ.ሜ) የመዲና ሰዎች ኢህራም የሚያደርጉበት ክልል ነዉ እንዲሁም በነሱ በኩል አቋርጠዉ ለሚመጡ ህዝቦች
2. **ሑለተኛዉ አል ጁህፋ ይባላል** የቆየች የዱሮ ከተማ ስለነበረች ፈራርሳለች በእሷና በመካ ከተማ መካከል ሶስት መራሂሎች ይገኛሉ (183 ኪ.ሜ) ራቢግ እሚባል ቦታ ላይ በጁህፋ ለዉጥ የሻም ሰዎችና እንዲሁም በነሱ በኩል አቋርጠዉ ለሚመጡ ህዝቦች ኢህራም የሚያደርጉበት ክልል ነዉ ነገር ግን በዙል ሑለይፋ ላይ ካለፉ ዙልሑለይፋ ላይ ኢህራም ማድረግ ግደታ ይሆንባቸዋል ።።
3. **ሶስተኛዉ ቀርነል መናዚል ይባላል** (አሰይል) ተብሎም ይጠራል በእሱና በመካ ከተማ መካከል ሁለት መራሂሎች ይገኛሉ (75 ኪ.ሜ) የነጅድ ሰዎችና

እንዲሁም በነሱ በኩል አቋርጠዉ ለሚመጡ ህዝቦች ኢህራም የሚያደርጉበት ክልል ነዉ።።

4. **አራተኛዉ የለምለም ይባላል** ቲሃማህ በሚባል አካባቢ የሚገኝ የተራራ ወይም የቦታ ስም ነዉ በመካና በየለምለም መካከል ሁለት መርሃላዎች ይገኛሉ (92 ኪ.ሜ) (አስ ሰዕዲያ) ተብሎም ይጠራል ።። ለየመን ህዝቦችና እንዲሁም በነሱ በኩል አቋርጠዉ ለሚመጡ ህዝቦች ኢህራም የሚያደርጉበት ክልል ነዉ።።
5. **አምስተኛዉ ዛቱ ኢርቅ ይባላል** የነጅድ ሰዎች (አዶሪበህ) ብለዉ ይጠሩታል በመካና በዛቱ ኢርቅ መካከል ሁለት መርሃላዎች ይገኛሉ (94 ኪ.ሜ) ለኢራቅ ህዝቦችና እንዲሁም በነሱ በኩል አቋርጠዉ ለሚመጡ ህዝቦች ኢህራም የሚያደርጉበት ክልል ነዉ።።

መኖሪያቸዉ ከሐረም ክልል ዉጪ ከሚቃት ክልሎች ዉስጥ ያሉ ከተሞች ኢሕራም የሚያደርጉት ባሉበት ቦታ ሲሆን ሚቃታቸዉ መኖሪያቸዉ ነዉ።። የመካ ከተማ ነዋሪዎች ሐጅ ለማድረግ ከቤታቸዉ ኢህራም ሲያደርጉ ዑምራ ለማድረግ ግን ከሐረም ክልል ዉጭ ተንዒም ሄደዉ ኢህራም ያድርጉ ነበዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- ለአቡ በከር ልጅ አብደረህማን ለሚባለዉ አኢሻ ዑምራ ማድረግ በፈለገች ጊዜ ለዑምራ ኢህራም እንድታደርግ እህትህን ያዝና ከሐረም ክልል ዉጭ ዉጣ ብለዉ አዘዉታል።።

ለኢሕራም በተከለሉ ቦታዎች በግራና በቀኝ አቅጣጫ አቋርጠዉ ለሚመጡ ሰዎች ከተከለሉት ቦታዎች ለነሱ በጣም በሚቀርቧቸዉ አቅጣጫ ሲደርሱ ኢህራም ማድረግ አለባቸዉ በግራና በቀኝ አቅጣጫ ለኢህራም ከተከለሉ ቦታዎች ማንኛዉንም ማግኘትና መቅጣጨት ያልቻሉ ሰዎች ለምሳሌ ፡- ሱዳን ሀገር የሚኖሩና እንዲሁም በነሱ በኩል አቋርጠዉ ለሚመጡ ህዝቦች ኢህራም ማድረግ ያለባቸዉ ጂዳ ሲደርሱ ነዉ፡፡

ሐጅን ወይም ዑምራን ያሰበ ሰዉ እነኝህ ክልሎች(ሚቃቶች) ላይ ኢህራም ሳያደርግ ማለፍ አይፈቀድለትም ሐጅን ወይም ዑምራን በማሰብ በአዉሮፕላን የሚጓዝ ለኢህራም በተመደቡ(በተከለሉ) ቦታዎች አቅጣጫ በሚደርስ ጊዜ ኒያ(ኢህራም) ማድረግ ግዴታ ይሆንበታል እነኝህ ክልሎች ሳይደርስ የኢህራም ልብሱን በመልበስ በቅድሚያ ይዘጋጅ በነሱ አቅጣጫ ሲደርስ በፍጥነት የኢህራምን ኒያ ማሰብ (መነየት) አለበት፡፡

ኢህራሙን አዉሮፕላኑ ጅዳ እስከሚያርፍ ድረስ ማቆየት አይቻልም ይህን ማድረግ የአላህን ወሰኖች ከመተላለፍ ይመደባል አላህ (ሱ.ወ) (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል

﴿وَمَن يَتَعَدَّ حُدُودَ ٱللَّهِ فَقَدۡ ظَلَمَ نَفۡسَهُۥ﴾ البقرة ٢٢٩

[የአላህን ወሰኖች የተላለፈ ራሱን በድሏል] አጥሎላቅ 1 [የአላህን ሕግ የሚተላለፍ እነርሱ በደለኞች ናቸዉ] አል-በቀራህ 229

﴿وَمَن يَعۡصِ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ وَيَتَعَدَّ حُدُودَهُۥ يُدۡخِلۡهُ نَارًا خَٰلِدٗا فِيهَا وَلَهُۥ عَذَابٞ مُّهِينٞ﴾ النساء ١٤

[አላህንና መልዕክተኛዉን ያልታዘዘ ወሰኖችን የጣሰም እሳትን ያስገባዋል፡፡ ከዉስጧም ዘወትር ይኖራል ፡፡አዋራጅ የሆነ ቅጣት ይጠብቀዋል] ፡፡ (አኒሳዕ 14)

ሐጅ ወይም ዑምራ ለማድረግ ሳያስብ በኢህራም ክልሎች ላይ ያለፈ ካለፈ በኋላ ሐጅ ወይም ዑምራ ማድረግ ከፈለገ መስራት አለብኝ ብሎ እወሰነበት ቦታ ላይ ኒያ (ኢህራም) ያድርግ ሐጅ ወይም ዑምራ ለማድረግ ሳያስብ በኢህራም ክልሎች ላይ ያለፈ መካ መሄድ የፈለገዉ ለሌላ ጉዳይ ከሆነ (ለምሳሌ) እዉቀት ፍለጋ፣ ቤተሰብ ለመጠየቅ ፣ ለህክምና ፣ ለንግድና ለሌላም ነገር ይሁን ከአሁን በፊት ሐጅ አድርጎ ከሆነ ኢህራም ማድረግ ግዴታ አይሆንበትም፡፡

ለሐጅ ወይም ለዑምራ ኒያ(ኢህራም) ማድረግ ሐጅና ዑምራ በሰራ ሰዉ ላይ ግዴታ አይደለም ሐጅና ዑምራ በሰዎች ላይ ግዴታ የሚሆኑት በዕድሜ (በሕይዎት) አንድ ጊዜ ብቻ ነዉ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ)ሐጅ በሰዎች ላይ በየዓመት ሁል ጊዜ ግዴታ ይሆናልን ?

ተብለዉ ተጠየቁ ነቢዩ ﷺ በዕድሜ አንድ ጊዜ ብቻ ነዉ ከአንድ በላይ የሚጨምር ካለ ትርፍ ነዉ በማለት መልሰዋል፡፡ እንዲሁ ዑምራም ከሐጅ ጋር ተመሳሳይ ነዉ በዕድሜ አንድ ጊዜ ብቻ ነዉ ግዴታ የሚሆነዉ፡፡

ነገር ግን በነኚህ ለኢህራም በተከለሉ (በተመደቡ) ቦታዎች ላይ ለሚያልፍ ሰዉ ለዑምራም ሆነ ከአሁን በፊት ሐጅ ያደረገ ቢሆንም እንኳ የሐጅ ወራት ገብቶ ከሆነ ለሐጅ አጂር እንዲፃፍለትና ለኢህራም በተመደቡ ከልሎች አጠገብ ምን ጊዜም ባለፈ ቁጥር ማንኛዉም ሰዉ ኢህራም ማድረግ ግዴታ ነዉ የሚል ዉዝግብ ስላለ ከዚህ ለመዉጣት ሲባል ኢህራም አድርጎ ማለፉ በደረጃ ይበልጣል፡፡

<u>የሀጅ ስራ አፈፃፀም ሂደት በሶስት ይከፈላል</u>

* የመጀመሪያዉ (አት-ተመቱዕ) ዑምራ አድርጎ እስከ ሐጅ ድረስ ነፃ መሆን ተመቱዕ ማለት በሐጅ ወራት ለዑምራ ብቻ ኒያ (ኢህራም) በማድረግ ከዚያም የኡምራን ስራ ከዕባን በመዞር ፤ በሶፋና በመርዋ መካከል ምልልስ በማድረግና ፀጉሩን በማሳጠር እንደጨረሰ ከኢህራሙ ይፈታ(ወደ መደበኛ አኗኗሩ ይመለስ) ፡፡

በዚያዉ አመት ዙል ሂጃ ስምንት ላይ(የዉመ-አተርዊያ) ለሀጅ ኒያ (ኢህራም) ማድረግ ነዉ፡:

* ሁለተኛዉ **አል ቂራን** ይባላል አልቂራን ማለት በሐጅ ወራት ዑምራንና ሐጅን በማጣመር በአንድ ላይ መነየት (ኢህራም) ማድረግ ወይም(ቂራን ማለት)በሐጅ ወራት ዑምራን ኒያ(ኢህራም) አድርጎ ከገባ በኋላ ከዚያም የኡምራዉን ጦዋፍ ከመጀመሩ በፊት(በተለያዩ ምክንያቶች የሀጅ ኒያን በዑምራ ላይ ማካተት ነዉ፡፡ መካ እንደደረሰ የመግቢያ ጦዋፍ(ጦዋፈ ልቁዱም)ያደርጋል በሶፋና በመርዋ መካከልም ለዑምራና ለሀጅ አንድ ጊዜ ብቻ (ማለት ሰባት ጊዜ)ምልልስ ያደርጋል ከዚያም እስከ ኢድ ቀን(ዙልሂጃ 10) እስከሚደርስ በኢህራም ላይ መቆየትአለበት ፡፡ የመግቢያ የሆነዉን ጦዋፍ ከጨረሰ በኋላ በሶፋና በመርዋ መካከል የሚያደርገዉን ምልልስ ለጦዋፈል ኢፋዳ(የኢድ ቀን ወይም በሌላ ቀን ከዕባን) እስከሚዞር ድረስ ማቆየት ይቻላል . በተለይም አንድ ሰዉ መካ ሲደርስ የዘገየ ሆኖ ከደረሰ በሶፋና በመርዋ መካከል ምልልስ ካደረኩ ሀጅ ያመልጠኛል ብሎ የሚፈራ ከሆነ ፡፡

* ሶስተኛዉ ኢፍራድ ይባላል. አልኢፍራድ ማለት በሐጅ ወራት ለሐጅ ብቻ ኒያ (ኢህራም) ማድረግ ነዉ መካ እንደደረሰ የመግቢያ ጦዋፈ (ጦዋፈልቁዱም) እና የሐጅን ሰዕይ (በሶፋና በመርዋ መካከል ምልልስ) ያደርጋል፡፡ ከኢህራሙ ሳይፈታ የኢድ ቀን (ዙል ሂጃ 10) እስከሚደርስ መቆየት አለበት ::የሐጅን ሰእይ ከሚና መልስ ማድረግ ይቻላል እዚህ ላይ የምንረዳዉ ሀጅ ብቻ ለማድረግ ኒያ ያደረገ እና ሐጅና ዑምራን አጣምሮ ለመስራት ኒያ (ኢህራም) ያደረገ ተመሳሳይ ስራ እንደሚሰሩ እንረዳለን ነገር ግን ቃሪን ሁለት ስራዎችን ባንድ ጊዜ ስለሰራ ማረድ አለበት፡፡ (ሙፍሪድ) ለሐጅ ብቻ ኒያ ያደረገ ማረድ የለበትም፡፡

ከሶስቱ የሐጅ መፈፀሚያ መንገዶች በደረጃ ተመቱዕ በላጭ ነዉ ምክንያቱም ረሱል(ሶ.ዐ.ወ)ባልደረባዎቻቸዉን ያዘዟቸዉና የመረጡላቸዉ ተመቱዕን ነበርና ለዚህም ነዉ ሀጅ ብቻ ለማድረግ ኒያ (ኢህራም) አድርገዉ የነበሩትን ወደ ዑምራ እንዲቀይሩ ያዘዟቸዉ፡፡ ኢብኑ አብባስ ስራቸውን ይውደድላቸውና ስለሀጅ ሙተኣ ተጠየቀ ሙሀጅሮች ፤ አንሷሮች፤ የረሱል (ሶ.ዐ.ወ)ሚስቶችና እኛም ሀጅ ብቻለማድረግ ኒያ አደረግን መካ እንደገባን ረሱል (ሶ.ዐ.ወ)ሐጅ ብቻ ለማድረግ ኒያ አድርጋችሁ የነበረዉን ወደ ዑምራ ቀይሩት አሉ ወደ አላህ ለመቃረብ የሚሰዋ እንሰሳ የያዘ ሲቀር ከዕባን እንዲሁም በሶፋና በመርዋ መካከል

ምልልስ አደረግን ከሚስቶቻችን ጋር ግንኙነት ፈፅምን ማንኛዉንም ልብስ ለበስን ብሏል (ቡኻሪ የዘገቡት)

ሙተመቲዑ ወይም ቃሪኑ የሚያርደዉ(የሚሰዋዉ) ካጣ እንዲሁም የሚገዛበት ብር ካላገኘ ብር ቢኖረዉም ለቀለብና ለሀገሩ መመለሻ የሚፈልገዉ ከሆነ ማረድ ግዴታ አይሆንበትም ፡ ፡ ፆም ይፁም አላህ እንዲህ ብሏል፡- (እስከ ሐጅ ድረስ በዑምራ የተጣቀመ ከሀድይ የቻለዉን (ለመስዋዕትነትያቅርብ) ይህን ያላገኘ በሐጅ ወራት ሶስት ቀናትን(ወደ ቤተሰቦቻችሁ) ስትመለሱ ደግሞ ሰባት ቀናትን ይፁም (ሀድይን የሚተኩና የተሟሉ)አስር ቀናት ይሆናሉ ፡፡

ሶስቱን ቀናት በአያምትተሸሪቅ ቀናት ዉስጥ መፆም ይችላል እነኝህ ቀናት ከዙል ሂጃ አ11ኛዉ ፤ አ12ኛዉና አ13ኛዉ ናቸዉ ፡ ፡ አሊሻና ኢብኑ ኡመር ፡-አያመትተሸሪቅ መፆም አይቻልም ሀድይ (የሚሰዋዉ) ያላገኘ ሰዉ ሲቀር ብለዋል፡፡ (ቡኻሪ የዘገቡት) ከነኝህ ቀናት በፊት መፆም ይችላል ለዑመራ ኒያ(ኢህራም) ካደረገ በኃላ ማረድ እንደማይችል እርግጠኛ ከሆነ የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ፡- ዑምራ ቂያማ ቀን ድረስ ከሐጅ ዉስጥ ገብታለች ብለዋል ፡፡ ሶስቱን ቀናት ለዑመራ ኒያ(ኢህራም) ካደረገ በኃላ የፆመ በእርግጥ ሐጅ ዉስጥ እንደፆመ ነዉ፡፡ ነገር ግን እነኝህን ቀናት የኢድ ቀን(ዙልሂጃ 10) መፆም

አይቻልም፡፡ አቡ ሰዒድ ስራቸውን ይውደድላቸውና ረሱል (ሶ.ዐ.ወ)ሁለት ቀናትን ከመፆም ከልክለዋል ዒድ አልፈጥርና ከዙል ሂጃ አ 10ዉን ቀን ብሏል ::(ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት)

እነኝህን ሶስት ቀናት አከታትሎም ሆነ ለያይቶ መፆም ይችላል ግን ከአያመትተሸሪቅ ማዘግየት አይችልም ሌሎቹን ሰባት ቀናት ወደ ቤተሰቦቹ ሲመለስ ከፈለገ አከታትሎ ወይም ለያይቶ መጾም ይችላል፡፡ አላህ ፆምን ግዴታ አደረገ እንጅ በተከታታይ መፆም አለበት የሚል መስፈርት አላስቀመጠም፡፡

የሐድዩ (የሚሰዋዉ) አይነት ግመል፣ ከብት፣ በግና ፍየል ናቸዉ፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿وَلِكُلِّ أُمَّةٖ جَعَلۡنَا مَنسَكٗا لِّيَذۡكُرُواْ ٱسۡمَ ٱللَّهِ عَلَىٰ مَا رَزَقَهُم مِّنۢ بَهِيمَةِ ٱلۡأَنۡعَٰمِۗ﴾ الحج ٣٤

(ለሁሉም ህዝቦች ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን ደንግገናል የአላህን ስም ከለማዳ እንስሳት በለገሳቸዉ ሲሳይ ያወሱት ዘንድ (ይህን አደረግን) (አል-ሐጅ34) ለማዳ እንስሳት የሚባሉት ግመል ከብት ፍየል እና በግ ናቸዉ አንድ ፍየል ወይም በግ ለአንድ ሰዉ በቂ ነዉ አንድ ግመል ወይም ከብት ለሰባት ሰዎች በቂ ነዉ፡፡

ጃቢር ስራቸውን ይውደድላቸውና ረሱል ﷺ ግመል ወይም ከብት ላይ ሰባት ሰዎች እንዲጋሩ አዘዉናል ብሏል፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበዉታል)

<u>የሚታረደዉ እንስሳ ሁለት ነገሮች ያሟላ መሆን አለባቸዉ</u>

1. ግመል ከሆነ አምስት ዓመት የሞላዉ መሆን ከብት ሁለት አመት ፍየል አንድ ዓመት በግ ስድስት ወር ከነዚህ ዕድሜ ያነሰ ከሆነ አይቻልም ረሱል ﷺ እንዳታርዱ አምስት ዓመት የሞላት ግመል ካልሆነች በስተቀር ይህችን ግመል ማግኘት ካልቻላችሁ ስድስት ወር የሞላዉ በግ ማረድ ትችላላችሁ ብለዋል ፡፡ (ቡኻሪ ሲቀሩ ሌሎቹ የዘገቡት)

2. ረሱል ﷺ እንድንር.ቃቸዉ ያዘዙን ከሆኑት አራት ነዉሮች ያገለለ መሆን: የዓይኗ መጥፋት ግልፅ የሆነ. በግልፅ የሚታይ በሽታ መኖር. የተሰበረች መሆን .የከሳች መሆን

ሀድዩ የሚታረድበት ቦታ ሚና ፤ መካና ሀረም ነዉ ረሱል ﷺ መካ የሚገኙ መንገዶች በሙሉ እነሱ ላይ ማረድ እንዲሁም ወደ መካ መግቢያ ማድረግ ይፈቀዳል ብለዋል፡፡ (አቡዳዉድ

ዘግበዉታል) መካ መታረዱ ለድሆች በጣም ጠቃሚ ነዉ መካ ሲታረድ የዒድ ቀን ወይም ከዒድ በኃላ ባሉት ሶስት ቀናት ዉስጥ ስለሆነ ለድሆች በጣም ጠቃሚ ነዉ ሀድዩን ከሀረም ክልል ዉጭ ያረደ ለምሳሌ አረፋ ላይ ወይም ሌላ ቦታ ግልፅ በሆነዉ ንግግር እንዳላረደ ነዉ የሚቆጠረዉ።።

የሚታረድበት ጊዜ የዒድ ቀን ፀሃይ ከፍ እንዳለች ሶላት የሚሰገድበት መጠን ካለፈ ጀምሮ አያመትተሽሪቅ መጨረሻ ድረስ ነዉ ረሱል ﷺ የኢድ ቀን ረፋድ ላይ ነዉ ያረዱት አያመትተሽሪቅ በሙሉ ማረድ ይቻላል የሚልም ሐዲስም አለ

የቂራንና የተመቱዕ ሐድይን ከዒድ ቀን በፊት ማረድ አይፈቀድም ረሱል ﷺ ከዒድ ቀን በፊት አላረዱም ረሱል ﷺ ሐጅ ላይ የምትሰሯቸዉን ስራዎች ከኔ ያዙ ብለዋል እንዲሁም ከአያመትተሽሪቅ ማሳለፍ አይቻልም።

በነኝህ አራት ቀናት ዉስጥ ቀን ሌሊት ማረድ ይቻላል ግን ቀን መሆኑ በደረጃ የበለጠ ነዉ።።

ሀድዩ መታረድ ያለበት ሁኔታ ግመል ከሆነ ች ግራ እጇን ታስራ እንደቆመች ይህ ካልተቻለ እንደተንበረከከች ማረድ ይቻላል ከግመል ውጭ ያሉ እንስሶች ከሆኑ በጎናቸዉ ከተኙ በኃላ ነዉ መታረድ ያለባቸዉ

የሚያርድ ሰዉ በሚያርድ ጊዜ ቢስሚላ ማለት ግደታ ነዉ የሚታረደዉ እንስሳ የአላህ ስም ካልተወሳበት ሃላል ሊሆን አይችልም(በክት ነዉ) አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-((ሲታረድ) የአላህ ስም ያልተወሳበትን (እንስሳ ሥጋ)አትመገቡ፡፡ እርሱ አመፅ ነዉና)(አል-አንዓም 121)፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ሀድዩ ተቀባይነት አያገኝም መመገብም አይቻልም በክት ነውና፡፡

በኢህራም ወቅት የሚከለከሉ ነገሮች

ማንኛዉም ሐጅ ወይም ዑምራ አድራጊ በኢህራም ወቅትየሚከለከላቸዉ ነገሮች ለሶስት ይከፈላሉ፡፡

በሁለቱም ፆታዎች ላይ ሐራም(ክልክል) የሆነ አለ

በወንዶች ብቻ ክልክል የተደረገ አለ

እንዲሁም በሴቶች ብቻ ህራም የሆነ አለ

<u>በሁለቱም ፆታዎች ላይ ሐራም የተደረገዉ እርሱም፡-</u>

1. የራስን ፀጉር በመላጨትም ይሁን በሌላ መንገድ ማስወገድ አላህ እንዲህ ብሏል፡-(ሐድይ ከሥፍራዉ እስከሚደርስ ድረስ ፀጉራችሁን አትላጩ) ፡፡(አል-በቀራህ 196) በርካታ ዑለማዎች መላ ሰዉነት ላይ የሚገኙ ፀጉሮችን ከራስ ፀጉር ጋር ተመሳሳይ ህግ አድርገዋል ስለዚህ ሙህሪም የሆነ ባጠቃላይ ከመላ ሰዉነቱ ላይ አንዲትንም ፀጉር ቢሆን እንኳ ማስወገድ አይችልም ፀጉሩን የላጨ ምን አይነት መቀጫ እንዳለበት አላህ(ሱ.ወ) በማያሻማ መልክ ተናግሯል፡- (ከመካከላችሁ በሽተኛ የሆነ ወይም ከራሱ ላይ ችግር ያለበት ሰዉ (ቢላጭ) የፆም፣ የምፅዋት ወይም የመስዋእት ቤዛ መክፈል ግድ ይሆንበታል)፡፡ ረሱል (ሶ.ዐ.ወ) ፆሙ ሶስት ቀናት እንደሆነም ምፅዋት ከሆነ ሰዎች

ከሚመገቧቸዉ ሶስት ቁና ለስድስት ድሆች ለያንዳንዳቸዉ ግማሽ ቁና መስጠት መስዋዕት(እርድ) ከሆነ አንድ ፍየል (ወይም በግ)ማረድ እንደሆነ አብራርተዋል ።።

2.ጥፍርን መቁረጥ ወይም መንቀል እጅ ላይና እግር ላይ ያሉ ጥፍሮች ተመሳሳይ ናቸዉ ነገር ግን ጥፍሩ ተሰብሮ ከተቸገረ የሚያስቸግረዉን ብቻ መቁረጥ ይችላል (መቀጫ) ቤዛ የለበትም ። ።

3. ኢሕራም ላደረገ ሰዉ ኢሕራም ካደረገ በኋላ ሰዉነቱም ላይ ሆነ ልብሱ ሽቶ መቀባት አይፈቀድለትም ረሱል ﷺ ዓረፋ ቁሞ እያለ ግመሉ ስለገደለችዉ ሙሕሪም (ሶሃባ) ሽቶ እንዳትቀቡ ት ምክንያቱንም ሲገልፁ የቂያማ ቀን ለብበይክ እያለ ስለሚነሳ ብለዋል።።

4. የጋብቻ ዉል መፈፀም ረሱል ﷺ ሙሕሪም ሰዉ አያገባም አይድርም ፣ አያጭምም ብለዋል (ሙስሊም የዘገቡት) ሙሕሪም የሆነ ሰዉ ማግባትና ለሴት ወልይ በመሆንም ይሁን ወኪል የጋብቻ ዉል መፈፀም አይፈቀድለትም።።

5. በስሜት ከሴት ጋር መነካካት፣ መሳሳምና መደባበስ አይፈቀድዲም

6. ከሴት ጋር ግንኙነት መፈፀም አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡- (በነኝህ (ወራት) ዉስጥ ሐጅን በራሱ ላይ ግዳጅ ያደረገ ሐጅ ዉስጥ ከሴት ጋር መገናኘት፣ (በአላህ ላይ) ማመፅም፣ (ከባልደረቦቹ) ጋር መከራከርም የለበትም) ፡፡ ከሴት ጋር መገናኘት ሐጃጅ (ሙሕሪም) ሊርቃቸዉ የሚገቡ ከሆኑ ነገሮች ክልክልነቱ በጣም ጠንከር ያለ ነዉ፡፡

ከሴት ጋር መገናኘት ሁለት ሁኔታዎች አሉት ፡፡ የመጀመሪያዉ ግንኙነቱ የተፈፀመዉ ከመጀመሪያዉ ተሀሉል በፊት ከሆነ ሁለት ባህሪዎች አሉት እነሱም፡-

- ግመል ወይም ከብት ማረድ ምንም ነገር ሳይመገብ ለድሆች ማከፋፈል
- ሐጁ ዉድቅ ነዉ ግን ማቋረጥ የለበትም ተጨማሪ በሚቀጥለዉ ዓመት ሳያዘገይ ቀጺማዉጣት ግዴታ ይሆንበታል. (ሐጅ ላይ ሙሕሪም ከሚከለከላቸዉ) ከግንኙነት ዉጭ ያሉት ሐጅን ዉድቅ አያደርጉትም፡፡ *ሁለተኛዉ ሁኔታ ግንኙነቱ የተፈፀመዉ ከተሀሉለል አወል(ከመጀመሪያዉ መፈታት) በኋላ ከሆነ ማለት ጀምረተል አቀባ ላይ ጠጠር ከወረወረና ከተላጨ በኋላ ግን ከጦዋፈል ኢፋዷ በፊት ሐጁ ትክክል ነዉ ነገር ግን ሁለት ነገሮች ግዴታ ይሆኑበታል፡፡

- ፍየል (ወይም በግ) ማረድ ምንም ነገር ከሲጋዉ ሳይመገብ ለድሆች ማከፋፈል .
- ከሐረም ክልል በመዉጣት የኢህራም ልብስ ለብሶ ኒያ (ኢህራም) በማደስ ለኢፋዱ ጦዋፍ ማድረግ።

7.ሙህሪም ከሚከለከላቸዉ ነገሮች የዱር አዉሬ ማደን።

ሙህሪም እያወቀ አዉሬ ከገደለ መቀጫ አለበት አላህ እንዲህ ብሏል፡- (ከናንተ እያወቀ ይህን የፈፀመ ከመካከላችሁ ፍትሃዉያን ሰዎች በሚሰጡት ብይን መሰረት የገደለዉን እንስሳ ምትክ ከቤት እንስሳዎች ከዕባ ደራሽ መስዋዕት ይተካል ።። ወይም ድሆችን ያበላል አሊያም ይህን የሚመጥን ፆም ይፆማል)።። (አል-ማኢዳ፡ 95) ለምሳሌ፡- እርግብ ከገደለ ፍየል ምትክ ይሆናል ምርጫ ይሰጠዋል ፍየል አርዶ ለድሆች ማከፋፈል ወይም ፍየሏን በማስገመት በዋጋዋ ልክ ሰዎች ከሚመገቡት የአንድ ጊዜ ምግብ ለድሆች መስጠት ለያንዳንዱ ድሃ ያንድ ቁና ግማሽ ወይም ድሆቹን መመገብ በመተዉ በድሆቹ ቁጥር ልክ የመፆም ምርጫ አለዉ

ዛፍ መቁረጥ በሙህሪም ላይ ሙህሪም ስለሆነ አይደለም የሚከለከለዉ ከኢህራም ጋር የሚያገናኘዉ ነገር የለም።። ሀራም የሚሆነዉ ሀረም ክልል ዉስጥ ባለ ሰዉ ላይ ነዉ ሙህሪም ቢሆንም ባይሆንም ስለዚህ አረፋ ላይ ያለን ዛፍ ሙህሪም የሆነም ያልሆነም መቁረጥ ይችላል .ግን ሙዝደሊፋ እና ሚና ላይ ያሉ

ዛፎች በሙህሪምም ላይ ሆነ ሙህሪም ባልሆነ ክልክል ናቸዉ።። ምክንያቱም አረፋ ከሀረም ክልል ዉጭ ስለሆነ ሙዝደሊፋና ሚና ሀረም ክልል ዉስጥ ስለሆኑ ነዉ ።።

<u>እነኝህ ሰባት ነገሮች በወንድም በሴት ላይ ክልክሎች ናቸዉ።።</u>

ወንዶችን ብቻ የሚመለከቱ ሁለት ክልክል ነገሮች አሉ እነሱም፡-

1. ራስን መሸፈን ረሱል (ሶ.ዐ.ወ) አረፋ ላይ ከግመሉ ወድቆ ስለሞተዉ ሶሃባ ‹‹ራሱን እንዳትሸፍኑ››ብለዋል (ቡኻሪ ሙስሊምየዘገቡት) ወንድ ራሱን በጥምጣምና በኮፊያ በሌላም ነገር መሸፈን አይችልም. ከራሱ ጋር የማይነካካ ከሆነ ጉንጥላ፣ የመኪና ጣራና ድንኳን ሌላም ነገር ቢሆን ችግር የለበትም።። በራሱ ሻንጣዉን ቢሸከም ችግር የለበትም እንዲሁም ዉሃ ዉስጥ ቢገባ ራሱ በዉሃ ቢሸፈን እንኳ ችግር አያመጣም

2. ወንዶችን ብቻ ከሚመለከቱ ክልክል ነገሮች የተሰፋን ልብስ መልበስ ማለትም በተለምዶ የሚለበስ ልብስ ሰዉነቱን ሙሉ በሙሉ የሚሸፍን ጀለቢያን ይመስል ወይም ከሰዉነቱ ከፊሉን የሚሸፍን ሱሪ፣ ፓንት ፣ሹፍ፣ የጅ ጓንትና የግር ሹራብ አብደላ ኢብኑ ኡመር ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዳወሱት ረሱል (ሶ.ዐ.ወ)ሙህሪም ሰዉ ምን አይነት ልብስ ነዉ መልበስ ያለበት

ተብለዉ ተጠየቁ ጀለቢያ፣ጥምጣም፣ በራኒስ ፣ሱሪ፣ኹፍና ማንኛዉንም ልብስ ዘዕፈራንና ወርስ በሚባል ቀለም የተነከረ መልበስ አይፈቀድለትም ብለዋል ::(ቡኻሪናሙስሊም የዘገቡት)ግን ሽርጥ ወይም የሚገዛበት ብር ከሌለዉ ሱሪ መልበስ ይችላል እንዲሁም ነጠላ ጫማ ወይም የሚገዛበት ብር ካላገኘ ሽፍን ጫማ ቢለብስ ችግር የለበትም ረሱል (ሶ.ዐ.ወ)(ሽርጥ ያላገኘ ሱሪ ይልበስ ነጠላ ጫማ ያላገኘ ሽፍን ጫማ ይልበስ ብለዋል(ቡኻሪ ሙስሊም)ቀለበት ሰዓት መነፀር የጆሮ ማዳመጫ ሙሀሪም አይከለከልም ::

እነኝህ ሁለት ክልክል ነገሮች የሚመለከቱት ወንዶችን ብቻ ነዉ. ሴት ግን ፀጉሯን መሸፈን አለባት ኢህራም ላይ የፈለገችዉን መልበስ ትችላለች ግን ጌጦችን ግልፅ ማድረግ ፣ የጅ ጓንት፣ ኒቃብ መልበስና ፊቷን መሸፈን አይፈቀድላትም ወንዶች ባካባቢዋ በሚያልፉ ጊዜ ብቻ ሲቀር ይህ ከሆነ ግን ፊቷን መሸፈን አለባት ሴት ፊቷን ዘመዶቿ ካልሆኑ በስተቀር እወንዶች ፊት መግለፅ ስለማይፈቀድላት::

ለሴትም ሆነ ለወንድ ኢህራም ባደረጉ ጊዜ የሚፈቀድላቸዉ የሆነን የልብስ አይነት መቀየር ይችላሉ::

ሙህሪም ካለፉት ክልክል ነገሮች አንዱን ቢፈፅም ለምሳሌ ፡- ግንኙነት ቢያደርግ አዉሬ ቢገድል ወይም ሌላ ነገር ቢፈጽም ሶስት ሁኔታዋች አሉት፡፡

የመጀመሪያዉ የፈፀመዉ እረስቶ ፣ ባለማወቅ ፣ ተገዶና ተኝቶ ከሆነ ምንም ነገር ወንጀልም ሆነ ቤዛም(ካሳ) የለበትም የሐጅ ስራዉ ዉድቅ አይሆንም ግን ምክንያቱ ከተወገደ በኋላ የሚቀጥል ከሆነ ወንጀለኛ ይሆናል ለምሳሌ፡- ሙህሪም ፀጉሩን ቢሸፍን የተኛ ሆኖ ምንም አይነት ነገር የለበትም ከእንቅልፉ ሲነሳ ቶሎ ፀጉሩን መግለፅ አለበት ፀጉሩን መግለፅ ግዴታ መሆኑን እያወቀ ራሱን በመሸፈን ላይ ከቀጠለ ወንጀለኛ ይሆናል ለጥፋቱም ቤዛ(መቀጫ) ይኖርበታል፡፡

ሁለተኛዉ በቂ የሆነ ምክንያት እያለዉ ክልክል የሆነን ነገር እያወቀ ቢሰራ ክልክልን ያለምክንያት እያወቀ የፈፀመ ሰዉ ለጥፋቱ መቀጫ(ካሳ) ግዴታ እንደሚሆንበት ሁሉ ይህ ነገር እሱንም ይመለከተዋል ወንጀል ግን የለበትም አላህ (ሶ.ዐ.ወ)እንዲህ ብሏል፡-(ከመካከላችሁ በሽተኛ የሆነ ወይም ከራሱ ላይ ችግር ያለበትሰዉ (ቢላጭ)የፆም ፤ የምፅዋት ወይም የመስዋእት ቤዛ መክፈል ግድ ይሆንበታል (አል.በቀራ 196)

ሶስተኛዉ ክልክል የሆነን እያወቀ ቢሰራ በቂ የሆነ ምክንያት ከሌለዉ ቤዛ(መቀጫ) አለበት መንጀለኛም ነዉ፡፡

ኢህራም ላይ የሚከለከሉ ነገሮች በቤዛ(በመቀጫ) ዙሪያ ለአራት ይከፈላሉ

*አንደኛዉ፡ ቤዛ(መቀጫ)የሌለበት እርሱም ጋብቻን መፈፀም

* ሁለተኛዉ፡ መቀጫዉ ግመል የሚሆንበት አለ እነሱም፡- ሐጅ ላይ ከመጀመሪያዉ መፈታት (ተህሉል) በፊት ግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም

* ሶስተኛዉ ፡ መቀጫዉ ከተገደለዉ አዉሬ ተመሳሳዩን(ከቤት እንስሳ) መሰል ከሌለዉ ደግሞ ዋጋዉን ይከፍላል እሱም፡- አዉሬ ማደን ነዉ

* አራተኛዉ ፡ መቀጫዉ ፆም ወይም ምፅዋት ወይም ምስዋዕት የሆነ አለ ባለፈዉ እንደተብራራዉ እርሱም ራስን መላጨት ነዉ፡

ከዚህ ጋር(ማለት ከቁጥር አራት መቀጫ ጋር) ያለፉት ሶስቱ ሲቀሩ ዐሊሞች ማንኛዉም ክልክል ነገር መቀጫዉ ተመሳሳይ ነዉ ብለዋል፡፡

የዑምራ አፈፃፀም ስርዓት

ዑምራ ማለት፡- ኢህራም(ኒያ) ፣ ከዕባን ሰባት ጊዜ መዞር፣ በሶፋና በመርዋ መካከል ሰባት ጊዜ ምልልስ ማድረግ እና የራስ ፀጉር መላጨት ወይም ማሳጠር ነዉ፡፡ ኢህራም ማለት(ኢህራም ማድረጊያዉ ሥፍራ ላይ ሲደርስ) የዑምራን ስራ ለመስራት ኒያ ማድረግ ነዉ ዑምራን ላሰበ ሰዉ ገላዉን መታጠብ ሱና ነዉ ከሚያገኘዉ ሽቶ ጥሩ በሆነዉ ራሱን ና ፂሙን መቀባት ከኢህራም በኋላ የሸቶዉ ሽታ(ከሰዉነቱ ላይ) መገኘቱ አይጎዳዉም ኢህራም ላይ ገላን መታጠብ ለወንድም ሆነ ለሴት ሱና ነዉ የወር አበባ እና የወሊድ ደም የምታይ ሴት ብትሆን እንኳ (ገላን መታጠብ ሱና ነዉ) ከታጠበና ሽቶ ከተቀባ በኋላ የኢህራም (ሁለት) ልብሶችን መልበስ እነሱም፡- ሸርጥና ጋቢ(ፎጣ) ናቸዉ ሴት ግን የፈለገችዉን መልበስ ትችላለች ጌጦችን ግልፅ ማድረግ ፣ ኒቃብና የእጅ ጓንት መልበስ አይፈቀድላትም ::ግን ዘመዶቿ ካልሆኑ ወንዶች አካባቢ በምትሆን ጊዜ ፊቷን መሸፈን አለባት

ከዚያም የወር አበባና የወሊድ ደም የሚያዩ ሴቶች ሲቀሩ የፈርድ ሶላት ጊዜዉ ደርሶ ከሆነ ሶላት ይስገድ፡፡ ግን የፈርድ ሶላት ጊዜዉ ካልደረሰ ከዉዱእ በኋላ የሚሰገዱ ሁለት ረከዓን ኒያ በማድረግ ሁለት ረከዓ ይስገድ፡፡ ሶላት እንደጨረሰ ለብበይክ ዑምረተን በማለት ኒያ (ኢህራም)ያድርግ ::

ትርጉም ፡- ለዑምራ አቤት ብያለሁ ማለት ነዉ ከዚያም የሚቀጥለዉን ይጠቀም(ለብበይክ አልላሁምመ ለብበይክ ለብበይክ ላሸሪከ ለክ ለብበይክ ኢንነል ሀምደ ወንኒዕመተ ለክ ወልሙልክ ላሸሪከ ለክ)

ትርጉም ፡- ጌታዬ ደግሜ ደጋግሜ ለጥሪህ አቤት እላለሁ ተጋሪ የለህም ምስጋና ፀጋና ንግስና ላንተ ብቻ ነዉ አጋር የለህም ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ)ኢህራም ሲያደርጉ የተጠቀሙት ይህንን ነዉ።።ወንዶች በተልቢያ(ለብበይክ አልላሁምመ ለብበይክ በሚሉ) ጊዜ ድምፃቸዉን ከፍ ማድረጋቸዉ ሱና ነዉ ምክኒያቱም ነቢዩ ﷺ ጅብሪል መጣና ባልደረባዋቼን በተልቢያና በላኢላህ ኢለሏህ ድምፃቸዉን ከፍ ማድረግ እንዳለባቸዉ እዘዛቸዉ በማለት አዘዘኝ ብለዋል (አምስቱ ዘግበዉታል)

ሴት ግን በተልቢያም ሆነ በተለያዩ ዚክሮች ድምፅ ከፍ ማድረግ የለባትም ከሷ የሚፈለገዉ ድምፃን መቀነስ ስለሆነ ።።

ወደ ሐጅ ሥርዓት ከገባ በኋላ በሆነ ችግር ምክኒያት በበሽታ ወይም በሌላ ነገር ኢህራሜን እፈታ ይሆናል የሚል ስጋት ከገባዉ የምፈታዉ ባገድከኝ ቦታ ላይ ነዉ በማለት ቅድመ ሑኔታ ማስቀመጥ ሱና ነዉ ነገር ግን ፍርሃት የሌለበት ሰዉ ይህን

መስፈርት ማስቀመጥ የለበትም ሙህሪም ሰዉ ተልቢያ (ለብበይክ አልላሁምመ ለብበይክ የሚለዉን) ማብዛት አለበት በተለይም ሁኔታዎች እና ጊዜዎች በሚፈራረቁበት (በሚቀያየሩበት) ጊዜ ለምሳሌ፡- ከፍተኛ ቦታ ሲወጣ ዝቅተኛ ቦታ ሲወርድ ፣ ሌሊትና ቀን ሲፈራረቁ ፣ ክልክል የሆነን ነገር በአዕምሮዉ ባስበጊዜ ዑምራ ከሆነ ኢህራም ካደረገ ጀምሮ ከዕባን መዞር እስከሚጀምር ድረስ ተልቢያን ማቋረጥ የለበትም ሐጅ ከሆነ ግን ኢህራም ካደረገ ጀምሮ የዒድ ቀን ጠጠር እስከ ሚወረዉር ድረስ ተልቢያን ማዘዉተር አለበት መካ ከተማ በሚቀርብ ጊዜ የሚመቸዉ ከሆነ ገላዉን መታጠብ ሱና ነዉ ነቢዩ ﷺ መካ መግባት ሲያስቡ ይታጠቡ ነበር፡፡

ከተከበረዉ መስጊድ ሲደርስ ለመግባት ቀኝ እግሩን ያስቀድም ከዚያ (ቢስሚልላሂ ወስሶላቱ ወስሰላሙ አላ ረሱሊላሂ አልሏሁምመ ኢግፊር ሊ ዙኑቢ ወፍተህ ሊ አብዋበ ረህመቲከ አኡዙ ቢልሏሂ ልአዚም ወቢወጅሂሂ ልከሪም ወሱልጧኒሂ ልቀዲም ሚነ ሸሸይጧኒ ርረጂም) የሚለዉን ያንብብ ::

ትርጉም፡- በአላህ ስም (እገባለሁ)የአላህ እዝነትና ሰላም በመለዕከተኛዉ ላይ ይዉረድ ጌታየ ሆይ ለወንጀሌ ምህረትህን ለግስልኝ የዝነትህን በር ክፈትልኝ ታላቅ በሆነዉ በአላህ ፣ በተከበረዉ ፊቱ እና መጀመሪያ የሌለዉ በሆነዉ ስልጣኑ ከአላህ እዝነት ከተባረረዉ ሰይጣን እጠበቃለሁ ማለት ነዉ፡፡ አላህን

በመፍራትና ለአላህ ክብር የሰጠ ሆኖ ይግባ የተከበረ ወደሆነዉ ቤቱም (በይቱላህ) እንዲደርስ ነገሮችን ሁሉ በማግራት አላህ የለገሰለትን ፀጋ ያስታዉስ ከዚያም ቤቱን ለመዞር እንዲጀምር ሀጀረል አስወድ ባለበት አቅጣጫ ወደሀረሙ ይግባ ድምፁን ከፍ በማድረግ ነወይቱ አጥጦዋፍ ማለት አይቻልም (ቢድዓ ነዉ) ከነቢዩ ﷺ አልተገኘም ኒያ ቦታው ልብ እንጅ ምላስ አይደለም ::

ከዚያም ሀጀረል አስወድን በቀኝ እጁ ይንካዉ የሚችል ከሆነም ይሳመዉ ይህን ሲያደርግ ግን ለአላህ (ሱ.ወ) ክብር እና የነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ)አርአያነት ለመከተል እንጅ ይህ ድንጋይ ይጠቅማል ይጎዳል የሚል እምነት መኖር የለበትም ለምን ቢባል ጥቅምና ጉዳት የአላህ ብቻ ስለሆነ:: ዑመር ኢብኑ ኸጣብ ስራቸውን ይውደድላቸውና ድንጋዩን በሚስሙት ጊዜ እኔ አንተ መጥቀምም መጉዳትም የማትችል ድንጋይ መሆንህን አዉቃለሁ ነቢዩ(ሶ.ዐ.ወ)ሲስሙህ ባላያቸዉ ኖሮ አልስምህም ይሉ ነበር::

መሳም ካልቻለ ድንጋዩን በጁ በመንካት እጁን ይሳም አብደላ ኢብኑ ኡመር ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዳወሱት ድንጋዩን በጁ ነካ ከዚያም እጁን ሳመ ይህን ነገር ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ)ሲሰሩት ካየሁ ጀምሬ ትቼዉ አላዉቅም ብሏል (ቡኻሪና ሙስሊም

የዘገቡት) በጁ መንካት ካልቻለ ከሰዎች ጋር መጋፋት የለበትም መጋፋት ለራሱ ተቸግሮ በሌሎችም ላይ ችግርን መፍጠር ስለሆነ ፡ ፡ ጉዳት እንዲሁም ጥቅም የሌለዉ ነገር ፤ ክርክር እና መገዳደል ሊከሰትም ይችላል በሩቅ ቦታ ላይ እንኳ ቢሆን በጁ ማመላከት በቂ ነዉ ኢብኑ አብባስ ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዳወሱት ነበዩ (ሶ.ዐ.ወ) ግመል ላይ ሆነዉ ቤቱን ዞሩ ሀጀረል አስወድ አለበት አካባቢ ሲደርሱ በያዙት ነገር ወደ ሀጀረል አስወዱ በማመላከት አላሁ አክበር አሉ ብሏል፡፡ (ቡኻሪ የዘገቡት)

ከዚያም የቀኝ አቅጣጫዉን በመያዝ ከዕባን በግራ አቅጣጫ በማድረግ (ከዕባዉን ይዙር) ሩክነል የማኒ ሲደርስ ከቻለ በጁ ይንካዉ ግን መሳም አይቻልም መንካት ካልቻለ መጋፋት የለበትም (ሩክነል የማኒ ማለት ሀጀረል አስወድ ካለበት ማዕዘን በኋላ ሶስተኛዉ ማዕዘን ነዉ)

ከዕባዉን በሙሉ ከሐጀረል አስወዱና ከሩክነል የማኒ ዉጭ ማንኛዉንም በጅ መንካት አይፈቀድም በሀጀረል አስወድና በሩክነል የማኒ መካከል በደረሰ ቁጥር (ረብበና አቲና ፊዱንያ ሀሰነተን ወፊል አኺረቲ ሀሰነተን ወቂና አዛበንናር)የሚለዉን ያንብቡ፡፡

ትርጉም ፡- ጌታችን ሆይ በቅርቢቱ ዓለም መልካም ነገርን በመጨረሻይቱም ዓለም መልካም ነገርን ለግሰን ከእሳት ቅጣትም ጠብቀን ማለት ነዉ፡፡ በሀጀረል አስወድ አጠገብ ባለፈ ቁጥር መጀመሪያ ሲጀምር የሰራዉን ሁሉ መስራት አለበት አላሁ አክበርም ይበል ቤቱን በሚዞርበት ጊዜ ካለፉት ቦታዎች ዉጭ ላሉት ቦታዎች ከሆነ አላህን በማዉሳት ወይም እርሱን በመማፀን አልያም ቁርአንን ማንበብ ይችላል፡፡

ወንድ ለመጀመሪያ ጊዜ ጦዋፍ ሲያደርግ መዞር ከጀመረ ጀምሮ ጦዋፉን እስከሚጨረስ (እስከሚያጠናቅቅ) ድረስ ኢድጢባዕ መጠቀም እና ከመጀመሪያዎቹ ሶስቱ ጦዋፎች(ዙሮች) ላይ ከመጨረሻዎቹ አራቶቹ ላይ ሳይሆን ረመል መጠቀም ሱና ነዉ

* ኢድጢባዕ ማለት ቀኝ ትካሻዉን ግልፅ ማድረግ ነዉ ጋቢዉን ከቀኝ ብብቱ ስር በማድረግ የጋቢዉን ሁለት ጫፎች ግራ ትካሻዉ ላይ ማድረግ

* ረመል ማለት እርምጃዎችን በማቀራረብ ፈጠን ብሎ መሄድ ማለት ነዉ ቤቱ የሚዞረዉ ሰባት ጊዜ ነዉ ከሀጀረል አስወዱ ጀምሮ በሀጀረል አስወድ ይጨርስ በሂጅሩ ዉስጥ ጦዋፍ ማድረግ አይቻልም

ስባት ጊዜ ዙሮ ከጨረሰ በኃላ ወደ መቃሙ ኢብራሂም በመሄድ ይኸን የቁርዓን አንቀፅ ያንብብ (ወትተኺዙ ሚን መቃሚ ኢብራሂመ ሙስሶላ

﴿وَعَهِدۡنَآ إِلَىٰٓ إِبۡرَٰهِـۧمَ وَإِسۡمَٰعِيلَ أَن طَهِّرَا بَيۡتِيَ لِلطَّآئِفِينَ وَٱلۡعَٰكِفِينَ وَٱلرُّكَّعِ ٱلسُّجُودِ﴾ البقرة ١٢٥

(ወአሂድና ኢላ ኢብራሂመ ወኢስማኢለ አንጠህሂራ በይቲየ ሊጥዒፊነ ወልኣኪፊነ ወርኩከኢ ስኩጁድ) (አልበቀራ 125)

ትርጉም ፡- ‹‹የኢብራሂምን መቆሚያ መስገጃ አድርጉ (በማለት ሰዎችን አዘዝን)፡፡ ወደ ኢብራሂምና (ልጃቸዉ) ኢስማዔልም ለጎብኚዎች ፤ ለተቀማጮች ፤ ለሩኩዕና ሱጁድ አድራጊዎችም ቤቱን አፅዱ የሚል ትዕዛዝ አስተላለፍን፡፡›› ከቻለ ከኢብራሂም መቆሚያ (መቃሙ ኢብራሂም) ቀረብ ብሎ ከጀርባዉ ሁለት ረከዓ ይስገድ፡፡ ካልቻለ ግን ራቅ ብሎ ይስገድ ከፋቲሃ በኃላ ከመጀመሪያዉ ረከዓ ላይ ሱረቱል ካፊሩን ያንብብ ሁለተኛዉ ረከዓ ላይ ሱረቱል ኢኽላስን ያንብብ፡፡ ከሰገደ በኃላ ወደ ሀጀረል አስወድ በመሄድ ከቻለ በጁ ይንካዉ፡፡ ግን በጁ መንካት ካልቻለ በጁም ሆነ በሌላ ነገር ማመላከት የለበትም፡፡

ከዚህ በኃላ ወደ ሶፋ (አልመስዓ ያምራ) ይዉጣ ከሶፋ ኮረብታ በሚቀርብ ጊዜ ይህን የቁርዓን አንቀፅ ያንብብ፡፡

﴿۞إِنَّ ٱلصَّفَا وَٱلۡمَرۡوَةَ مِن شَعَآئِرِ ٱللَّهِۖ فَمَنۡ حَجَّ ٱلۡبَيۡتَ أَوِ ٱعۡتَمَرَ فَلَا جُنَاحَ عَلَيۡهِ أَن يَطَّوَّفَ بِهِمَاۚ وَمَن تَطَوَّعَ خَيۡرٗا فَإِنَّ ٱللَّهَ شَاكِرٌ عَلِيمٌ﴾ البقرة ١٥٨

(ኢንነ ስሶፋ ወልመርወተ ሚን ሸዓኢሪ ልላሂ ፈመን ሀጅጀ ልበይተ አዊ እተመረ ፈላ ጁናህ አለይሂ አን የጥወፈ ቢሂማ ወመን ተጦውወአ ኸይረን ፈኢንነ ልሏህ ሻኪሩን አሊም) (አልበቀራ 158)

ትርጉም፡- ሶፋና መርዋ ከአላህ (ትእዛዝ መፈፀሚያ)ምልክቶች መካከል (ሁለቱ) ናቸዉ፡፡ በሐጅ ወይም በዑምራህ ጊዜ (የአላህን)ቤት የነበኘ ሰዉ በሁለቱ (መካከል)በመመላለሱ በርሱ ላይ ኃጢአት የለበትም ፡፡ (በግዴታነት ያልፀናበትን)መልካም ስራ በፈቃደኝነት የሰራም (ከአላህ ዘንድ ተገቢዉን ምንዳ ያገኛል)፡፡ አላህ (ለባሮቹ መልካም ስራ)ዕዉቅና ሰጭ (የሚፈፅሟቸዉን ፅድቅ ተግባራትም) ዐዋቂ ነዉ፡፡ ይህን የቁርዓን አንቀፅ እዚህ ቦታ ላይ (ሶፋ ኮረብታ በሚቀርብ ጊዜ ብቻ) እንጅ ሌላ ቦታ ላይ ማንበብ የለበትም፡፡ ከዚያ ሶፋ ኮረብታ ላይ ይዉጣ ከዕባን ማየት እስከሚችል ድረስ ወደ ከዕባ ይዙር እጆቹን ከፍ በማድረግ አላህን ያመስግን ከዚያም ማድረግ በሚፈልገዉ ዱዓ አላህ (ሱ.ወ) ይጠይቅ ነቢዩ ﷺ እዚህ ቦታ ላይ ከሚያደርጓቸዉ ዱዓዎች ይህ ዱዓ አንዱ ነበር (ላኢላህ ኢልለ ልሏህ ወህደሁ

ላሸሪከ ለሁ ለሁ ልሙልኩ ወለሁ ልሀምድ ወሁወ አላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲር ላኢላህ ኢልለ ልሏሁ ወህደሁ አንጀዘ ወዕደሁ ወነሶረ አብደሁ ወሀዘመል አህዛበ ወህደህ) ሶስት ጊዜ ይደጋግመዉ በዚህ መካከልም የተለያዩ ዱዓዎችን ያድርግ፡፡

ትርጉም ፡- ከአላህ በስተቀር በዕዉነት የሚመለክ አምላክ የለም እሱ ብቸኛ ነዉ ለርሱ ተጋሪ የለዉም ንግስና ለርሱ ብቻ ነዉ ምስጋናም የርሱ ነዉ እርሱ በነገሩ ላይ ሁሉ ቻይ ነዉ ከአላህ በስተቀር በእዉነት የሚመለክ አምላክ የለም እሱ ብቸኛ ነዉ ቃል ኪዳኑን ፈፀመ አገልጋዩን (ሙሀመድን)ረዳ የተሰበሰበዉን የጠላት ጦር ለብቻዉ ድል ነሳ(በታተነ)

ከዚያ ከሶፋ ኮረብታ ወደ መርዋ በዝግታ ይዉረድ አረንጓዴ ቀለም የተቀባ የግድግዳዉ ምሰሶ አጠገብ እስከሚደርስ ድረስ ከደረሰ በኋላ በሚችለዉ መጠን (መንገዱ ክፍት ከሆነ) ሰዎችን ሳያስቸግር በደንብ(በፍጥነት) ይሩጥ እሁለተኛዉ አረንጓዴ ቀለም የተቀባ የግድግዳዉ ምሰሶ አጠገብ እስከሚደርስ ድረስ ከዚህ በኋላ እሩጫዉን በመተዉ በእርምጃ ብቻ ጉዞዉን ወደ መርዋ ይቀጥል መርዋ ላይ በመዉጣት ፊቱን ወደ ከዕባ በማዞር እጆቹን ከፍ በማድረግ ሶፋ ላይ የሰራዉን በሙሉ ይስራ (ሶፋ ላይ ያደረገዉን ዱዓ በሙሉ መርዋ ላይ ይድገመዉ) ከመርዋ ወደ ሶፋ በእርምጃ መሄድ አለበት ቦታ ላይ በእርምጃ በመሄድ መሮጥ አለበት ቦታ ላይ በመሮጥ ይዉረድ ከዚያም ሶፋ ላይ

ይዉጣ ፊቱን ወደ ከዕባ በማዞር እጆቹን ከፍ በማድረግ መጀመሪያ ላይ ሲጀምር የሰራዉን በሙሉ ይስራ (በሶፋና በመርዋ መካከል) ሲንቀሳቀስ የፈለገዉን የቻለዉን ዚክር ዱዓ ከፈለገ ቁርዓን መቅራት ይችላል ሶፋና መርዋ ላይ መዉጣት በሁለቱ አረንጓዴ ቀለሞች መካከል መሮጥ ሱንና እንጂ ግዴታ አይደለም፡፡ መሮጥ ወንዶችን እንጂ ሴቶችን አይመለከትም፡፡ በእንዲህ አይነት መልኩ ሰባት ጊዜ በሁለቱ ኮረብታዎች መካከል ምልልስ በማድረግ ከጨረሰ በኋላ (ልብ ይበሉ! ከሶፋ አንስቶ እስከ መርዋ ድረስ ያደረገዉ ጉዞ (ሰዕይ) አንድ ዙር ነዉ እንዲሁም ከመርዋ እስከ ሶፋ ያለዉ ጉዞ ደግሞ ሁለተኛ ዙር መሆኑን አይርሱ)!!

* ወንድ ከሆነ የራስ ፀጉሩን ይላጭ ወይም ያሳጥር መላጨት በደረጃ ይበልጣል ምናልባት ያደረገዉ ዑምራ የተመቱዕ ዑምራ ከሆነ የሐጅ ጊዜዉ ከቀረበ ፀጉሩ በማይበቅልበት ሁኔታ ከመላጨት ማሳጠሩ ይሻላል ለምን ቢባል በሐጅ ጊዜ ስትፈታ መላጨቱ በላጭ ስለሚሆን

* ሴት ግን በማንኛዉም ሁኔታ ማሳጠር ነዉ ያለባት አትላጭም ከእያንዳንዱ ጉንጉን ላይ የጣትዋን የላይኛዉን ክፍል (የጥፍሯን)ያህል መቁረጥ ይኖርባታል (እንጂ ሙሉ ፀጉሯን አትላጭም)

ወንዶች ሲላጩ ፀጉራቸዉን በሙሉ መላጨት ግደታ ይሆንባቸዋል አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል :- (ራሳችሁን ላጭታችሁ) (አል-ፈትህ .27 ነቢዩ ﷺ ፀጉራቸዉን በሙሉ ነዉ የላጩት የሐጃችሁንና የዑምራችሁን አሰራር ከኔ ተማሩ በማለትም ተናግረዋል የሚያሳጥረዉም በሚያሳጥርበት (ጊዜ) ፀጉሩን በሙሉ ነዉ ማሳጠር ያለበት እንጂ (የተወሰነ ፀጉር ብቻ ማሳጠር አይቻልም)

እነኝህን ስራዎች በመስራት የዑምራ ስራ ይጠናቀቃል ሙሉ በሙሉ ከዑምራ ይፈታል ኢህራም ካደረገ በኋላ የተከለከላቸዉ ነገሮች ሁሉ በሙሉ ይፈቀዱለታል።።

የውምራ አፈፃፀም ስርዓቱ ጠቅለል ባለ መልኩ

1. ገላን መታጠብ ሽቶ መቀባት

2. የኢህራምን ልብስ መልበስ ሽርጥና ፎጣ ለወንድ ኢስላም የሚፈቅደዉ ከሆነ ማንኛዉም ልብስ መልበስ ለሴት

3.ተልቢያን ከዕባን መዞር እስከሚጀምር ድረስ ማቆየት

4. መጀመሪያዉም መጨረሻዉም ሐጀረል አስወድ ከመሆኑ ጋር ከዕባን ሰባት ጊዜ መዞር

5. ከኢብራሂም መቆሚያ ጀርባ ሁለት ረከዓዎች መስገድ

6. መጀመሪያዉ ሶፉ ሲሆን መጨረሻዉ ደግሞ መርዋ ሰባት ዙር መዞር

7. ፀጉር መላጨት ወይም ማሳጠር ለወንዶች ማሳጠር ብቻ ለሴቶች ።።

የሐጅ ሥርዓተ-አምልኮ አፈፃፀም

ለሐጅ ኢህራም ማድረግ(የዉሙተርዊያ) ዙልሂጃ ስምንተኛዉ ቀን ረፋድ ላይ ሐጅ ማድረግ የፈለገ ለሐጅ ካለበት ስፍራ ሆኖ ኢህራም ያድርግ ኢህራም ለማድረግ ወደ ከዕባም ሆነ ወደሌላ መስጊዶች ዘንድ መሄድ ሱና አይደለም ፡፡ ይህ ከመልዕክተኛዉም ሆነ ከሶሃቦች አልተገኘም ለሐጅ ኢህራም በሚያደርግ ጊዜ ለዑምራ ኢህራም ሲያደርግ የተጠቀመዉን በሙሉ ይጠቀም ገላዉን ይታጠብ ሽቶ ይቀባ ከዉዱእ በኃላ ሁለት ረከዓ ይስገድ ከዚያም ሐጅን በመነየት ድምፁን ከፍ ያድርግ ሐጅ ላይ ተልቢያና ኢህላል ስርዓታቸዉ ከዑምራ ጋር ተመሳሳይ ነዉ ነገር ግን ሐጅ ላይ ለብበይከ ሐጀን ነዉ ማለት ያለበት ትርጉም ፡-ለሐጅ ሥራ ብቻ አቤት ብያለሁ ማለት ነዉ፡፡ ወደ ሐጅ ሥርዓት ከገባ በኃላ በሆነ ችግር ምክኒያት ኢህራሜን እፈታ ይሆናል የሚል ስጋት ከገባዉ የምፈታዉ ባገድከኝ ቦታ ላይ ነዉ በማለት ቅድመ ሑኔታ ማስቀመጥ(ሱና) ነዉ ነገር ግን ፍርሃት የሌለበት ሰዉ ይህን መስፈርት ማስቀመጥ የለበትም

<u>ሚና መሄድ</u>

ከዚያም ሚና በመሄድ ዙህር ፣ ዐስር ፣ መግሪብ ፣ ኢሻና ፈጅርን (መግሪብ ሲቀር) በማሳጠር (ሁለት ሁለት ረከዓ በማድረግ) ሶላቶችን በሙሉ ጊዜያቸዉን በመጠበቅ ብቻ ብቻቸዉን በመለየት ይስገድ አብደላ ኢብኑ ኡመር ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዳወሱት ነቢዩ ﷺ እንዲሁም አቡበክር ኡመር ኡስማንም ቢሆኑ ለሙስሊሞች መሪ እንደሆኑ መጀመሪያ አካባቢ ላይ ሚና ሁለት ረከዓ ሰግደዋል ነቢዩ ﷺ ዙህርን ከዐሱር እንዲሁም መግሪብን ከዒሻ ጋር ሚና ላይ አያጣምሩም ነበር ። (ቡኻሪ የዘገቡት)

<u>ዐረፋ ላይ መቆየት(መገኘት)</u>

ዘጠነኛዉ ቀን ላይ ፀሀይ ከወጣች በኃላ ከሚና ወደ ዐረፋ ይጓዝ ከቻለ የዙሁር ወቅት እስኪገባ ድረስ ነሚራ ተብሎ የሚጠራዉ ስፍራ (በአሁኑ ወቅት መስጊድ ተሰርቶበታል) ላይ መቆየት ሱና ነዉ ካልቻለ ችግር የለበትም እዚህ ቦታ ላይ መቆየት ሱና እንጅ ግዴታ አይደለም የዙሁር ወቅት ሲገባ ዙህርን ና ዐስርን አንድ ላይ(ተቅዲም) በማድረግ ሁለት ሁለት ረከዓ ብቻ ይስገድ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ)ያደርጉት የነበረዉ ይህ ነዉ።

እንደ ሙስሊም ዘገባ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ዐረፋ እስከሚደርሱ ተጓዙ ነሚራ በመባል እሚታወቀዉ ቦታ ላይ ድንኳን ተዘጋጅቶላቸዉ አገኙ ከዚያም አረፉ ፀሃይ ወደ መጥለቂያዋ አቅጣጫ ወረድ ስትል ቀስዋእ የምትባለዉን ግመላቸዉን እንድትዘጋጅላቸዉ አዘዙ በጥነል ዋዲ እሚባለዉ ቦታ ላይ መጡ ዉጥባ አደረጉ ከዚያም አዛንና ኢቃም አደረጉ ዙህርን ሰገዱ ከዚያም ኢቃም አደረጉ ዐስርን ሰገዱ በመካከላቸዉ ምንም የሰገዱት ነገር የለም ከዚያም ግመላቸዉ ላይ ወጡና ወደ መቆሚያዉ ስፍራ መጡ ወደ ከፅባ በመዞር ፀሃይ እስከምትጠልቅ ድረስ እዚህ ቦታ ላይ የቆሙ(የቆዩ) ከመሆን አልተወገዱም። ሐጅ ለሚያደርግ ሰዉ የዐረፋ ቀን ከቀኑ መጨረሻ ላይ ለዱዓ ለዚክርና ቁርዓን ለመቅራት ሀሳቡን ለነዚህ ብቻ በማድረግ (እነኝህን መጠቀሙ) ሱና ነዉ ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) የተገኙ የሆኑን አዝካሮችና ዱዓዎች ይጠቀም ።

ለቻለ ዐረፋ ላይ ነቢዩ ﷺ እቆሙበት ቋጥኞቹ አካባቢ ቢቆም የተሻለ ነዉ ካልቻለ ግን አረፋ ይሁን እንጅ ማንኛዉም ቦታ ላይ መቆም (መቆየት) ይችላል።ጃቢር ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዳወሱት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እዚህ ቦታ ላይ አርጃለሁ ሚና እሁሉም ቦታ ላይ ማረድ ይቻላል በያላችሁበት እረዱ እዚህ ቦታ ላይ

ቆምኩኝ አረፋ በሙሉ መቆሚያ ነዉ እዚህ ቦታ ላይ ቆምኩኝ (ጀምዕ) ሙዝደሊፋ በሙሉ መቆሚያ ነዉ ።። (የሙስሊም ዘገባ)

ዐረፋ ላይ የቆመ ሰዉ የዐረፋን ክልል በትክክል ማወቅ ግደታ ይሆንበታል የዐረፋን ክልል የሚገልፁ የፈለገ ሰዉ የሚያገኛቸዉ የሆኑ ብዙ ምልክቶች አሉ ነገር ግን ብዙ ሰዎች በዚህ ነገር ላይ ችላ ሲሉ ይታያሉ ባለማወቅና ሌሎች ሰዎችን በመከተልም ከዐረፋ ክልል ዉጭ ይቆማሉ እነዚህ ሰዎች ከዐረፋ ክልል ዉጭ የሚቆሙት ሐጅ ማለት ዐረፋ ላይ መቆም ስለሆነ ሐጃቸዉ ትክክል አይደለም

አብዱ ረህማን ኢብኑ የዕመር ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዳስተላለፉት ነቢዩ ﷺ ዐረፋ ላይ በቆሙ ጊዜ ከሳቸዉ ጋር ነበርኩኝ ነጅድ ከሚባለዉ አካባቢ ሰዎች መጡ ሐጅ ማለት ምንድን ነዉ በማለት ለአላህ መልዕክተኛ ጥያቄ አቀረቡ የአላህ መልዕክተኛም ﷺ ሐጅ ማለት አረፋ ላይ መቆም ነዉ የሙዝደሊፋ ሌሊት ከፈጅር ሶላት በፊት አረፋ ላይ የቆመ ሐጁ ትክክል ነዉ የሚና ቀኖች ሶስት ናቸዉ ሁለት ቀን ሚና ላይ ቆይታ ካደረገ በኃላ የቸኮለ ካለ ወንጀል የለበትም የሚቆይም እንደዚሁ ወንጀል የለበትም አንድን ሰዉ ከኃላቸዉ (እግመላቸዉ ላይ) በማድረግ እነኝህን መልዕክቶች ለህዝቦች እንዲያስተላልፍ አደረጉ ።።

ዐረፋ ላይ ቀን የቆመ ፀሀይ እስከምትገባ መቆየት ግዴታ ይሆንበታል ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ፀሀይ እስከምትገባ ቆይታ ስላደረጉ እሳቸዉም የሐጅን ስራ ከኔ ያዙ ብለዋል ። ፀሀይ ከመግባቷ በፊት ወደ ሙዝደሊፋ መመለስ በድንቁርና ዘመን የነበሩ ሰዎች (ከኢስላም በፊት የነበሩ ሰዎች) ስራ ስለሆነ ኢስላም ደግሞ ጃሂሊያዎችን እንድንፃረር አዞናል ።ዐረፋ ላይ መቆም የሚድ ቀን ፈጅር (ጎህ) እስከሚወጣ ድረስ ይቆያል ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) (ሰዎች)ሙዝደሊፋ በሚያድሩበት ሌሊት ፈጅር ከመዉጣቱ በፊት አረፋ ላይ የቆመ በእርግጥም (አረፋ ላይ መቆምን) አግኝቷል ብለዋል ።

ግን አረፋ ላይ ሳይቆም የሚድ ቀን ፈጅር የወጣበት ሰዉ በእርግጥም ሐጅ አምልጦታል ።

ወደ ሐጅ ሥርዓት ከገባ በኋላ በሆነ ችግር ምክኒያት ኢህራሜን እፈታ ይሆናል የሚል ስጋት ከገባዉ የምፈታዉ ባገድከኝ ቦታ ላይ ነዉ በማለት ቅድመ ሑኔታ አስቀምጦ ከሆነ ከኢህራሙ ይፈታ ምንም ነገር የለበትም ግን መጀመሪያ መስፈርት ካላስቀመጠ በዑምራ ይፈታ ከዕባ ይሂድ ቤቱን ይዙር በሶፋና በመርዋ መካከል ምልልስ ያድርግ ፀጉሩን ይላጭ እሚታረድ ይዞ ከሆነ ይረድ በሚቀጥለዉ ዓመት ይህን ያመለጠዉን ሐጅ ቀዷ

ያዉጣ ማረድም አለበት ካላገኘ አስር ቀን ይፁም ሶስት ቀን ሐጅ ላይ ሰባት ቀን ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ።።

ኢማሙ ማሊክ ሙወጥጦዕ ላይ የዘገቡት ሀዲስ ዑመር ኢብኑ ኸጧብ ስራቸውን ይውደድላቸውና አቡ አዩብ እና ሐብባር ኢብኑ ልአስወድ ሐጅ አምልጧቸው አስረኛዉ ቀን ላይ በመጡ ጊዜ በዑምራ እንዲፈቱ የተፈቱ ሁነዉ እንዲመለሱ በሚቀጥለዉ ዓመት ሐጅ እንዲሰሩ ና ማረድ እንደሚኖርባቸዉ ያላገኘ ሐጅ ላይ ሶስት ቀን እንዲፆም እቤተሰቦቹ ዘንድ ሲመለስ ሰባት ቀን እንዲፆም አዘዋቸዋል።።

<u>ሙዝደሊፋ ላይ ማደር</u>

ፀሐይ ከገባች በኋላ ከዐረፋ ወደ ሙዝደሊፋ ጉዞዉን ይቀጥል መግሪብ እና ኢሻን (አጣምሮ) ይስገድ መግሪብን ሶስት ኢሻ ሁለት ረከዓ በማድረግ ይስገድ ሐጅ ላይ ለሆነ ሰዉ ሱናዉ መግሪብና ኢሻን መስገድ ያለበት ሙዝደሊፋ ላይ ነዉ ነቢዩን ﷺ ለመከተል

ሌሊቱ ግማሽ ስለሆነ ኢሻ ያመልጠኛል ብሎ ከፈራ የኢሻ ወቅቱ ሳይወጣ ማንኛዉም ስፍራ ይሁን ኢሻን መስገድ ግደታ ይሆንበታል ሙዝደሊፋ ላይ ይደር (ሱናዉ መተኛትነዉ)በሶላትም ሆነ በሌላ ነገር ሌሊቱን ማሳለፍ የለበትም ረሱል (ሶ.ዐ.ወ)ይህን አላደረጉምና፡፡

ደካማ የሆኑ ወንዶችና ሴቶች ከሌሊቱ መጨረሻ አካባቢ ላይ ከሙዝደሊፋ ወደ ሚና መሄድ ይፈቀድላቸዋል ፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ አብደላ ኢብኑ ኡመር ስራቸውን ይውደድላቸውና ከቤተሰባቸዉ ደካማ የሆኑትን ቀደም ብለዉ እንዲሄዱ ያደርጉ ነበር ሙዝደሊፋ መሸዓረል ሀራም ላይ በሌሊት ይቆማሉ አላህን (ሱ.ወ) የቻሉትን ያህል ያስታዉሳሉ ከዚያ ይመለሳሉ ከመካከላቸዉ ለሱቢህ ሶላት ሚና ላይ የሚደርስ አለ ከመካከላቸዉም ከፈጅር በኋላ የሚደርስ አለ ሚና እንደደረሱ ጠጠር ይወረዉራሉ አብደላ ኢብኑ ዑመር ስራቸውን ይውደድላቸውና ደካማ ለሆኑ ሰዎች ነቢዩ ﷺ ፈቅደዉላቸዋል ይል ነበር ፡፡ግን ደካማና ከደካማ ጋር የሚጓዝ ካልሆነ ፈጅርን እስከሚሰግድ ድረስ ሙዝደሊፋ ላይ መቆየት አለበት፡፡የፈጅር ሶላት ሰግዶ እንደጨረሰ መሸዐረል ሀራም ይሂድ ወደ ቂብላ ይዙር አላሁ አክበር ላኢላህ ኢለሏህ ይበል በጣም እስከሚነጋ ድረስ ዱዓ እያደረገ ይቆይ መሸዐረል ሀራም መሄድ ካልቻለ አለበት ቦታ ላይ ዱኣ ያድርግ ፡፡

<u>ሚና በመሄድ ሚና ላይ መቀመጥ</u>

ሙዝደሊፋ ላይ የተቀመጡ ሁጃጆች ፀሃይ ከመዉጣቷ በፊት ዚክራቸዉንና ዱዓቸዉን እንደጨረሱ ወደ ሚና ይሂዱ ሚና እንደደረሱ ወደፊት የሚዘረዘሩትን ነገሮች ይስሩ ::

1. ጀምረተል አቀባ ላይ ጠጠር መወርወር ይህ ጀምረተል ኩብራ ይባላል:: ወደ መካ የሚቀርብ ከመሆኑ ጋር የሚገኘዉ ሚና ጫፍ ላይ ነዉ:: ሰባት ጠጠሮችን የተወሰነ ከሸንበራ ከፍታ ያላቸው የሆኑን ይልቀም ከዚያም ወደ ጀምራዉ ጠጠሮችን በመነጣጠል ይወርዉራቸዉ ሲወረዉር ከዕባን በግራዉ ሚናን ደግሞ በቀኙ አቅጣጫ ያድርግ አብደላ ኢብኑ መስዑድ ስራቸውን ይውደድላቸውና የዘገቡት ሀዲስ እሱ ጀምረተል ኩብራ ላይ እንደደረሰ ከዕባን በግራዉ ሚናን ደግሞ በቀኙ አቅጣጫ በማድረግ ሰባት ጊዜ ወረወረ ከዚያም ያ የበቀራ ምዕራፍ የወረደበት የሆነዉ (ነብይ ﷺ) በዚህ መልክ ነዉ የወረወረዉ በማለት ተናግሯል :: (ቡኻሪ ሙስሊም)

ጠጠሮቹን በወረወረ ቁጥር አላሁ አክበር ይበል ::

ትልልቅ ድንጋዎችን እንዲሁም ጫማዎችን ሌሎችንም ነገሮች መወርወር አይፈቀድም ::

አላህን (ሱ.ወ) የፈራና ደረጃዉን ከፍ ያደረገ ሆኖ ይወርዉር ብዙሀን መሃይሞች የሚሰሩትን ስራ መስራት የለበትም መጮህ ፣ ወከባ መፍጠርና መሳደብ የለበትም ።።

2. ጠጠር ከወረወረ በኋላ ሀድይ ይዞ ከሆነ ይረድ ካልያዘ ገዝቶ ማረድ ይችላል።።

3. ሀድዩን ካረደ በኃላ ወንድ ከሆነ ፀጉሩን ይላጭ ወይም ያሳጥር መላጨት ግን በደረጃ ይበልጣል የበለጠበትም ምክንያቱ የአላህ (ሱ.ወ) መልእክተኛ ﷺ ፀጉራቸዉን ለሚላጩ ሰዎች አላህ እዝነቱንና ምህረቱን ይለግስላቸዉ በማለት ሶስት ጊዜ በመደጋገም ዱዓ ሲያደርጉ ለሚያሳጥሩ ሰዎች ግን አንድ ጊዜ ብቻ ነዉ ያደረጉት ግን ሲላጭም ሆነ ሲያሳጥር ሁሉንም ፀጉሩን መሆኑ ግዴታ ነዉ ከፊል ፀጉሩን ላጭቶ ከፊሉን መተዉ በኢስላም ክልክል ነዉ ።።

የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ፀጉራቸዉን በሙሉ ነዉ የላጩት እሳቸዉም የሐጅን አፈፃፀም ስነስርዓት ከኔ ያዙ ብለዋል።። ሴት ግን ከፀጉሯ ጫፍ የጥፍር ያህል ነዉ መቁረጥ ያለባት:: የተዘረዘሩትን በሙሉ ከፈፀመ በኢህራም ምክንያት ክልክል

የሆኑ ነገሮች ከሚስት ጋር መገናኘት ሲቀር በሙሉ ይፈቀዱለታል ፡ ፡ እንደተፈታ ሽቶ መጠቀሙ ሱና ነዉ አኢሻ ስራዋን አላህ ይውደድላትና ለአላህ መልዕክተኛ ﷺ ኢህራም ከማድረጋቸዉ በፊት እና ሲፈቱ ሽቶ እንደምትቀባቸዉ ተናግራለች ፡፡ (ቡኻሪ ሙስሊም)

4. ከዕባን መዞር ጦዋፍ አዚያራ እና ኢፋዷ ይባላል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል ከዚያም (ጥፍርን በመቁረጥ ፣ ፀጉርን በመላጨት...)እድፎቻቸዉን ያስወግዱ ፡፡ ስለቶቻቸዉንም ይሙሉ ፡፡ ጥንታዊዉን ቤትም ይዙሩት (አልንም)፡፡ አኢሻ ስራዋን አላህ ይውደድላትና እንዳወሳችዉ ከመለዕክተኛዉ ﷺ ጋር ሐጅ አደረግን ከዚያም አስረኛዉ ቀን ላይ (ወደ ከዕባ) ተመለስን (ቡኻሪ ሙስሊም) ሙተመቲዕ ከሆነ ከዕባን ከዞረ በኋላ ሶፋና መርዋ ይሂድ የመጀመሪያዉ ሰዕይ ለዑምራ ስለሆነ፡፡ አሁን ለሐጅ ሶፋና መርዋ በመሄድ መመላለስ ግዴታ ይሆንበታል፡፡

እንደ ሙስሊም ዘገባ አሚሻ(ረዲየ ላሁ አንሃ) ያንድን ሰዉ ሐጁንም ሆነ ዑምራዉን በሶፋና በመርዋ መካከል ጉበኝት እስካላደረገ ድረስ አላህ አያሟላለትም ብላለች።

ሙፍሪድ ወይም ቃሪን ከሆነ ከቁዱም (ከመግቢያ) ጠዋፍ በኋላ ሶፋና መርዋ ሂዶ ከሆነ ሁለተኛ ሶፋና መርዋ መሄድ የለበትም ጀቢር ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዳወሱት የአላህ መልዕክተኛም ሆኑ ባልደረቦቻቸዉ በሶፋና በመርዋ መካከል አንድ ጊዜ ብቻ እንጅ ምልልስ አላደረጉም ማለት መጀመሪያ ላይ ብቻ ነዉ ምልልስ ያደረጉት። (ሙስሊም የዘገቡትሐዲስ) ግን መጀመሪያ ላይ ሶፋና መርዋ ካልሄደ አሁን መሄድ ግደታ ይሆንበታል ይህን ካላደረገ ሐጁ ሙሉ ሊሆን አይችልም።

ጠዋፈል ኢፋዷን ጨርሶ ከኢፋዷ በፊትም ይሁን በኋላ ሙፍሪድም ይሁን ቃሪን ሰዕይ ካደረገ ሁለተኛን ፍች ይፈታል (ክልክል የነበሩ ነገሮች በሙሉ ይፈቀዱለታል)። አብደላ ኢብኑ ዑመር ስራቸውን ይውደድላቸውና የአላህ መልዕክተኛን (ሶ.ዐ.ወ)የሐጅ አደራረጋቸዉን ሁኔታ እና ባህሪ ሲገልፅ እንድህ

ብሏል:: አስረኛዉ ቀን ላይ አረዱ ወደ ከዕባ በመመለስ ከዕባንም ጎበኙ ተከልክለዉ ከነበረዉ ነገር በሙሉ ተፈቱ ::

እነኝህን ስራዎች የሚድ ቀን ወደፊት እንደ አመጣጣቸዉ ደረጃቸዉን ጠብቆ መስራቱ በደረጃ ይበልጣል

1. ጀምረተል አቀባ ላይ ጠጠር መወርወር

2. ሀድይ ማረድ

3. መላጨት ወይም ማሳጠር

4. ከዕባን መዞር በሶፋና መርዋ መካከል ምልልስ ማድረግ ሙተመቲዕ ከሆነ ሙፍሪድ ወይም ቃሪን ከሆነ ግን(አሁን ሰዕይ ማድረግ ያለበት) ጦዋፈል ቁዱም ላይ በሶፋና በመርዋ መካከል ምልልስ ካላደረገ ነዉ ::

ነቢዩ ﷺ በዚህ መልክ ነዉ ደረጃቸዉን ያስቀመጡት እርሳቸዉም የሐጅ አፈፃፀም ስርዓትን ከኔ ያዙ ብለዋል፡፡ ቅደም ተከተላቸውን ሳይጠብቅ ቢሰራቸዉ ምንም ችግር የለበትም ኢብኑ አብባስ ስራቸውን ይውደድላቸውና የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ስለማረድ ፣ መላጨትና ስለ መወርወር ማስቀደም እና ማዘግየት ተጠይቀዉ ምንም ችግር የለም ሲሉ መልሰዋል ብሏል (ቡኻሪና ሙስሊም)

የሚድ ቀን ከዕባን መዞር ካልቻለ መዘግየት ይችላል ግን አያመተሸሪቅን (አያመተሸሪቅ ማለት ከኢድ ቀን ቀጥለው ያሉ ሶስት ቀናት፤11ኛው 12ኛው እና 13ኛው ቀን) አለማሳለፉ በደረጃ ይበልጣል ችግር ያለበት ሰዉ ሲቀር (ለምሳሌ) ፡- በሽታ ፣ የወር አበባ እና የወሊድ ደምን ይመስል

<u>ሚና ለማደርና ጠጠር ለመወርወር መመለስ</u>

ሐጅ ያደረገ ሰዉ የሚድ ቀን ከጦዋፍ ና ከሰዕይ በኋላ ሚና በመመለስ የሚድ ቀን ቀሪዉን ሰዓት ሚና ላይ ያሳልፍ እንዲሁም የተሸሪቅ ቀኖችን እና ሌሊቶችንም ነቢዩ ﷺ እነኝህን ቀኖችና ሌሊቶች ሚና ላይ ነበር የሚያሳልፏቸዉ ።። አስራአንደኛዉን ቀን /11/፣ አስራ ሁለተኛዉን /12/ እና አስራሶስተኛዉንም /13/ ከዘገየ ሚና ላይ ማደር ግደታ ይሆንበታል በችግር ምክኒያት ሚና ላይ ማደርን መተዉ ይቻላል አብባስ ኢብን አብደል ሙጦሊብ ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዳወሱት ነቢዩን ﷺ እነኝህን ሌሊቶች መካ ለማሳለፍ(ለሁጃጆች) ዉሃ ያጠጣ ስለነበረ ፍቃድ ጠይቋቸዉ ፈቅደዉለታል።። (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ)

በተሸሪቅ ቀኖች እሶስት ቦታዋች (ገንዳዎች) ላይ ጠጠሮችን ይወርዉር ለያንዳንዱ ሰባት ጠጠሮችን በተከታታይ ፀሀይ ከእኩለ ቀን ወደ መጥለቂያዋ ዘንበል ካለች በኋላ አላሁ አክበር በማለት ይወርዉር ።። ከመስጂደል ኸይፍ ቀጥሎ በሚገኘዉ እመጀመሪያዉ ጀምራ (ገንዳ) ላይ ይወርዉር ከዚያ የተወሰነ በመሄድ ወደቂብላ በመዞር ለረጂም ጊዜ በመቆም እጆቹን ከፍ በማድረግ አላህን ይለምን ዱዓ ያድርግ

ከዚህ በኋላ ጀምረተል ዉስጧ ላይ ይወርዉር ከዚያም ግራ አቅጣጫዉን በመያዝ ወደቂብላ በመዞር ለረጂም ጊዜ በመቆም እጆቹን ከፍ በማድረግ ዱዓ ያድርግ ከዚያ ጀምረተል አቀባ ላይ ይወርዉር ከዚህ በኋላ ይመለስ እዚህ ቦታ ላይ ለዱዓ መቆም የለበትም በዚህ መልክ የአላህ (ሱ.ወ) መልዕክተኛ ﷺ

እንደሚሰሩ ኢማሙል ቡኻሪ ዘግበዋል፡፡

በሚወረወርባቸዉ ቦታዋች መካከል ለረጂም ጊዜ መቆም ካልቻለ የቻለዉን ያህል ይቁም፡፡በርካታው ህዝብ የተወዉን ሱና ባለማወቅም ወይም ግምት ባለመስጠት ሊሆን ይችላል ህያዉ ለማድረግ የቻለዉን ያህል ይቁም፡፡ በነኝህ ቀኖች ዉስጥ ከእኩለ ቀን በኋላ እንጅ ጠጠር መወርወር አይቻልም፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ከእኩል ቀን በኋላ እንጅ አልወረወሩም፡፡

አስራሁለተኛዉ ቀን ላይ ጠጠር ከወረወረ የሐጅ ግዴታዎችን በርግጥ ጨረሰ ፡፡ ከዚህ በኋላ ምርጫ አለዉ፡፡ ከፈለገ አስራ ሶስተኛዉን ቀን ሚና ላይ በማሳለፍ ከዕኩለ ቀን በኋላ ጠጠር ይወርዉር ፡፡ ከፈለገ ከሚና ይመለስ (ግን) ሚና ላይ መቆየቱ በደረጃ ይበልጣል ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ)ይሰሩት የነበረዉ ይህ ስለሆነ፡፡ ግን አስራ ሁለተኛዉ ቀን ላይ ከሚና ሳይንቀሳቀስ ፀሀይ ከገባች መቸኮል (ሚናን ለቆ መዉጣት) የለበትም (ይረጋጋ)፡፡ ነገር ግን ፀሀይ እስከምትጠልቅ ድረስ ሚና ላይ የቆየዉ በምርጫዉ

ካልሆነ ለመሄድ ዝግጁ ሆኖ መንገድ በመኪና በመጨናነቅ ምክንያት ቢዘገይ በሌላም ነገር ሊሆን ይችላል ጉዞዉን ይቀጥል ምንም ነገር የለበትም፡፡

<u>ጠጠር ለመወርወር ሌላን ሰዉ መተካት</u>

ሐጅ የሚያደርግ ሰዉ የሚችል ከሆነ ራሱ ጠጠርን መወርወር ግዴታ ይሆንበታል ፡፡ የሚያደርገዉ ሐጅ ትርፍም ይሁን ግዴታ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል (ሀጅንና ዑምራንም ለአላህ ሙሉ) ሐጅና ዑምራ ለማድረግ አንድ ሰዉ ከጀመረ ትርፍ እንኳ ቢሆኑ መጨረስ ግደታ ይሆንበታል፡፡ ማንም ሰዉ ይሁን ጠጠር የሚወረዉርለት ሰዉ መተካት አይችልም በሽተኛ ፣ ትልቅ ሰዉና ህፃን የሆነ በሌላም ምክንያት በራሱ መወርወር ካልቻለ በዲኑና በዕዉቀቱ የሚተማመንበትን ሰዉ ይወረዉርለት ዘንድ መተካት ይችላል፡፡

የተወከለዉ ሰዉ መጀመሪያ ለራሱ ሰባት ጠጠሮችን መወርወር አለበት ከዚህ በኋላ ላወከለዉ ሰዉ ኒያ በማድረግ (ሁለተኛ)ይወርዉር ለራሱና ላወከለዉ ሰዉ አንድ ቦታ ላይ በተከታታይ ቢወረዉር ችግር የለዉም ለራሱ እሶስቱም ገንዳዎች ላይ ወርዉሮ ከጨረሰ በኋላ እንደገና ወደኋላ በመመለስ ላወከለዉ ሰዉ መወርወር ግዴታ አይሆንበትም ግዴታ መሆኑን የሚጠቁም መረጃ ስላልተገኘ ፡፡

የመሰናበቻ ጦዋፍ

ሐጅ ያደረገ ሰዉ ከሚና ከተመለሰ በኋላ ወደ ሀገሩ መመለስ ከፈለገ የመሰናበቻ ጦዋፍ ሰባት ጊዜ ከዕባን ሳይዞር መዉጣት የለበትም ይህ ጦዋፍ መካ ዉስጥ ከሚሰራቸዉ ስራዎች የመጨረሻ ስራ መሆኑ ግዴታ ነዉ ከዚህ በኋላ መካ ላይ ከጉዞዉ ጋር የተሳሰሩ በሆኑ ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር መቆየት አይቻልም ጓደኞቹን ወይም መኪና መጠበቅን ይመስል ከዚህ ዉጭ ለሆነ ጉዳይ ከቆየ ግን ሁለተኛ ጦዋፍ ማድረግ ግዴታ ይሆንበታል የመሰናበቻ ጦዋፍ የወር አበባና የወሊድ ደም በሚያዩ ሴቶች ላይ ግደታ አይደለም ::

የሐጅ አፈፃፀም ጠቅለል ባለ መልኩ

<u>የመጀመሪያዉ ቀን ማለት ሐጃጅ ስምንተኛዉ ቀን ላይ መስራት ያለበት</u>

1. ገላዉን ይታጠብ ሽቶ ይቀባ የኢህራም ልብስ ይልበስ ካለበት ቦታ ላይ ለሐጅ ኢህራም ያድርግ ከዚያም ይበል ፡- (ለብበይክ አልላሁምመ ለብበይክ ለብበይክ ላሸሪከ ለክ ለብበይክ ኢንነል ሀምደ ወንኒዕመተ ለክ ወልሙልክ ላሸሪከ ለክ)

ትርጉም ፡- (ጌታዬ ደግሜ ደጋግሜ ለጥሪህ አቤት እላለሁ አጋር የለህም ምስጋና ፀጋና ንግስና ላንተ ብቻ ነዉ አጋር የለህም)

2. ወደሚና መጓዝ ዘጠነኛዉ ቀን ፀሀይ እስከምትወጣ ድረስ ሚና መቆየት ስምንተኛዉ ቀን ላይ ዙህርን ዐስርን መግሪብን ዒሻን እና ፈጅርን (ሚና) ይስገድ ፡፡ እያንዳንዱን ሶላት በወቅቱ መስገድ አለበት ባለ አራት ረከዓ የሆኑትን ሶላቶቹ ብቻ ሁለት ሁለት ረከዓ እያደረገ ይስገድ

<u>ሁለተኛዉ ቀን ወይም በዘጠነኛዉ ቀን ላይ ሐጃጁ መሰራትያለበት ስራ</u>

1. ፀሀይ ከወጣች በኋላ ዐረፋ ይሂድ ዙህርን እና ዐስርን በማሳጠር ተቅዲም በማድረግ ይስገድ ከዕኩለ ቀን በፊት ከቻለ ነሚራ ላይ ቆይታ ያድርግ

2. ሶላት ከሰገደ በኋላ ፀሀይ እስከምትገባ ድረስ እጆቹን ከፍ በማድረግና ወደ ቂብላ በመዞር ሌሎች ነገሮችን በሙሉ በመተዉ በዚክር እና አላህን በመለመን ጊዜዉን ያሳልፍ

3. ፀሀይ ከገባች በኋላ ሙዝደሊፋ ይሂድ ሙዝደሊፋ ላይ መግሪብን ሶስት ኢሻን ሁለት ረከዓ አድርጎ ይስገድ ነህ እስከሚወጣ ድረስ ሙዝደሊፋ ላይ ቆይታ ያድርግ

4. ፈጅር ከወጣ በኋላ የፈጅር ሶላትን ይስገድ በጣም እስከሚነጋ ድረስ ጊዜዉን በዚክር እና በዱዓ ያሳልፍ

5. ፀሀይ ከመዉጣቷ በፊት ሚና ይሂድ

<u>አስረኛ (ሶስተኛዉ) ቀን ላይ ሚና የሚሰራ ስራ ማለትም የዒድ ቀን</u>

1. ሚና እንደደረሰ ጀምረተል አቀባ ይሂድ ሰባት ጠጠሮችን በተከታታይ ለያንዳንዱ ጠጠር አላሁ አክበር እያለ ይወርዉር

2. የሚያርደዉ ከያዘ ይረድ

3. ፀጉሩን ይላጭ ወይም ያሳጥር ይህን ካደረገ የመጀመሪያዉን ፍች ይፈታል ልብሱን ይልበስ ሺቶ ይቀባ ኢህራም በማድረጉ ምክንያት ተከልክሏቸዉ የነበሩ ነገሮች ሁሉ ይፈቀዱለታል ከሴትጋር ግንኙነት ብቻ ሲቀር፡፡

4. መካ በመመለስ ጠዋፈል ኢፋዷን ሰባት ጊዜ ከዕባን ይዙር (ነገር ግን እዚህ ጠዋፍ ላይ ትከሻ መግለፅም ሆነ ሮጥ ሮጥ ማለት የለም) በሶፋና በመርዋ መካከል ሰዕይ ያድርግ ሙተመቲዕ ከሆነ እንዲሁም ሙተመቲዕ ባይሆንም ከመግቢያ ጠዋፍ /ጠዋፈልቁዱም/ ጋር ሰዕይ ካላደረገ ሰዕይ የማድረግ ግዴታ አለበት ጠዋፈል ኢፋዷን ካደረገ ተከልክሏቸዉ ከነበሩ ነገሮች ሁለተኛ ይፈታል ነገሮች በሙሉ ይፈቀዱለታል፡፡ (የግብረ ስጋ - ግንኙነት ማድረግን ጨምሮ ማለት ነዉ)

5. አራተኛው ቀን፡ አስራ አንደኛዉን ሌሊት ሚና ለማደርሚና ይመለስ

<u>አራተኛዉ ቀን ላይ ማለት አስራ አንደኛዉ ቀን ላይ የሚሰራ ስራ</u>

1. እሶስቱ ጠጠር መወርወሪያ ገንዳ ዉስጥ ይወርዉር ጀምረተል ኡላና ጀምረተል ዉስጧ ከዚያም ጀምረተል አቀባ ለያንዳንዱ

ሰባት ጠጠር በተከታታይ አላሁ አክበር እያለ ይወርዉር የዙሁር ወቅት ከገባ በኋላ እንጅ ሳይገባ መወርወር አይቻልም ከጀምረተል ኡላ እና ከጀምረተል ዉስጧ በኋላ ዱዓ ለማድረግ መቆም እንዳለበት አይርሳ፡፡

2. አስራሁለተኛዉን ሌሊት ሚና ላይ በማደር ያሳልፍ፡፡

<u>አምስተኛዉ ቀን ላይ ማለት አስራሁለተኛዉ ቀን ላይ መሰራት ያለበት</u>

1. አራተኛዉ ቀን ላይ በወረወረበት መልኩ ሶስቱም ገንዳዎች ላይ ይወርዉር፡፡

2. ከቸኮለ ፀሀይ ከመግባቷ በፊት ከሚና ለቆ ይሂድ መቆየት ከፈለገም ሚና ላይ ማደር ይችላል፡፡

<u>ስድስተኛዉ ቀን ላይ ማለት አስራ ሶስተኛዉ ቀን ላይ መሰራት ያለበት</u>

ይህ ቀን ሚና ላይ ለዘገየ ብቻ የተለየ ነዉ፡፡

1. በሁለቱ ቀኖች ዉስጥ እንደወረወረ ሁሉ እሶስቱም ገንዳዎች ላይ ይወርዉር።።

2. ከዚህ በኋላ ከሚና ይመለስ

ወደ ሀገሩ መመለስ ባሰበ ጊዜ የመጨረሻ ስራዉ የመሰናበቻ ጦዋፍ መሆን አለበት ወላሁ አዕለም ።።



የሐጅ ማዕዘናትና ግዴታዎች

የሐጅ ግዴታዎች በሁለት ይከፈላሉ:

* አንደኛዉ ክፍል የሐጅ አርካኖችን (ማዕዘናትን) ይመለከታል ሐጃጁ ከዚህ አንዱን ከተወ ሐጁ ዉድቅ ነዉ የሚሆነዉ (ስለዚህ ሌላ ሐጅ እንደገና ማድረግ ይኖርበታል) ሁለተኛዉ ሐጃጁ ከዚህ አንዱን ቢተዉ ሐጁ ዉድቅ አይሆንም

ሐጁ ዉድቅ የሚሆንበት ክፍል አርካኖች (ማዕዘናት) ተብለዉ ይጠራሉ እነሱም፡-

1. ኒያ (ኢህራም) ማድረግ

2. አረፋ ላይ መገኘት

3. ጦዋፈል ኢፋዳ (ከዕባን መዞር) እና

4. ሠዕይ (በሶፋና በመርዋ መካከል ምልልስ ማድረግ) ናቸዉ እነኝህ አራቶቹ ኢህራም አረፋ ላይ መቆም ጦዋፈል ኢፋዳ በሶፋና

በመርዋ መካከል ምልልስ ማድረግ እነኝህ ካልተሟሉ የሐጅ ስራ ትክክል አይደለም ዉድቅ ነዉ።።

ሐጃጁ ከዚህ አንዱን ቢተዉ ሐጁ ዉድቅ አይሆንም የተባለዉ የሐጅ ግዴታዎች (ዋጂባት) በመባል ይጠራሉ።። እነሱም፡-

1. ለኢህራም ማድረጊያ የተከለሉ (የተመደቡ)ቦታዎች ላይ ኢህራም ማድረግ።።

2. የዙል ሂጃ ዘጠነኛዉ ቀን ዐረፋ ላይ ፀሃይ እስከምትጠልቅ ድረስ መቆየት።።

3. (10ኛዉን) የሚድ ሌሊት ሙዝደሊፋ ማደር

4. የሚድ ቀን ጀምረተል አቀባ ጠጠር መወርወር እና አያመትተሸሪቅ ጀምረተል አቀባ ላይና እሌሎቹ እሁለቱ ገንዳዋች ላይ ጠጠር መወርወር

5. ለወንዶች ፀጉርን መላጨት ወይም ማሳጠር ሴቶችግን ማሳጠር ብቻ

6. ሁለት ሌሊቶች ሚና ማደር አስራ አንደኛዉን እና አስራሁለተኛዉን ለቸኮለ ሰዉ ለዘገየ ግን አስራ ሶስተኛዉንም ሌሊት መጨመር እነኝህ ስድስት ነገሮች የሐጅ

ግዴታዎች(ዋጂባት) ናቸዉ ግን ዋጂብ ቢሆኑም ሐጃጁ ቢተዋቸዉ ሐጁ አይበላሽም ::

በርካታዎቹ ዑለማዎች እነኝህን ስድስት ዋጅባት የተወ አንድ ፍየል ወይም ሰባት ሰዎች አንድ ግመል እንዲሁም ሰባት ሰዎች አንድ ከብት መካ ከተማ ዉስጥ በማረድ ለከተማይቱ ድሆች ማከፋፈል ግዴታ አለበት ብለዋል አላህ አዕለም

የመሰናበቻ ጦዋፍ (ጦዋፈል ወዳዕ)ማንኛዉም ሐጅ ያደረገ ሁሉ መካን ለቆ ወደ ሀገሩ ሲመለስ ግዴታ ይሆንበታል:: ኢብን አብባስ ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዳወሱት ሰዎች(መካን) ከመልቀቃቸዉ በፊት ከዕባን ለመጨረሻ ጊዜ እንዲዞሩ (ጦዋፈል ወዳዕ) ታዘዋል :: የወር አበባ የመጣባቸዉ ሴቶች ግን የመሰናበቻዉን ጦዋፍ ሳያደርጉ (መካን)መልቀቅ ይችላሉ :: (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ)

የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ሐጀተል ወዳዕ ላይ የመካን ከተማ ሲለቁ የመሰናበቻ ጦዋፍ (ጦዋፈል ወዳዕ) አድርገዉ እንደለቀቁ ተረጋግጧል ::



አንዳንድ ሑጃጆች የሚፈፅሟቸዉ ስህተቶች

1. ጦዋፍን ከሀጀረል አስወድ በፊት መጀመር

2. ጦዋፍ ሲያደርጉ በሂጅሩ ዉስጥ መዞር

3. እሰባቱም ጦዋፍ ላይ ፈጠን ፈጠን ብሎ መሄድ

4. ሐጀረል አስወዱን ለመሳም ከሰዎች ጋር ሀይለኛ ግፊ መጋፋት

5. ሐጀረል አስወድ በራሱየመጥቀም ሐይል አለዉ ብለዉ ያምናሉ ለዚሂም ነዉ ሀጀሩን በጃቸዉ ከነኩት በኃላ ሌላዉን የሰዉነታቸዉን ክፍል በጃቸዉ የሚያብሱት፡፡

6. የከዕባን ሁሉንም ማዕዘን መንካት እንደዉም የከእባን ግድግዳ በሙሉ በመንካት ሰዉነታቸዉን የሚያብሱ አሉ ይህ ፍፃሜ ደግሞ መሃይምነት እና ጥመት ነዉ፡፡

7. ጦዋፍ በሚደረግ ጊዜ ለሰባቱም ሁሉ ማንኛዉንም ዱዓ የማይጠቀም ሲሆን ለያንዳንዳቸዉ የተለየ ዱዓ መመደብ፡፡

8. ጦዋፍ አድራጊዎች ከፊሎቹ ከሚሰሯቸዉ ስህተቶች ሰዎች በመሰባሰብ ከመካከላቸዉ አንድ መሪ ያደርጋሉ፡፡ የተመረጠዉ ሰዉ ድምፁን ከፍ በማድረግ ዱዓ ሲያደርግ ከዚያም ህዝቦቹ ባንድ ድምፅ ያስተጋባሉ፡፡

9. የጦዋፍ የሆኑትን ሁለት ረከዓ መቃሙ ኢብራሂም አጠገብ ካልሆነ በስተቀር አይቻልም በሚል ግንዛቤ ከሰዎች ጋር መጋፋት እነዚህን ሁለት ረከዓ ደግሞ መስጊዱ ዉስት ከሆነ የትም ቦታ መስገድ ይቻላል

10. ሰዕይ ከሚያደርጉ ከፊል ሰዎች ከሚሰሯቸዉ ስህተቶች ከሶፋ እስከ መርዋ ያለዉን ቦታ በሙሉ መሮጥ እሚሮጠዉ ከመጀመሪያዉ አረንጓዴ ምልክት ጀምሮ እስከ ሁለተኛዉ አረንጓዴ ምልክት ብቻ ነዉ

ከምልክቶቹ ዉጭ ያለዉን በሙሉ በዝግታ ነዉ መሄድ ያለበት፡ ፡

11. እዚህ ቦታ ላይ ከሚሰሩ ስህተቶች ሴቶች በሁለቱ ምልክቶች መካከል ልክ እንደወንዶች መሮጣቸዉ አንዱ ነዉ፡፡

12. ሰዕይ ላይ ከሚከሰቱ ስህተቶች (ኢነ ሶፋ ወልመርወተ ሚን ሸዓኢሪ ላሂ) የሚለዉን አንቀፅ ሶፋ ላይም ሆነ መርዋ ላይ በደረሱ ቁጥር ማንበብ (ማለትም ድምሩ ሰባትይሆናል ማለት ነዉ) የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ሶፋ እንደደረሰ የመጀመሪያዉ ዙር ላይ ብቻ ነዉ እንዲነበብ ያዘዙት፡፡

13. ሰዕይ ላይ ከሚከሰቱ ስህተቶች በሶፋና በመርዋ መካከል ለሚያደርጋቸዉ እንቅስቃሴዎች ለያንዳንዱ ዙር የተለየ ዱዓ መጠቀም

14. ከፊል ሑጃጆች ዐረፋ ላይ ከሚፈፅሟቸዉ ስህተቶች ከአረፋ ክልል ዉጭ መቀመጣቸዉ::

15. እንዲሁም ከአረፋ ፀሀይ ሳትገባ መመለሳቸዉ አንዱ ስህተት ነዉ

16. ዱዓ ሲያደርጉ ወደ አረፋ ተራራ መዞራቸዉ::

17. ሚና እገንዳወቹ ላይ ሲወረዉሩ ወደ ሰይጣን እንደሚወረዉሩ ማመናቸዉ::

18. እገንዳወቹ ላይ ትልልቅ ድንጋዮችና ጫማዎችን እንዲሁም እንጨቶችን መወርወር::

19. በተሸሪቅ ቀኖች እመጀመሪያዉ ገንዳ እና እሁለተኛዉ ገንዳ ላይ ጠጠር ከወረወሩ በኃላ ዱዓ ለማድረግ አለመቆም::

20. ሁሉንም ጠጠሮች ባንድ ጊዜ መወርወር::

21. ጠጠር መወርወርን እንደቀላል ነገር መገመታቸዉ ለዚህም ነዉ በራሳቸዉ መወርወር እየቻሉ ሌላ ሰዉ የሚወክሉት

22. የመሰናበቻ ጦዋፍ ካደረጉ በኃላ መካ ላይ መቀመጥ ስህተት ነዉ ነገር ግን አዲስ ለሚከሰት ነገር ለምሳሌ ፡- ለሶላት ኢቃም ቢደረግ ኡለማዎች መቆየት ይቻላል ብለዋል ከመሰናበቻ ጦዋፍ በኃላ ያልተፈቀዱ በሆኑ ነገሮች ምክንያት ከተቀመጠ የመሰናበቻ ጦዋፍን መድገም ግዴታ ይሆንበታል፡፡

23. ከመሰናበቻ ጦዋፍ በኃላ ከመስጊድ ሲወጡ ፊታቸዉን ወደ መስጊዱ በማዞር ወደ ኃላ መሄድ እንደ ነሱ አባባል ለከዕባ ክብር ከመስጠታቸዉ አንፃር

ይህ ድርጊታቸዉ የሱና ተቃራኒ ይልቁንም ቢድዓ ነዉ

ቢድዓ ማለት እምነትም ሆነ አምልኮት በአላህ መልእክተኛ(ሶ.ዐ.ወ)እና የተቀኑ በሆኑት ኸሊፋዎቹ በነበሩበት ተቃራኒ በሆነ መልኩ አዲስ የተከሰተ ሁሉ ቢድዓ ይባላል፡፡ ለከዕባ ክብር ከመስጠቱ አንፃር በማጅራቱ ወደ ኃላ የሚመለሰዉ ሰዉ እንደሱ አስተሳሰብ የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ለከዕባ ከሚሰጡት ክብር የበለጠ እርሱ የሚሰጠዉ መሆኑን ይገምታልን

ወይስ የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)ይህ አወጣጥ የከዕባን ክብር የሚገልፅ መሆኑን አልተረዱም ማለት ነዉን ?!!

24. የመሰናበቻ የሆነዉን ጦዋፍ እንደጨረሱ እመስጊዱ በር ላይ ሲደርሱ ወደ ከዕባ በመዞር ከዕባን ለመሰናበት ዱዓ ያደርጋሉ ይህ ነገር ቢድዓ ነዉ ለምን ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ)አልሰሩትም (ወይም አላዘዙም) ማንኛዉም ነገር አላህን ለማምለክ ተብሎ የሚሰራ ሁሉ ከሸሪዓ ማስረጃ ከሌለዉ ከንቱ ነዉ የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ዲነል ኢስላም ጋር ግንኙነት የሌለዉን ነገር እነዲከሰት ያደረገ ተቀባይነት የለዉም ብለዋል።(ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት)

በአላህ ና በመልዕክተኛዉ ያመነ ሰዉ በሚያደርገዉ አምልኮት ሁሉ ከመልዕክተኛዉ (ሶ.ዐ.ወ) የተገኘዉን መከተል ግዴታ ይሆንበታል። የአላህን (ሱ.ወ) ምህረትና ዉዴታ ማግኘት ለሚሻ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል (በላቸዉ :- አላህን የምታፈቅሩ ከሆናችሁ ተከተሉኝ አላህ ያፈቅራችኋል ኃጢአቶቻችሁንም ይመራል አላህ መሓሪ አዛኝ ነዉ) ። (አሊ-ኢምራን 31) መልዕክተኛዉን (ሶ.ዐ.ወ) በሰሩት ሁሉ መከተል እንዳለብን ሁሉ ያልሰሩትንም ባለመስራ መከተል አለብን ።

ማንኛዉም ነገር እንዲሰራ የሚያደርገዉ ምክንያቱ በመልዕክተኛዉ (ሶ.ዐ.ወ)ጊዜ እየተገኘ አለመስራታቸዉ ይህ ነገር የሚያመላክተዉ መተዉ ሱና መሆኑን ነዉ ይህ ነገር ሰዎች ቢወዱትም እንኳ በአላህ ዲን ላይ አዲስ ነገር አይፈቀድም።

ሐጅ ማድረግ የፈለገ ሰዉ ሐጅ ከማድረጉ በፊት የሐጅን ህግጋቶች ጠንቅቆ ቢማር አቤት እንዴት ያረካል አላህን (ሱ.ወ) በእዉቀት ያመልከዉ ዘንድ እና መልዕክተኛዉን (ሶ.ዐ.ወ) መከተልን ያረጋግጥ ዘንድ::አንድ ሰዉ እማያዉቀዉ ሀገር ለመሳፈር ቢፈልግ የሚሳፈርበት ሀገር የሚያደርሰዉን መንገድ ሲጠይቅ ታየዋለህ:: ወደ አላህና እንዲሁም ወደ ጀነት እሚያደርስን መንገድ የገባ ሰዉ ፍላጎቱ እንዲሳካለት ይህን መንገድ ከመጀመሩ በፊት መጠየቅ(ግዴታ) እና ተገቢ አይደለምን ? !! አላህ (ሱ.ወ) ቀጥተኛ የሆነዉን መንገዱን እንዲመራን እንዲሁም ከመራን በኋላ ልቦቻችንን እንዳያጠምብን እና እሱ ሰጭ የሆነ ጌታ ነዉና እዝነቱን ይለግስልን ዘንድ እንጠይቀዋለን ::

የአላህ እዝነትና ሠላም ለአገልጋዩና ለመልዕክተኛዉ ለሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ)ለቤተሰቦቻቸዉና ለባልደረቦቻቸዉ ሁሉ ይሁን::



ሐጅ ላይ ያለ ሰው በምን አይነት ሥራ ይጠመድ?

ጥያቄ፡- በሐጅ ጊዜ ውስጥ ሐጀኛ ሊፈፅማቸው የሚገቡ ስራዎች ምንድን ናቸው?

መልስ፡- "ሐጀኛ በሐጅ ጊዜው አላህን በማውሳት-በዚክር-፣ በሚባዳ፣ የአላህን ትዕዛዛት በመከወን እና ወደ አላህ የሚያቃርቡ በሆኑ በነ ሥራዎች-በሶደቃ፣ ደካሞችን በማገዝ፣ እውቀት የሌላቸውን በማስተማር...- ራሱን መጥመድ ነው ያለበት። ባገኘው አጋጣሚ አብዝቶ ቁርአንን ማንበብ ይወደድለታል። በቻለው አቅም ታላቁ መስጂድ (መስጂዱል-ሐራም)ውስጥ ኢዕቲካፍ ማድረግ ተወዳጅ ስራው ነው። ካልተቸገረ ወይም ሰዎችን ማጣበብ እስካልሆነበት ድረስ በአላህ ቤት ላይ መዞር (ጠዋፍ ማድረግ) እጅግ ተመራጭ ስራ ነው። ጠዋፍ አንድ ሙስሊም መካ ውስጥ እንጂ ሊያገኘው የማይችለው አምልኮ ነው። ጠዋፍ የዑምራ ግማሽ ነው። ዑምራ ጠዋፍና በሶፋና በመርዋ መካከል መመላለስ ነው።

ሐጀኛ አላህ እርም ካደረገበት ነገር ዐይኑን መስበር አለበት። ምላሱንም ከሃሜት፣ ከስድብና ከቧልት ማቀብ አለበት። እጁንም ሰዎችን ከማስቸገር እና ከማስከፋት መጠበቅ አለበት። ሙስሊም ማለት ሙስሊሞች ከምላሱና ከእጁ ተንኮል የዳኑለት ሰው ነው። አላህ በሐጅ ውስጥ የወሲብ ወሬን፣ ፍስቀትን(በአላህ ላይ ማመጽ) እና ክርክርን እርም አድርጓል። ይህ ጉዞ የሰላምና የፍቅር እንዲሆን የክርክር እና የጥላቻ መንገዶችን አላህ ዘግቷል።”



የሐጅ ስርዐተ ምስጢራት በጥቂቱ

ጥያቄ፡- እጅግ ዋና የሆነው የሐጅ ስርዐት ምስጢር የቱ ነው?
መልስ፡- "ምሳሌያዊ ቋንቋውን ከተረዳን የብዙዎቹን የሐጅ ስራዎች (መናሲከል-ሃጅ) ምስጢር ማወቅ እንችላለን።
ኢሕራም:- የመጀመሪያው የሐጅ ስራ- ኢሕራም- ራስን ወደ ሐጅ ስራ ማስገባት እና በአላህ በተቀመጡ መርሆች ስር ማደር ማለት ነው። በእውነቱ ይህ ከነፍስ ፍላጎት፣ ከደመነፍስ ዝንባሌ ራስን አላቆ ከአላህ ውጪ ካሉ ነገሮች ፍላጎቷን በማገድ ስለ አላህ ታላቅነት በማሰብ እንድትታጠር ማድረግ እንጂ ሌላ አይደለም።

ተልቢያህ፡- ተልቢያህ (ለበይክ ማለት) ይህንን ገደብ በነፍስ ላይ ማረጋገጥ እና በምላስ መመስከር እንጂ ሌላ አይደለም። መታዘዝን ፈጣሪን በብቸኝነት መቀበልን የሚያረጋግጥ ንግግር እንጂ ሌላ አይደለም።

ጠዋፍ፡- ለብቸኝነቱ ከማደር በኋላ በአላህ ቤት ላይ መዞር (ጠዋፍ) በአላህ ቅድስና ዙርያ ቀልብን ማሽከርከር እንጂ ሌላ አይደለም። ውለታው እንጂ ህላዌው የማይታየውን ባለውለታ ወዳጁን ማስደሰት የሚችልበት መንገድ የተደናገረው አፍቃሪ የሚሰራው ስራ ይመስላል።

ሰዕይ፡- ከጠዋፍ በኋላ በሶፋና በመርዋ መሀል ሰዕዩ የእዝነት ምልክት በሆኑት ሁለቱ ቦታዎች መሀል ምህረት እና ርህራሄን ፍለጋ መመላለስ እንጂ ሌላ አይደለም።

ውቁፍ፡- ከሰዕይ በኋላ ዐረፋ ሜዳ ላይ መቆምስ (ውቁፍ) በፍርሃት በተሞላ ልብ፣ ለልመና በተዘረጋ እጅ፣ በዱዓእ በተጠመደ ምላስ፣ በአዛኞች አዛኝ ላይ በተጠነሰሰ ተስፋ... ለአላህ ለመዋደቅ መንፈስን መለገስ እንጂ ሌላ አይደለም።

ረሚይ፡- የልብ ብርሃንን ከሚፈነጥቀው ከዚህ ተግባር በኋላ ጠጠር መወርወርስ (ረሚይ) ቢሆን ተንኮል እና የሸር ሰራተኞችን መናቅና መጥላትን፣ የነፍስን ክፉ አባዜ ማውገዝን የምንገልፅበት ምሳሌ እንጂ ሌላ አይደለም። ግለሰብንም ሆነ ህዝብን ከሚበክለው ደመነፍስ ራስን ለማራቅ ያለን ወኔ የሚጠቁም ቁሳዊ ገለፃ እንጂ ሌላ አይደለም።

ዘብህ፡- እርዱስ ቢሆን ለንፅህና እና ለፅዳት ደረጃ መብቃትን የሚጠቁም መደምደሚያ እንጂ ሌላ አይደለም። ታላቅነትን በመገንባት ላይ በጠነከረ እጅ መቆሸሸን የምናርድበት ምልክት እንጂ ሌላ አይደለም። ንፁህ እና መልካም የአላህ ሰራዊቶች መስዋእትነትንና ትጋትን የሚያመለክት ዓርማ እንጂ ሌላ አይደለም!''

❋ ❁ ❋

የነቢዩን ﷺ መስጊድ ጉብኝት የሚመለከት ድንጋጌ

መዲና ረሱል ሰ. አ. ወ የተሰደዱባት፣ተረጋግተው የኖሩባት ወህይ የወረደባት ሀገር ናት።መዲና የረሱል ሰ. አ. ወ መስጊድ ያለበት ሲሆን መስጊዱም ከሶስቱ ለኢባዳ ጉዞ ከተፈቀደባቸው መስጊዶች አንዱ ነው::

የነቢዩን ﷺ መስጊድ መጎብኘት ከሐጅ ሸርጦች፣ከማእዘናቱ፣ ከዋጅቦቹም ሆነ ከሱናዎቹም ውስጥ አይደለም:: ወደ መዲና ሲኬድ ኢህራም አይደረግም ጉብኝቱ በማንኛውም ወቅት የተደነገገ ነው::

የጉብኝቱ ዓላማ መቃብሩን ለመጎብኘት ሳይሆን በመስጊዱ ሶላት ለመስገድ መሆን ይኖርበታል:: አቡ ሁረይራ (ረዐ) ባስተላለፉት መሰረት ነቢዩ ﷺ ‹‹ወደ ሦስት መስጊዶች ብቻ እንጂ (ለዕባዳ ተብሎ) ጉዞ አይደረግም፤እነሱም :- (የመካው) የተከበረው መስጊድ፣የመልእክተኛው ﷺ መስጊድና የአልአቅሷ መስጊድ ናቸው::›› [በሙስሊም የተዘገበ] ብለዋል::

ሸይኹል እስላም እብን ተይምይያ እንዲህ ብለዋል:- ‹‹የጉዞ ዓላማው በመስጊዳቸው ለመስገድ ሳይሆን መቃብሩን መጎብኘት

ከሆነ . . . የኢማሞችና የአብዛኞቹ ዑለማእ አቋም ይህ ያልተደነገገና ያልታዘዘ ነው የሚል ነው፡፡ . . .

የነቢዩን ﷺ መቃብር መጎብኘትን የሚመለከቱ ሐዲሶች በሁሉም የሐዲስ ሊቃውንት ሙሉ ስምምነት ደዒፍ (ደካማ) ሐዲሶች ናቸው፡፡እንዲያውም የፈጠራ (መውዱዕ) ሐዲሶች ናቸው፡፡ ተቀባይነት ካላቸው የሱነን ባለቤቶች ውስጥ አንድም ሰው አልዘገባቸውም፤ከኢማሞች ውስጥም አንድም ኢማም አንዱንም (ሐዲስ) በማስረጃነት አላቀረበም፡፡›› [መጅሙዕ አልፈታዋ ክፍል 27 ገጽ 26]



ዝያራንና ኣዳቡን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች

1 - ጎብኚው ወደ መስጊዱ ሲደርስ ቀኝ እግሩን አስቀድሞ ‹‹አልሏሁምመ እፍተሕ ሊ አብዋበ ረሕመትከ›› [በሙስሊም የተዘገበ]ማለት ሱና ነው።።

2 - ሁለት ረከዓ ተሕይቱል መስጅድ ይሰግዳል።። ሶላቱ በተከበረው ረውዷ ቢሰግድ በላጭ ነው።።

3 - የነቢዩን ﷺ እና የሁለቱ ባልደረቦቻቸውን መቃብር መጎብኘት ሱና ይሆናል።። ከነቢዩ ﷺ መቃብር ትይዩ በአደብና በእርጋታ ቆሞ ድምጹን ዝቅ በማድረግ ‹‹አስ’ሰላሙ ዐለይከ አይ’ዩሀን’ነቢዩ ወረሕመቱሏሂ ወበረካቱህ፤ሰል’ለል’ሏሁ ዐለይከ፤ ወጀዛከ ዐን ኡም’መትከ ኸይረን።።›› ይላል።።

ትርጉሙ ‹‹ አንቱ ነቢዩ ሆይ! የአላህ ሰላም፣እዝነቱና በረከቶቹ ለርስዎ ይሁን።። ከአክብሮት የተቀናጀ የአላህ ረሕመት በርስዎ ላይ

ይውረድ፡፡ አላህ ለኡመትዎ ለዋሉት ውለታ መልካሙን ይዋልልዎት፡፡›› ማለት ነው፡፡

ከዚያም ወደ ቀኝ አንድ ወይም ሁለት እርምጃዎችን በመራመድ ከአቡበከር (ረዐ) መቃብር ፊት በመቆም ‹‹አስ'ሰላሙ ዐለይከ ያ አባ በከር ያ'ሺሊፈተ ረሱሊልላህ ﷺ ወረሕመቱልሏሂ ወበረካቱሁ፤ረድየሏሁ ዐንከ፣ወጀዛከ ዐን ኡምመት ሙሐመድን ﷺ ኸይረን፡፡›› በማለት ሰላምታ ማቅረብ፡፡

ከዚያም ወደ ቀኝ አንድ ወይም ሁለት እርምጃዎችን በመራመድ ከዑመር (ረዐ) መቃብር ፊት በመቆም ‹‹አስ›ሰላሙ ዐለይከ ያ ዑመር ያ አሚረል ሙእምኒን ወረሕመቱልሏሂ ወበረካቱሁ፤ ረድየሏሁ ዐንከ፣ወጀዛከ ዐን ኡምመት ሙሐመድን ﷺ ኸይረን፡ ፡›› በማለት ሰላምታ ማቅረብ፡፡

4 - የነቢያዊውን መስጊድ ለሚጎበኝ ሰው የአምስቱንም ወቅቶች ሶላት በነቢዩ ﷺ መስጊድ መስገድ፣መስጊዱ ውስጥ የአላህን ዝክርና ዱዓእ፣የሱና ሶላቶችን በተለይም በተከበረው ረውዷ ውስጥ ማብዛት ሱንና ነው፡፡

5 - የቁባእ መስጊድን እዚያ ለመስገድ መንብኘት ሱንና

ሲሆን ጉብኝቱ ቅዳሜ ቀን ቢሆን በላጭ ነው፡፡ ከእብኑ ዑመር (ረዐ) በተላለፈው መሰረት ‹‹የአላህ መልእክተኛ ﷺ በእንስሳ ጀርባ ተቀምጠውና በእግርም ወደ ቁባእ መስጊድ ይመጡና ሁለት ረከዓ ይሰግዱበት ነበር፡፡››ብለዋል፡፡ በሌላ ዘገባ ‹‹ወደ ቁባእ ይመጡ ነበር›› የሚል ተመልክቷል፡፡ በየቅዳሜው ማለት ነው፡ ፡ [በሙስሊም የተዘገበ]

6 - የበቂዕ መቃብሮችን፣የሹሀዳእና የሐምዛን መቃብር መንብኘትም ሱንና ነው፤ነቢዩ ﷺ ይጎበኟቸውና ‹‹አስ’ሰላሙ ዐላ አህል አድ’ዲያር ምነል ሙእምኒነ ወልሙስሊሚን፣ወእን’ና እንሻአል’ኋሁ ብኩም ላሕቁን፡፡ አስአሉል’ኋህ ለና ወለኩም አልዓፍያ›› [በሙስሊም የተዘገበ] በማለት ዱዓእ ያደርጉላቸው ነበር፡፡

በዚያራ ውስጥ የሚከሰቱ ስህተቶችና ማሳሰቢያዎች

1 - መቃብሩንና በመዲና የሚገኙ ታሪካዊ ስፍራዎችን ለመጎብኘት ዓላማ መሳፈር፡፡ የተደነገገው ነቢያዊውን መስጊድ ለመጎብኘትና እዚያ ለመስገድ ዓላማ ጉዞ ማድረግ ብቻ ነው፡፡ መቃብሩን መጎብኘትም በዚህ ውስጥ ይገባል፡፡

2 - በዱዓእ ጊዜ ፊትን ወደ መቃብሩ ማዞር፡፡

3 - ነቢዩን ﷺ መለመንና ከአላህ ሌላ ጉዳዩን እንዲፈጽሙለትና ሃጃውን እንዲሞሉለት መጠየቅ፡፡ ይህን ማድረግ በአላህ ማጋራትና ዐቢይ ሽርክ ነው፡፡

4 - በከፍሉ ግድግዳ ላይ በረከት ለማግኘት ዓላማ መተሻሸትና በእጅ መነካካት፡፡ ይህ ሐራም የሆነ ብድዓና ወደ ሽርክ የሚያደርስ መረማመጃ ነው፡፡

5 - በነቢዩ ﷺ መቃብር አጠገብ ድምጽን ከፍ ማድረግና ብዙ መቆም፣ወደዚያ በገቡ ቁጥር ከሩቅ ሆኖ ሰላምታ መደጋገም፣ ሰላምታ በሚያቀርብበት ጊዜ ሶላት ውስጥ እንደሚደረገው ዓይነት ቀኝ እጅን ደረት ላይ በግራው ላይ አድርጎ መያዝ፡፡

ለጎብኚዎች የሚፈቀዱ ሱናዎች

1. በቂዕ የሚባለውን መካነ መቃብር መዘየር ምክንያቱም ብዙ ሰሀባዎች የተቀበሩበት ሲሆን ከነሱም ውስጥ ሶስተኛው ኸሊፋ ኡስማን ኢብኑ አፋን ረ. ዓ ይገኙበታል።
2. የኡሁድ ሰማእታትን መዘየር ከነሱም ውስጥ የሰማእታት አለቃ ሀምዛ ረ. ዓ ይገኙበታል ሁሉንም አላህ እንዲወዳቸው ዱአ ማድረግ ።
3. ወደ ቁባእ መስጊድ በመሄድ ሰላት መስገድ መስጂድ ቁባእ በኢስላም የመጀመሪያው መስጊድ ነው ።
" ከቤቱ ታጥቦ ወደ መስጂድ ቁባእ በመሄድ ሰላት የሰገደ የኡምራን ምንዳ ያህል ነው" ነቢዩ ሰ. አ. ወ
4. ከእነዚህ መስጊዶች ውጪ መዲና ውስጥ ሌላ የሚጎበኝ መስጊድ በሸሪአ የለም ።ስለዚህ ማንም ሰው ምንም ላይጠቅመው መዲና ውስጥ ወዲያና ወዲህ በመመላለስ ጊዜውን ባያቃጥልና ባይለፋ የተሻለ ነው ።



አሥሩ የዚልሂጃ ቀናት- ከዱኒያ ቀናቶች ሁሉ በላጮች

ከዱኒያ ቀናቶች ሁሉ እጅግ በላጮች የሆኑት የመጀመሪያዎቹ አሥሩ የዚልሂጃ ወር ቀናት ናቸው። እነሆ እነኚህ ምርጥ ቀናት ከፊት ለፊታችን ተደቅነዋል። ለዚህም ይመስላል ሙስሊሙ የአላህን ቤት ከዕባን ለመጎብኘት ያለው ጉጉቱ ድንበር አልፏል፤ በከዕባ ዙሪያ ጠዋፍ ለማድረግ፣ በሶፋና መርዋ መካከል ለመሮጥ እና ዐረፋ ላይ ቆሞ አላህን ለመለመን ያለው ስሜት ጣሪያ ነክቷል። የታላቁን ነቢይ መስጅድ መስጅደ-ነበዊን ለመጎብኘትና በመስጅዱ ውስጥ በተከበረው ቦታ ረውደቱ ሸሪፋ ላይ ለመስገድ ያለው መነሣሣት ውስጥን ይነቀንቃል፤ በሀሣብ ያምሣል፣ ከንፍ ቢኖር "ምነዋ ወደዚያ ወደተቀደሰው ምድር በበረርኩ!" ያስብላል።

ወዳጆቼ! እኛስ እነኚህ እጅግ የተባረኩና የተከበሩ ቀናቶች ከያዙት ምንዳ ለመቋደስ ምን ማድረግ እንችል ይሆን?

አላህ ሱብሃነሁ ወተዓላ ዘወትር በትእዛዙ በመገኘት ለቋሚው ሀገራቸው ለሚሰንቁ መልካም ባሮቹ በነኚህ በተባረኩ ቀናት ውስጥ ምን ዓይነት ትልቅ ምንዳ ይሆን ያዘጋጀላቸው?

የዚልሂጃ ወር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ታላቅነት

1. አላህ ሱብሃነሁ ወተዓላ የማለባቸው ቀናት መሆናቸው

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ አለ

﴿وَالْفَجْرِ (١) وَلَيَالٍ عَشْرٍ (٢) وَالشَّفْعِ وَالْوَتْرِ﴾ الفجر ١-٣

"በነህ እምላለሁ። በዐሥር ሌሊቶችም። በጥንዱም በነጠላውም።" **(አል-ፈጅር 89፤ 1-3)**

ከጃቢር ኢብኑ ዐብዱላህ (ረ.ዐ) እንደተዘገበው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እነኚህ አሥር ቀናቶች የትኞቹ እንደሆኑ በሚያመላክተው ሀዲሣቸው ውስጥ እንዲህ ብለዋል፡-

(العشر عشر الأضحى، والوتر يوم عرفة، والشفع يوم النحر)

"አሥሩ ማለት አሥሩ የአድሃ ቀናት ናቸው። 'ወትር'/ ነጠላው/ የተባለው የዐረፋ ቀን ሲሆን 'ሸፍዕ' /ጥንዱ/ ማለት ደግሞ የነህር /የእርዱ/ ቀናት ናቸው።" ብለዋል። ሀዲሱን ኢማም ነሣኢ እና ሃኪም በሙስሊም መስፈርት መሠረት ሰሂህ ትክክለኛ ሀዲስ ነው ብለውታል።

ኢማም በይሀቂ ከዐብዱላህ ኢብኑ ዙበይር እንደዘገቡት ደግሞ:-

(ليالٍ عشر، العشر الثماني، وعرفة، والنحر)

“አሥርቱ ሌሊቶች የመጀመሪያዎቹ ስምንቶቹ፣ የዐረፋ ቀን እና የእርድ ቀን ናቸው።” ብለዋል።

2. እነኚህ ቀናት “አያም መዕሉማት” /የታወቁ ቀናት/ም ይባላሉ

ይህም በሚከተለው የቁርዓን አንቀፅ ውስጥ የተጠቀሠ ነው።

﴿وَيَذْكُرُوا اسْمَ اللَّهِ فِي أَيَّامٍ مَّعْلُومَاتٍ﴾

“በታወቁ ቀኖችም ውስጥ የአላህን ስም ያወሱ ዘንድ” (አል-ሀጅ 22፤ 27)

“የቁርዓን ተርጓሚ” በመባል የሚታወቁት ታላቁ ሰሃባ ዐብዱላህ ኢብኑ ዐባስ እነኚህ ቀናት “አሥርቱ ቀናት” ናቸው ያሉ ሲሆን በነኚህ ቀናት ውስጥ ታላቁን ጌታ አላህ ሱብሃነሁ ወተዓላን በብዛት ማውሳት የተወደደ ነው።

3. ከዱኒያ ቀናቶች ሁሉ በላጮቹ

ይህም በሚከተለው ሀዲስ ውስጥ ተነግሯል። ከጃቢር (ረ.ዐ) እንደተዘገበው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

(أفضل أيام الدنيا أيام العشر، يعني: عشر ذي الحجة، قيل: ولا مثلهن في سبيل الله؟، قال ولا مثلهن في سبيل الله إلا رجل عفر وجهه في التراب، وذُكر عرفة، فقال يوم مباهاة ينزل الله تبارك وتعالى إلى سماء الدنيا، فيقول: عبادي شعثًا غبرًا ضاحين، جاءوا من كل فجٍّ عميق يسألون رحمتي، ويستعيذون من عذابي ولم يروا، فلم نر يومًا أكثر عتيقًا وعتيقة من النار)

''ከዱኒያ ቀናቶች ሁሉ በላጮቹ አስሩ ቀናት ናቸው። ማለትም አሥሩ የዚልሂጃ ቀናት። በአላህ መንገድ ላይ መውጣትም ቢሆን የነሱ አምሣያ የለምን? ተብለው ተጠየቁ። እርሳቸውም 'በአላህ መንገድ ላይም ቢሆንም እነሱን የሚመስል የለም። ፊቱ ከአፈር የተገናኘ ሰው (በአላህ መንገድ ላይ የሞተ) ሲቀር።' አሉ። ስለ ዐረፋም ተወሳና መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ 'እሱ የሙባሃት /አላህ በባሮቹ የሚኩራራበት/ ቀን ነው። አላህ ወደ ቅርቢቱ ዓለም ይወርድና ባሮቼ ተንጨፋረው፣ አቧራ የለበሱ ሆነውና ተንሣቁለው እሩቅ ከሆነ አቅጣጫ ሁሉ እዝነቴን ሊጠይቁ እሷን ያላዩ ሲሆን ከእሣቴም በኔ ሊጠበቁ መጡ። ወንድም ሆነ ሴት በብዛት ከእሣት ነፃ የሚወጡበት እንዲዚህ ቀን አላየንም'።
'' (በዛር ሀዲሱን ዘግበውታል)

4. በርካታ የሀጅ ሥራዎች የሚሠሩት በነኚህ ቀናት ውስጥ ነው

ከነኚህም መካከል የዚልሂጃ ስምንተኛ ቀን በሙዝደሊፋ ይታደራል፤ በዘጠነኛው ቀን በዐረፋ ላይ ይቆማል፤ ከዚህም በተጨማሪ ለመስዋእት የሚሆን እንሠሳት መንዳት፣ ጠጠር መወርወር፣ ፀጉር መላጨት አሊያም ማሣጠር፣ በዚልሂጃ አሥረኛው ቀን ጠዋፍ ማድረግንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

5. የአምልኮ ዘርፍ የሆኑት ዋና ዋናዎቹ የሚሰበሰቡባቸው ቀናቶች ናቸው

ኢማም ሃፍዝ ኢብኑ ሀጀር ፈትሁልባሪ በተሠኘው ታዋቂ ኪታባቸው ውስጥ እንዲህ ይላሉ

(والذي يظهر أن السبب في امتياز عشر ذي الحجة لمكان اجتماع أمهات العبادة فيه، وهي الصلاة والصيام والصدقة والحج، ولا يتأتى ذلك في غيره)

"የዚልሂጃ አሥርቱ ቀናትን ለየት ከሚያደርጉ ነገሮች መካከል ቦታው ከአምልኮ ተግባራት ዋና ዋና የሚባሉት በአንድ ላይ ተሰባስበው የሚሠሩበት መሆኑ ነው። ይህውም ሰላትን፣ ፆምን፣ ሰደቃን (ምጽዋትን) እና ሀጅን ያጠቃልላል። ከነኚህ ቀናት ውጭ እነኚህ ሁሉ ነገሮች አንድ ላይ የሚሰባሰቡበትን ኢጋጣሚ አናገኝም።" (ፈትሁልባሪ ቅጽ 2፣ ገጽ **462**)

በነኚህ ቀናት ውስጥ ከሚወደዱ ሥራዎች መካከል

1. ሐጅና ዑምራ ማድረግ

በነኚህ ቀናት ውስጥ የሚሠሩ ምርጥ የአምልኮ ሥራዎች ናቸው። ምክኒያቱም የነኚህ አምልኮ ሥራዎች ትክክለኛ ወቅቱ ይህ ነውና። ከአቢሁረይራ (ረ.ዐ) እንደተዘገበው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ)እንዲህ አሉ:-

(العمرة إلى العمرة كفارة لما بينهما، والحج المبرور ليس له جزاء إلا الجنة)

"አንደኛው ዑምራ እሰከ ሌላኛው ዑምራ በመካከላቸው የተሰራ ወንጀልን ያብሣልኝ መብሩር /የተሟላ/ የሆነ ሀጅ ምንዳው ጀነት ብቻ እንጂ ሌላ ኣይደለም።" (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

2. በበጎ ሥራዎች ላይ መበርታት

ከዐብዱላህ ኢብኑ ዐባስ (ረ.ዐ) እንደተዘገበው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ:-

(ما مِن عمل أفضل من عمل فى هذه الأيام العشر، قالوا: ولا الجهاد؟ قال ولا الجهاد إلا رجل خرج بماله ونفسه فلم يرجع منه بشيء)

“በነኚህ አሥር ቀናት ውስጥ የሚሠራ ሥራን የሚበልጥ ምንም የለም። ‘ጅሃድም ቢሆን?’ አሏቸው። እርሣቸውም ‘አዎን ጅሃድም ቢሆን ገንዘቡንና ነፍሱን ይዞ ወጥቶ ያልተመለሰ ሰው ብቻ ሲቀር።’ አሉ።” (ኢማም አህመድና ቱርሙዚ ዘግበውታል)

እንዲሁ በሌላ ዘገባም:-

(لا تطفئوا سرجكم ليالي العشر)

“በአሥርቱ ቀናት ለሊቶች ውስጥ መብራታችሁን አታጥፉ።” የሚል ዘገባ የመጣ ሲሆን ይህም ትርጉሙ “በነኚህ ቀናት ውስጥ ቁርዓን ቅሩ፣ በሰላትም በርትታችሁ ቁሙ ለማለት ነው” ተብሏል።

3. ዚክር ማብዛት

ከኢብኑ ዑመር (ረ.ዐ) እንደተዘገበው የአላህ መልእክተኛ ﷺ እንዲህ አሉ:-

(ما من أيام أفضل عند الله ولا العمل فيهن أحب إلى الله من هذه الأيام العشر، فأكثروا فيهن من التهليل والتكبير وذكر الله، وإن صيام يوم منها يعدل بصيام سنة، والعمل فيهن يضاعف سبعمائة ضعف)

“በደረጃቸውም ሆነ በውስጣቸው በሚሠራ ሥራ ከነኚህ አሥር ቀናት የሚበልጥ በአላህ ዘንድ አንድም የለም። በነሱ ውስጥ ላኢላህ ኢለላህ፣ አላሁ አክበር ማለትንና አላህን ማውሣት አብዙ። ከነሱ ውስጥ አንድ ቀን መፆም የአመት ፆምን ይስተካከላል። በነሱ ውስጥ የሚሠራ ሥራ እስከ ሰባት መቶ ድረስ እጥፍ ድርብ ይሆናል።” (በይሀቂና ኢማም አህመድ ዘግበውታል)

4. በነሱ ውስጥ ተክቢራ ማብዛት

ዐብዱላህ ኢብኑ ዑመር እና አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) በአሥርቱ ቀናት ውስጥ “አላሁ አክበር!” እያሉ ወደ ገበያ ይወጣሉ። ሰዎችም የነሱን ተክቢራ እየተቀበሉ “አላሁ አክበር!” ይሉ ነበር። እንዲህም ብለዋል። “ዑመር በሚና በሚገኘው ቁባቸው ውስጥ ተክቢራ ያደርጉ የነበረ ሲሆን በመስጅድ ውስጥ ያሉ ሰዎችም እርሣቸውን ይሰሙና ‘አላሁ አክበር!’ ይሉ ነበር። ገበያ ውስጥ ያሉ ሰዎችም ሚና በተክቢራ እስክትናወጥ ድረስ ‘አሏሁ አክበር!’ ይሉ ነበር።” ብለዋል። (ፈትሁል ገፋር ቀጽ 5፣ ገጽ **379**)

5. ሀጅ ሥራ ውስጥ ላልተሠማራ ሰው የመጀመሪያዎቹን ዘጠኝ ቀናት መፆም

ይህንንም ሀሠን፣ ኢብኑ ሲሪን እና ቀታዳህን የመሣሰሉ ታቢዒዮችን ጨምሮ በርካታ ሰሃቦች ሰርተውታል። ኢማም ነወዊ እንዲህ ብለዋል፡-

(ليس في صوم هذه التسعة كراهة بل هي مستحبة استحبابًا شديدًا، لا سيما التاسع منها، وهو يوم عرفة)

"አነኚህ ዘጠኝ ቀናት መፆማቸው የሚጠላ አይደለም። ባይሆን እጅግ ተወዳጅ ነገር ነው። በተለይም ዘጠነኛው ቀን። እሱም የዐረፋ ቀን ነው።" (ሸርሁል ሙስሊም ቀጽ 3፣ ገጽ **245**)

ከአቢ ቀታዳህ እንደተዘገበው ደግሞ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ስለ ዐረፋ ቀን ፆም ተጠየቁ። እንዲህም አሉ፡-

(يكفِّر السنة الماضية والباقية)

"ያለፈውንና የሚመጣውን አመት ወንጀል ያብሳል።" (ኢማም ሙስሊም እና አህመድ ዘግበውታል)

6. ቁርዓንን ማንበብ

ከኢብኑ መስዑድ (ረ.ዐ) እንደተዘገበው የአላህ መልእክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

(من قرأ حرفًا من كتاب الله فله به حسنة، والحسنة بعشر أمثالها، لا أقول الم حرف، ولكن ألف حرف، ولام حرف، وميم حرف)

''ከአላህ ኪታብ አንድ ፊደል ያነበበ ሰው የመልካም ምንዳ አለው። አንዱ መልካም ምንዳ አሥር ተመሣሣይ እጥፍ ይባዛለል። አንድ ሰው 'አሊፍ-ላም-ሚም' ያለ እንደሆነ አንድ ፊደል ሊይደለም። ነገርግን 'አሊፍ' አንድ ፊደል ነው፣ 'ላምም' አንድ ፊደል ነው፣ 'ሚምም' አንድ ፊደል ነው።''(ቡኻሪና ቱርሙዚ ዘግበውታል)

7. ኡድሂያ ማዘጋጀት

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ አለ

﴿فَصَلِّ لِرَبِّكَ وَانْحَرْ﴾

''ስለዚህ ለጌታህ ስገድ፤ (በስሙ) ሰዋም።'' (አል-ከውሰር 108፤ 3)

ከዓኢሻ (ረ.ዐ) እንደተዘገበው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡-

(ما عمل آدمي من عمل يوم النحر أحب إلى الله من إهراق الدم، وإنها لتأتي يوم القيامة بقرونها وأشعارها وأظلافها، وإن الدم ليقع من الله بمكان قبل أن يقع على الأرض فطيبوا بها نفسًا)

“ከነህር /እርድ/ ቀን ሥራዎች ውስጥ የእደም ልጅ ደምን ከማፍሠስ በላይ ወደ አላህ ተወዳጅ የሆነ አንድም ሥራ አልሠራም። እርዷም የቂያማ ቀን ከነፀጉሯና ጥፍሯ ትመጣለች። ደሙም መሬት ላይ ከማረፉ በፊት ከአላህ ዘንድ ቦታ ይይዛል። በዚህም ነፍሣችሁን አስደስቱ (ደስ ይባላችሁ)።” (ቱርሙዚ፣ ሃኪም እና ኢብኑ ማጀህ ዘግበውታል)

ኡድሂያ ማረድ የተዘጋጀ ሰው ኡድሂያውን እስኪያርድ ድረስ ፀጉሩንም ሆነ ጥፍሩን የሰውነቱን መንካት የለበትም። ከኡሙ ሰለማ (ረ.ዓ) በተላለፈው ሀዲስም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ)፦

إِذَا دَخَلَتِ الْعَشْرُ وَأَرَادَ أَحَدُكُمْ أَنْ يُضَحِّيَ فَلا يَمَسَّ مِنْ شَعَرِهِ وَبَشَرِهِ شَيْئًا

“አንዳችሁ ኡድሂያ ለማረድ አስቦ አሥርቱ ቀናት የገቡ እንደሆነ ከፀጉሩም ሆነ ከሰውነቱ አንዳቸውም ነገር አይንካ።” ብለዋል። (ሙስሊም እና ነሣኢ ዘግበውታል።)

﴿إِنَّ فِي خَلْقِ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَاخْتِلَافِ اللَّيْلِ وَالنَّهَارِ لَآيَاتٍ لِّأُولِي الْأَلْبَابِ (١٩٠) الَّذِينَ يَذْكُرُونَ اللَّهَ قِيَامًا وَقُعُودًا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمْ وَيَتَفَكَّرُونَ فِي خَلْقِ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ رَبَّنَا مَا خَلَقْتَ هَٰذَا

بَاطِلًا سُبْحَانَكَ فَقِنَا عَذَابَ النَّارِ (١٩١) رَبَّنَا إِنَّكَ مَن تُدْخِلِ النَّارَ فَقَدْ أَخْزَيْتَهُ وَمَا لِلظَّالِمِينَ مِنْ أَنصَارٍ (١٩٢) رَّبَّنَا إِنَّنَا سَمِعْنَا مُنَادِيًا يُنَادِي لِلْإِيمَانِ أَنْ آمِنُوا بِرَبِّكُمْ فَآمَنَّا رَبَّنَا فَاغْفِرْ لَنَا ذُنُوبَنَا وَكَفِّرْ عَنَّا سَيِّئَاتِنَا وَتَوَفَّنَا مَعَ الْأَبْرَارِ (١٩٣) رَبَّنَا وَآتِنَا مَا وَعَدتَّنَا عَلَىٰ رُسُلِكَ وَلَا تُخْزِنَا يَوْمَ الْقِيَامَةِ إِنَّكَ لَا تُخْلِفُ الْمِيعَادَ﴾ آل عمران ١٩٠-١٩٤

“ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር ሌሊትና ቀን በመተካካት ለባለ አዕምሮዎች በርግጥ ምልክቶች አሉ። (እነርሱም) እነዚያ ቆመው ተቀምጠውም በጎኖቻቸው ተጋድመውም አላህን የሚያወሱ በሰማያትና በምድር አፈጣጠርም የሚያስተነትኑ ጌታችን ሆይ ይሽንን በከንቱ አልፈጠርከውም። ጥራት ይገባህ ከእሳትም ጠብቀን የሚሉ ናቸው።

ጌታችን ሆይ! እኛ በጌታችሁ እመኑ በማለት ወደ እምነት የሚጠራን ጠሪ አመንንም፤ ጌታችን ሆይ! ኃጢያቶቻችንንም ለኛ ማር ክፉ ሥራዎቻችንንም ከኛ አብስ፤ ከንጹህ ሰዎችም ጋር ግደለን።

ጌታችን ሆይ! በመልዕክተኞችህም ላይ የተስፋ ቃል ያደረግክልንን ስጠን በትንሳዔ ቀንም አታዋርደን ቀጠሮን አታፈርስምና (የሚሉ ናቸው) ።” (አሊ-ዒምራን 3፤ 190-194)

﴿شَهِدَ اللَّهُ أَنَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ وَالْمَلَائِكَةُ وَأُولُو الْعِلْمِ قَائِمًا بِالْقِسْطِ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ﴾ آل عمران ١٨

“አላህ በማስተካከል የቆመ (አስተናባሪ) ሲኾን ከርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ መኾኑን መሰከረ መላእክቶችና የእውቀት ባለቤቶችም (እንደዚሁ መሰከሩ) ከርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤ አሸናፊው ጥበበኛው ነው።” (አሊ-ኢምራን 3÷18)

ኢስላም በአምስት ማዕዘናት ላይ የተገነባ ኃይማኖት ነው። እነዚህም ሸሃዳ (ላኢላሃ ኢለሏህ ሙሐመዱን ረሱለላህ)፣ ሰላት፣ ዘካት፣ ፆምና ሐጅ በመባል ይታወቃል። ያለ አምስቱ ኢስላም የተባለው ቤት አይቆምም። ማዕዘን ከሌለ ቀድሞውንስ ቤት ይታሰባልን? በኢስላም አዋቂዎች ዘንድ አንድ መርህ አለ፡-

ይኸውም አንድ ነገር ማዕዘን ነው (ሩክን) ሲባል ያለ እርሱ ምንም ፋይዳ ሲሆን ነው። ይህ ማለት ከነዚህ አምስት ጉዳዮች አንዱ ከተጓደለ ኢስላም አልተሟላም እንደ ማለት ነው። ለዚህም እነዚህ አምስት ጉዳዮች “አርካኑል ኢስላም” (የኢስላም ማዕዘናት) በመባል ይታወቃሉ።

በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ስለ መጀመሪያው የእምነቱ ማዕዘን ሸሃዳ እንነጋገራለን። ስለመጀመሪያው የኢስላም ማዕዘን በተነሳ ቁጥር ወደ አዕምሮአችን የሚዘልቀው ተውሂድ የሚለው ቃል ነው። ነገር

ግን፤ ሸሃዳ ከተውሂድ ባለፈ መልኩ ብዙ አቅጣጫዎችን ይዳስሳል። በእርግጥ ተውሂድ (አላህን በብቸኝነት መገዛት)፣ ወሳኝና አስፈላጊ ብሎም መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑ አያጠራጥርም።

ሸሃዳ ምንድን ነው?

ሸሃዳ የሚለው ቃል በቁርዓን ውስጥ በተለያዩ አገላለፆች ከአንድ መቶ ስልሳ ጊዜ ባላነሰ ተወስቷል። መሠረታዊ ትርጉሙም "አንድን ነገር በአይን መመልከት፣ በሚገባ መረዳት፣ ወይንም ማመንና መመስከር" የሚሉት ይሆናሉ። ስለዚህም፤ ሸሃዳ በውስጡ ሦስት ፅንሰ ሃሳቦችን አዝሏል ማለት ነው፡-

1. እውቀት
2. እምነት
3. ምስክርነት

ሸሃዳ ግልፅና አጠር ባለ አረፍተ ነገር የሚገለፅ የእምነቱ ማዕዘን ነው። ይኸውም ***"ከአላህ ውጪ በእውነት የሚገዙት አምላክ የለም፣ ሙሐመድም (ሲ.ዐ.ወ) የአላህ መልእክተኛ ነው።"*** የብዙ ሀይማኖቶች የእምነት ፅንሰ-ሀሳብ የሚገለፀው "እኔ አመንኩ" /I believe/ በሚለው ቃል ሲሆን ነገር ግን የኢስላም የእምነት ፅንሰ-

ሀሳብ እኔ አመንኩ በሚለው ቃል አይጀምርም። ይልቁንስ "አሸሃዱ (እኔ አውቃለሁ፣ አምናለሁ፣ በሚገባ ተረድቻለሁ፣ በዚህም ቀና ብዬ ልቆም የምስክርነት ቃሌን እሰጣለሁ)" በሚል የተሟላ ሀሳብ እንጂ።

ይህንን የምስክርነት ቃል ከመወለዳችን ጀምሮ በእያንዳንዷ የቀን ውሎአችን በአዛንና በኢቃማህ (ለሰላት በሚደረግ ጥሪ) ወቅት እንሰማዋለን። ምን ያህሎቻን ቆም ብለን አስበናል? የምንናገረውንና የምንሰማውን በእርግጥ ኖርንበታል? ሸሃዳ በምላስ እንቅስቃሴዎች የሚላወሱ የእምነት ቃላት ብቻ አይደሉም። የህይወት መምሪያ መሣሪያዎች ናቸው። ሸሃዳ፤ "ላኢላሃ ኢለሏህ ሙሐመደን ረሱሉሏህ" ማለት ብቻ አይደለም። በሸሃዳ የሚያምኑ ሠዎች የሸሃዳን እውነትነት ያረጋግጣሉ። በልባችንና በመንፈሳችንም እናውቃለን፤ በግልጽም ሸሃዳን እንመሰክራለን፤ ምስክርነታችንንም በሁለመናችን እንገልጻለን።

ሸሃዳ ሰዎችን ወደ ኢስላም ክልል ያሻግራል። ወደ ግዛቱ ያስገባል። የሰውን እምነት ያዳብራል። ሸሃዳ በእውቀትና በእምነት ከተመሰከረ ህይወትን ይቀይራል። ከፍጡር ባርነት ወደ ፈጣሪ ባርነት ያሸጋግራል። ሁሉም ሰው የአላህ ባሪያ ነው። ሸሃዳን በእውነት የመሰከራት ግን አላህን ወደ ማምለክ (ዒባዳ) ይራመዳል። የተወደደም የአላህ ሰው ይሆናል።

ሸሃዳ ለተውሂድና ለመልዕክቱ እጅ መስጠት ማለት ነው። ሸሃዳ ከአላህ ውጪ በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለና ለሁሉም ነቢያቶችና መልዕክተኞች እውቅናን መስጠት ብሎም ሙሐመድ ﷺ የነቢያቶች መደምደሚያ እንደሆኑ ከልብ ማመንን መመስከር ነው።

የመጀመሪያው የሸሃዳ መርህ ተውሂድ ነው። ተውሂድ (አላህን በብቸኝነት መገዛት) የሰው ልጅ ከማንኛውም ባርነት ነፃ ያወጣል። ከዓለማዊ አጥር ያሻግራል። ለሰውና ሰው ሰራሽ ጣኦታት እጅ ከመስጠት ያድናል። አላህን ብቻ የማምለክን ነፃነት ያጎናፅፋል። የተውሂዱ ባለቤት ለማንም ክብሩን አያዋርድም- ለአላህ ብቻ ሲቀር፤ ለማንም አታጎነብስም ከ አንተ ይበልጡም ይነሱ ለአላህ ብቻ ሲቀር። ከአላህ ውጪ ማንንም አይጠራም። አይለምንም። ከአላህ በላይ ለየትኛውም ስልጣንና ኃይል እውቅና አይሰጥም። ለአላህ በፍፁም ልቡ ታዛዥ ይሆናል። እነዚህን የተውሂዱ ውጤቶች ተውሂደል ዐቡዲያ(ተውሂድ አል ኡሉሂያ) ፣ ተውሂድ አር-ሩቡቢያ ተውሂድ አል-አስማዕ ወሲፋት በማለት እንጠራቸዋለን።

ሸሃዳ የሰውን ልጅ ሰሜቱን ከመገዛቱ ነፃ ያወጣዋል። ከሰይጣን ጎትጓታና ጓደኝነት ያላቅቀዋል። ሸሃዳ ከነበሩበት ያለፉ የኃጢያት ማህደር ለማላቀቅ በቅናቻ ጎዳና እንድራመድ፣ የተቅዋን

የእውነተኝነት ትሩፋት እንድንመለከት ብሎም በፍትሃዊነት ብርሃን እንድንሞላ ያስችለናል።

ሸሃዳ ከጀሃነም ቅጣትም ያድናል። የታማኝ ሸሃዳ ባለቤቶች ዘልአለማዊ መኖሪያቸው ጀነት ናት። ከፍርዱ ቀን መከራዎች በእውነተኛ ሸሃዳቸው ይጠበቃሉ። በጀነት የፈተና ድልድዮች ላይም በፍጥነትና በቀላሉ ያልፋሉ። የስኬትን ሸማም ይደርባሉ።

ሸሃዳ የኢስላማዊ ማህበረሰብ አካል ያደርጋል። ሸሃዳ የፍቅር ምንጭ ነው። ከዘር፣ ቀለምና ጎሳ የላቀ የፍቅር መተሳሰሪያ ገመድም ነው። የማይበጠስ የአላህ ገመድ። ሸሃዳችን የእምነት ብቻ ሳይሆን ማህበረሰባዊና ህብረተሰባዊ ሸሃዳም ነው። በከፍተኛ ድምፅ ለዓለም የምናሰማው የፍትህ ምስክርነታችን ነው። የሰውን ልጅ ሁሉ ከባርነት የምናወጣበት በአላህ ጥላ ስር እንዲሰበሰቡ የምንጣራበት ዓርማችን ነው-ሸሃዳችን።

﴿وَجَاهِدُوا فِي اللَّهِ حَقَّ جِهَادِهِ هُوَ اجْتَبَاكُمْ وَمَا جَعَلَ عَلَيْكُمْ فِي الدِّينِ مِنْ حَرَجٍ مِّلَّةَ أَبِيكُمْ إِبْرَاهِيمَ هُوَ سَمَّاكُمُ الْمُسْلِمِينَ مِن قَبْلُ وَفِي هَٰذَا

لِيَكُونَ الرَّسُولُ شَهِيدًا عَلَيْكُمْ وَتَكُونُوا شُهَدَاءَ عَلَى النَّاسِ فَأَقِيمُوا الصَّلَاةَ وَآتُوا الزَّكَاةَ وَاعْتَصِمُوا بِاللَّهِ هُوَ مَوْلَاكُمْ فَنِعْمَ الْمَوْلَىٰ وَنِعْمَ النَّصِيرُ﴾ الحج ٧٨

“በአላህም ሃይማኖት ተገቢውን ትግል ታገሉ። እርሱ መርጧችኋል። በናንተም ላይ በሃይማኖቱ ውስጥ ምንም ችግር አላደረገባችሁም። የአባታችሁን የኢብራሂምን ሃይማኖት ተከተሉ፡ ። እርሱ ከዚህ በፊት ሙስሊሞች ብሎ ሰይሟችኋል። በዚህም (ቁርአን) ፤ መልከተኛው በእናንተ ላይ መስካሪ እንዲሆን እናንተም በሰዎቹ ላይ መስካሪዎች እንድትኾኑ (ሙስሊሞች ብሎ ሰይሟችኋል)። ሶላትንም አስተካክላችሁ ስገዱ፣ ዘካንም ስጡ፣ በአላህም ተጠበቁ፣ እርሱ ረዳታችሁ ነው። (እርሱ) ምን ያምር ጠባቂ! ምን ያምርም ረዳት!” (አል-ሐጅ 22፡78)



ኢስላም፣ ኢማንና ኢህሳን

عَن عُمَر رضي اللهُ عنه قال: " بَيْنَما نَحْنُ جُلُوسٌ عِنْدَ رسُولِ الله صلى الله عليه وسلم إذْ طَلَعَ عَلَيْنَا رَجُلٌ شَدِيدُ بَياضِ الثِّيَابِ شَدِيدُ سَوَادِ الشَّعَرِ، لا يُرَى عليه أَثَرُ السَّفَرِ ولا يَعْرِفُهُ مِنَّا أَحَدٌ، حَتى جَلَسَ إلى النَّبِّي صلى الله عليه وسلم، فأسْنَدَ رُكْبَتَيْهِ إلى رُكْبَتَيْهِ ووَضَعَ كَفَّيْهِ على فَخِذَيْهِ، وقال: يا محمَّدُ أَخْبرني عَن الإسلامِ، فقالَ رسُولُ الله صلى الله عليه وسلم: الإسلامُ أَنْ تَشْهَدَ أَنْ لا إلهَ إلا اللهُ وأَنَّ محمَّداً رسولُ الله، وتُقِيمَ الصَّلاةَ، وتُؤتيَ الزَّكاةَ، وتَصُومَ رَمَضان، وتَحُجَّ الْبَيْتَ إن اسْتَطَعتَ إليه سَبيلاً. قالَ صَدَقْتَ. فَعَجِبْنا لهُ يَسْأَلُهُ ويُصَدِّقُهُ، قال : فَأَخْبرني عن الإيمان. قال: أَن تُؤمِنَ باللهِ، وملائِكَتِهِ وكُتُبِهِ، ورسُلِهِ، واليَوْمِ الآخِرِ، وتُؤمِنَ بالْقَدَرِ خَيْرِهِ وشَرِّهِ. قال صدقت. قال : فأخْبرني عَنِ الإحْسانِ. قال: أنْ تَعْبُدَ الله كَأَنَّكَ تَرَاهُ فإنْ لَمْ تَكُنْ تَرَاهُ فإنَّهُ يَرَاك. قال: فأَخبرني عَنِ السَّاعةِ، قال:ما المَسْؤولُ عنها بأَعْلَمَ من السَّائِلِ . قال: فأخبرني عَنْ أَمَارَتِها، قال: أن تَلِدَ الأمَةُ رَبَّتَها، وأَنْ تَرَى الحُفاةَ العُراةَ العالَةَ رِعاءَ الشَّاءِ يَتَطَاوَلُون في الْبُنْيانِ، ثُمَّ انْطَلَقَ، فَلَبثْتُ مَلِيّاً، ثُمَّ قال : يا عُمَرُ، أَتَدْرِي مَنِ

السَّائِلُ؟ قُلْتُ: اللهُ ورسُولُهُ أَعلَمُ . قال: فإِنَّهُ جِبْرِيلُ أَتاكُمْ يُعَلِّمُكُمْ دِينَكُمْ ". (رواه مسلم)

ዑመር ኢብን አል- ኸጣብ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦

''ከአላህ መልእክተኛ ጋር ተቀምጠን እያለ ልብሱ በጣም የነጸና ጸጉሩ በጣም የጠቆረ አንድ ሰው መጣ። የጉዞ ምልክት አይታይበትም። ከመካከላችንም የሚያውቀው ሰው የለም። ከነቢዩ አጠገብ ተቀመጠ። ጉልበቶቹን ወደ ጉልበቶቻቸው አስጠጋ። መዳፎቹን ከጭኖቹ ላይ አኖረ። 'ሙሐመድ ሆይ! ስለ ኢስላም ንገረኝ?' ሲልም ጠየቀ። የአላህ መልእክተኛም 'ኢስላም ከአላህ ሌላ አምልኮ የሚገባው አምላክ እንደሌለ እና ሙሐመድ መልእክተኛው መሆናቸውን መመስከርህ፣ ሶላትን ደንቡን አሟልተህ መስገድህ፣ ዘካ መስጠትህ፣ ረመዷን መጾምህና የአላህንም ቤት ወደርሱ የመጓዝ አቅም ካለህ ሐጅ ማድረግህ ናቸው' አሉት። 'እውነት ብለሃል' አላቸው። በድርጊቱ ተገረምን። ይጠይቃቸዋል፣ እውነት ብለሃል ይላቸዋልም። 'ስለ ኢማን ንገረኝ?' ሲልም ጠየቃቸው። 'በአላህ፣ በመላእክት፣ በመጽሐፍት፣ በመልእክተኞች፣ በመጨረሻው ቀንና በቀደር ደግም ይሁን ክፉ ማመንህ ነው' በማለት መለሱለት። 'እውነት ብለሃል' አላቸው። 'ስለ ኢሕሳን ንገረኝ?' በማለትም ጠየቃቸው። 'አላህን እንደምታየው አድርገህ ማምለክህ ነው። አንተ ባታየውም እርሱ

ያይሐል' አሉት። 'ስለ ጊዜዋ (ስለ ትንሳኤ) ንገረኝ?' አላቸው። 'ተጠያቂው ከጠያቂው የበለጠ ስለ እርሷ አዋቂ አይደለም' አሉት። 'ስለ ምልከቶቿ ንገረኝ?' አላቸው። 'ባዶ እግራቸውን እና እርቃን የሆኑ ድሃ ፍየል ጠባቂዎች በሕንጻ ግንባታ ሲፎካከሩ ማየትህ ነው' አሉት። ከዚያም ሄደ። ጥቂት ጊዜ ቆየን። ነቢዩም 'ዑመር ሆይ! ይህ ጠያቂ ማን እንደሆነ ታውቃለህ?' አሉኝ። 'አላህና መልእክተኛው ያውቃሉ' አልኳቸው። 'ጅብሪል ነው። ሐይማኖታችሁን ሊያስተምራችሁ ወደናንተ ዘንድ መጣ'።'' (ሙስሊም ዘግበውታል)

የሐዲሱ ከብደትና ጠቀሜታ

ኢብን ደቂቅ አል ዒዲ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡-

''ይህ ሐዲስ ግልጽም ስውርም የሆኑ ስራዎችን መሠረቶች ያካተተ ታላቅ ሐዲስ ነው። የሸሪዓ እውቀቶች ሁሉ ወደርሱ የሚያደርሱ፣ የርሱ ምንዛሬዎች ናቸው። የሱንናን እውቀት ሁሉ ሰብስቦ ይዟል። ለሱንና እውቀት ልከ እንደ እናት ማለት ነው። የፋቲሐ ምእራፍ የቁርአንን ዓይነተኛ መልእክቶች ሁሉ የያዘች በመሆኗ 'የቁርአን እናት' እንደተሰኘችው ሁሉ ይህም ሐዲስ የሌሎች ሐዲሶች መልእክቶች ሁሉ አስኳል ከመሆኑ አኳያ 'የሱንና እናት' ሊሰኝ ይችላል።''

የቃላት ትርጉም

መዳፎቹን በጉልበቶቹ ላይ አኖረ፡- ከራሱ ጉልበቶች ላይ በማኖር ስርዓት ያለው አቀማመጥ ተቀመጠ። በነሳኢ ዘገባ መሠረት ደግሞ *"እጆቹን ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጉልበቶች ላይ አሰቀመጠ። "* የሚል ተወስቷል። ግና የመጀመሪየው ዘገባ የተሻለ ጥራት ያለው ነው።

በድርጊቱ ተገረምን። ይጠይቃል፣ 'እውነት ተናገርክ' ሲልም ይደመድማል፡- የአዋቂ ዓይነት ጥያቄ እየጠየቀ *"እውነት ብለሐል"* በማለት መልሱን ያጸድቃል። ወይም ጥያቄው አላዋቂ ያስመስለዋል። መልሶቹን ማጽደቁ ደግሞ አዋቂነቱን ያመለክታል።

በአላህ ማመንህ፡- ኢማን በቋንቋ ደረጃ ልቦና አንድን ነገር በማያጠራጥር ሁኔታ መቀበሉን አመልካች ሲሆን፣ በሸሪዓው ደግሞ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ያመጡትን መልእክት ሙሉ በሙሉ መቀበል ነው።

የቂያማ ምልክቶች፡- ቂያማ ከመከሰቷ በፊት ቀድመው የሚታዩ ምልክቶች ናቸው።

ባሪያ ጌታዋን ትወልዳለች፡- ትርጉሙም ቂያማ ሲቃረብ ከእንስት ባሪያ የመውለድ ልምድ ይበዛል። ልጆቹ ልክ እንደ አባቶቻቸው ነጻ

ሰዎች ስለሚሆኑ የእናቶቻቸው ጌቶች (ባለቤቶች) ይሆናሉ። በሕግ ደረጃ የአባት ባሪያ ባለቤትነቱ ወደ ልጅ ይሸጋገራል። ከዚህ አኳያ ልጇ ጌታዋ ይሆናል።

ጥቂት ጊዜ ቆየሁ፡- በሌላ ዘገባ እንደተወሳው ለሦስት ቀናት ያህል ከነቢዩ ርቄ ቆይቼ አገኘኋቸው።

አጠቃላይ መልእክት

ኢስላም ምንድን ነው?፡- ኢስላም ማለት በቋንቋ ደረጃ ለአላህ መታዘዝ እና እጅ መስጠት ማለት ነው። በሸሪዓው ትርጉሙ መሠረት ደግሞ ባአምስት መሠረቶች ላይ የታነጸ ሐይማኖት ነው። እነርሱም ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለ እና ሙሐመድም (ሰ.ዐ.ወ) መልእክተኛው መሆናቸውን መመስከር፣ ሶላትን ደንቡን አሟልቶ መስገድ፣ ዘካ መስጠት፣ የረመዷንን ወር መጾም፣ እንዲሁም አቅሙ ላለውና መጓጓዣና ስንቅ፣ እንዲሁም ለሐጅ ደርሶ እስኪመለስ የቤተሰቡን ቀለብ የሚችል ሰው በእድሜ ልክ አንድ ጊዜ የአላህን ቤት መሐጀጅ ናቸው።

ኢማን ምንድን ነው?፡- ኢማን በቋንቋ ደረጃ አንድን ነገር እውነት ብሎ መቀበል ሲሆን፣ በሸሪዓው አተረጓጎም መሠረት የሚከተሉትን ነጥቦች ያጠቃልላል። የአላህን ሕልውና አንድነት እና አጋር የሌለው መሆኑን ማመን፣ መላኢካ የሚባሉ፣ የአላህ የተላቁ ባሮች የሆኑ፣ የታዘዙትን ያለ ተቃውሞ የሚፈጽሙ፣ ከብርሃን የተፈጠሩ፣

የማይበሉ፣ ጾታ የሌላቸው፣ የማይራቡ፣ ቁጥራቸውን ከአላህ ውጭ ሌላ ማንም የማያውቃቸው የአላህ ፍጡራን እንዳሉ ማመን፤ ከአላህ በተወረዱ መለኮታዊ መጽሐፍት ማመንና ሳይበረዙና ሳይከለሱ በፊት የአላህ ሸሪዓዎች እንደነበሩ መቀበል፤ አላህ የሰው ልጆችን ወደ ቅን ጎዳና ለመምራት በመረጣቸውና መለኮታዊ መጽሐፍትን ባወረደላቸው የአላህ መልእክተኞች ሁሉ ማመን፤ እንዲሁም መልእክተኞች ከሐጢአት የተጠበቁ ሰዎች መሆናቸውን ማመን። በመጭው ዓለም መኖር፣ አላህ ሰዎችን ከመቃብር ለማስነሳት በዚህች ዓለም የሰሩትን ስራ እንደሚመረምር፣ መርምሮም መልካም ከሆነ እንደሚመነዳቸው፣ ክፉ ከሆነም እንደሚቀጣቸው ማመን፤ በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ የሚከሰት ማናቸውም ነገር በአላህ ውሳኔና ፈቃድ፣ እንዲሁም እርሱ ለሚያውቀው ጥበብ እንደሚከሰት ማመን፤ የእምነት መሠረቶች እነዚህ ናቸው። በነርሱ ያመነ ዳነ። ስኬታማም ሆነ። ያስተባበላቸው መንገድ ሳተ። ከሰረም።

ኢሕሳን ምንድን ነው?፡- አላህን እንደምታየው አድርገህ ማምለክህ፣ ማለትም አላህን በፍጹም ቅንነትና ታማኝነት (ኢኽላስ) በተሟላ አኳኋን (ኢትቃን) እንደምታየው አድርገህ ማምለክህ ነው። ይህን ባትችል እንኳ እርሱ ካንተ የሚመነጩ ኢምንትም ይሁኑ ትልቅ ነገሮች ሁሉ እንደሚያይ ማስታወስ ይገባሐል። ሙስሊም ባሰፈሩት ዘገባ፡- "አላህን እንደምታየው አድርገህ መፍራትህ ነው" የሚል ቃል ሰፍሯል።

ቂያማና ምልክቶቿ፡- ቂያማ የምትከሰትበትን ትክክለኛ ጊዜ ከአላህ ውጭ የሚያውቅ የለም። ከፍጡራኑ ለአንዱም፣ ለመልእኩም ይሁን ለመልእክተኛው አላካፈለም። ለዚህም ነው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጅብሪልን፡- *"ተጠያቂው ከጠያቂው የተሻለ እውቀት የለውም።"* ያሉት። ይህም ሆኖ ቂያማ ከመከሰቷ በፊት እውን የሚሆኑ አንዳንድ ምልክቶችን ነግረውታል።

1. የዘመን መበላሸት፣ የስነ ምግባር መዳከም፣ ብዙዎች ልጆች ወላጆቻቸውን ያንገላታሉ። ይቃረኗቸዋል። ከነርሱ ጋር ያላቸው ግንኙነትም ጌታ ከባሪያው ጋር ያለው ዓይነት ይሆናል።

2. ነገሮች የተገላቢጦሽ ይሆናሉ። አጅንዳዎች ይደበላለቃሉ። በመሆኑም ርካሽና ወራዳ ሰዎች የሕዝቦች መሪ ይሆናሉ። ኃላፊነቶች ተገቢ ላልሆኑ ሰዎች ይሰጣሉ። በሰዎች እጅ ገንዘብ ይበዛል። አባካኝነትም ይበረክታል። ሰዎች በሚገነቧቸው ሕንጻዎች ርዝመት፣ ባሏቸው ቁሳቁሶች ይፎካከራሉ። በድህነት እና በችግር ውስጥ በሌሎች ምጽዋትና ድጋፍ ይኖሩ የነበሩ ዘላኖች፣ ፍየል ጠባቂዎችና መሰል ዝቅተኛ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሰዎች የበላይ፣ የጉዳዮቻቸው ተቆጣጣሪዎች ይሆናሉ።

ከሐዲሱ የሚቀሰሙ ትምህርቶች

ስለ እውቀት መጠየቅ፡- ሙስሊም ለዱንያው ወይም ለአኼራው የሚጠቅመውን ብቻ ይጠይቃል። ጥቅም አልባ የሆኑ ነገሮችን ከመጠየቅም ይታቀባል። ከአንድ የትምህርት ስብስብ ላይ የተገኘና ታዳሚዎች ሊያውቁት ይገባል የሚለው ጉዳይ ያለው፣ ያን ጉዳይ ከመካከላቸው አንዱ ካልጠየቀ፣ እርሱ ቢያውቀው እንኳ- በመጠየቅ በመልሱ ተሳታፊዎች እንዲጠቀሙ ሊያደርግ ይገባል። የማያውቀውን ነገር የተጠየቀ "አላውቀውም" በማለት የመመለስ ግዴታ አለበት። ይህን ማድረጉ ጥንቁቅነቱን፣ አላህን ፈሪነቱንና አዋቂነቱን ያመለክታል።

ጥያቄና መልስ፡- ከጥንት እስከ ዛሬ ውጤታማ የማስተማር ስልት ነው። በነቢዩ ሐዲሶች ውስጥ በርካታ ጊዜ ጥቅም ላይ ሲውል ተስተውሏል። ምክንያቱም ጥያቄ የአድማጮችን ስሜት ይስባል። ትክክለኛውን መልስ ለመስማትም አእምሯዊና ስነ ልቦናዊ ዝግጅት እንዲያደርጉ ይረዳል።

አለባበስንና ገጽታን ማሳመር፡- ወደ መስጊድና ዒልም (እውቀት) ወደሚሰጥበት ቦታ ሲሄዱ አለባበስን ማሳመር፣ የአቀማመጥ ስርዓትን መጠበቅ፣ ለመምህርና ለተማሪ ስርዓታማ ግኙነት መገዛት ተገቢ ነው።



የእስልምና መሠረቶችና ታላላቅ ምሰሶዎች

عَنْ أَبِي عَبْدِ الرَّحْمَنِ عَبْدِ اللَّهِ بْنِ عُمَرَ بْنِ الْخَطَّابِ رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُمَا قَالَ: سَمِعْتُ رَسُولَ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم يَقُولُ: " بُنِيَ الْإِسْلَامُ عَلَى خَمْسٍ: شَهَادَةِ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللَّهُ وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللَّهِ، وَإِقَامِ الصَّلَاةِ، وَإِيتَاءِ الزَّكَاةِ، وَحَجِّ الْبَيْتِ، وَصَوْمِ رَمَضَانَ". رَوَاهُ الْبُخَارِيُّ وَمُسْلِمٌ.

የአላህ መልእክተኛ ተከታዩን ሲናገሩ ሰምቻለሁ በማለት አብደላህ ቢን ዑመር ቢን አልኸጧብ አስተላልፈዋል፡-

“እስልምና ከአምስት መሠረቶች ላይ ታንጿል:: እነርሱም ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም መልእክተኛው መሆናቸውን መመስከር፣ ሶላትን ደንቡን ጠብቆ መስገድ፣ ዘካ መስጠት፣ የአላህን ቤት መሐጀድና የረመዳንን ወር መጾም ናቸው:: ” (ቡኻሪና ሙስሊም)

አጠቃላይ መልእክት

የእስልምና ግንብ፡- የአላህ መልእክተኛ ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም እርሳቸው ያመጡትንና ሰዎች ከክህደት ከልል ወጥተው፣ ከእሳት ርቀው፣ ለጀነት ተገቢ የሚሆኑበትን መለኮታዊ መልእክት

በጽኑ መሠረት ላይ በታነጸ ግንብ መስለውታል። ይህ ግንብ የቆመባቸውን መሠረቶችንም ዘርዝረዋል፡-

ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የርሱ መልእክተኛ መሆናቸውን መመስከር። ትርጉሙም የአላህን ሕልውናና አንድነት ማጽደቅ፣ እንዲሁም የነቢዩ ሙሐመድን ነብይነት እና ተልእኮ መቀበል ነው። ይህ መሠረት ለሌሎች የእስልምና ምሰሶዎች እንደ መሠረት የሚቆጠር ነው። የአላህ መልእክተኛ ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፡-

“ላኢላሐ ኢለላህ ያለ ጀንት ገባ።” (በዛር የዘገቡት ሶሂህ ሐዲስ)

ሶላትን ደንቡን አሟልቶ መስገድ፡- ትርጉሙ ሶላትን ደንቡንና ወቅቱን ጠብቆ፣ መስፈርቶችን አሟልቶ፣ ግዴታዎችን፣ ሱንናዎችን እና አደቦችን በትክክል አከናውኖ፣ በስብእና ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ ሊያሳድርና ከእኩይ ድርጊቶች እንዲርቅ ሊያደርግ በሚችልበት አኳኋን መስገድ ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿اتْلُ مَا أُوحِيَ إِلَيْكَ مِنَ الْكِتَابِ وَأَقِمِ الصَّلَاةَ ۖ إِنَّ الصَّلَاةَ تَنْهَىٰ عَنِ الْفَحْشَاءِ وَالْمُنكَرِ ۗ وَلَذِكْرُ اللَّهِ أَكْبَرُ ۗ وَاللَّهُ يَعْلَمُ مَا تَصْنَعُونَ﴾

“ከመጽሐፍ ወደ አንተ የተወረደውን አንብብ። ሶላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ። ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ

ትከለክላለችና፡፡ አላህንም ማውሳት ከሁሉ ነገር በላጭ ነው፤ አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ያውቃል፡፡" (አል አንከቡት 45)

ዘካ መስጠት፡- የግዴታ መጠን (ኒሷብ) የደረሰ እና ዘካ ለመክፈል መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች ያሟላ ገንዘብ ያለው ሰው ለድሆችና ለሌሎች ተገቢ የሕብረተሰብ ክፍሎች ከዚያ ከገንዘቡ የተወሰነ መጠን መስጠቱ ዘካ ይባላል፡፡

ሐጅ፡– በሐጅ ወራት፣ ማለትም በሸዋል፣ በዙል ቂእዳ፣ እና በዙል ሂጃ የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ውስጥ የአላህን ቤት ለመጎብኘት በመሻት ተጉዞ የአላህ መልእክተኛ ያብራሩትን ስርዓት መፈጸም ሐጅ ይባላል፡፡ ሐጅ ለግለሰብም ሆነ ለማሕበረሰብ በርካታ ፋይዳዎችን የሚያስገኝ፣ በአካልና በገንዘብ የሚፈጸም ኢባዳ ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ በተለያዩ ሐገሮች ውስጥ የሚኖሩ ሙስሊሞች እንዲገናኙ ጥሩ አጋጣሚ የሚፈጥር ታላቅ አለማቀፋዊ ኢስላማዊ ጉባኤ ነው፡፡ ይህም ስለሆነ የሐጅ ምንዳ ትልቅ ሆኗል፡፡ የአላህ መልእክተኛ ስለላሁ ዓለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፡-

"ተቀባይነት ያገኘ ሐጅ ከጀነት ውጭ ሌላ ምንዳ የለውም፡፡" (ቡኻሪና ሙስሊም)

ሐጅ ግዴታ የተደረገው በ6ኛው ዓመተ ሂጅራ በተከታዩ የቁርአን መልእክት ነው፡-

﴿فِيهِ آيَاتٌ بَيِّنَاتٌ مَّقَامُ إِبْرَاهِيمَ ۖ وَمَن دَخَلَهُ كَانَ آمِنًا ۗ وَلِلَّهِ عَلَى النَّاسِ حِجُّ الْبَيْتِ مَنِ اسْتَطَاعَ إِلَيْهِ سَبِيلًا ۚ وَمَن كَفَرَ فَإِنَّ اللَّهَ غَنِيٌّ عَنِ الْعَالَمِينَ﴾ آل عمران ٩٧

“በውስጡ ግልጽ የኾኑ ተዓምራቶች የኢብራሒምም መቆሚያ አልለ። ወደ ውስጡ የገባ ሰው ጸጥተኛ ይኾናል። ለአላህም በሰዎች ላይ ወደርሱ መኼድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው። የካደም ሰው አላህ ከዓለማት ሁሉ የተብቃቃ ነው።” (አሊ ዒምራን 97)

ረመዷን መጾም፡- የረመዷን ጾም በሁለተኛው ዓመተ ሂጅራ በተከታዩ የቁርአን መልእክት ግዴታ ተደረገ፡-

﴿شَهْرُ رَمَضَانَ الَّذِي أُنزِلَ فِيهِ الْقُرْآنُ هُدًى لِّلنَّاسِ وَبَيِّنَاتٍ مِّنَ الْهُدَىٰ وَالْفُرْقَانِ ۚ فَمَن شَهِدَ مِنكُمُ الشَّهْرَ فَلْيَصُمْهُ ۖ وَمَن كَانَ مَرِيضًا أَوْ عَلَىٰ سَفَرٍ فَعِدَّةٌ مِّنْ أَيَّامٍ أُخَرَ ۗ يُرِيدُ اللَّهُ بِكُمُ الْيُسْرَ وَلَا يُرِيدُ بِكُمُ الْعُسْرَ وَلِتُكْمِلُوا الْعِدَّةَ وَلِتُكَبِّرُوا اللَّهَ عَلَىٰ مَا هَدَاكُمْ وَلَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ﴾

“(እንድትጾሙ የተጻፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከቅን መንገድና (እውነትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች (አንቀጾች) ሲኾን ቁርአን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው። ከእናንተም ወሩን ያገኘ ሰው ይጹመው። በሽተኛ ወይም በጉዞ ላይ የኾነም ሰው ከሌሎች ቀኖች ቁጥሮችን (በልኩ) መጾም አለበት። አላህ በእናንተ

ገሩን (ነገር) ይሻል፡፡ በእናንተም ችግሩን አይሻም፡፡ ቁጥሮችንም ልትሞሉ አላህንም ቅኑን መንገድ ስለመራችሁ ታከብሩትና ታመሰግኑት ዘንድ (ይሀን ደነገግንላችሁ) ፡፡" (አል በቀራህ 185)

ጾም ነፍስን የሚያጸዳ፣ መንፈስን የሚያመጥቅ፣ ለአካላዊ ጤንነትም ጠቃሚ የሆነ ኢባዳ ነው፡፡ የአላህን ትእዛዝ ለመፈጸም ሲል በትክክል ያከናወነው ወንጀሉ ይማርና ጀነትም ይገባ ዘንድ ሰበብ ይሆንለታል፡

በዚህ ሐዲስ የተወሱት የእስልምና ዋናዋና መሠረቶች ሲሆኑ፣ ማሟያዎች ለምሳሌ ሱናዎችና የሚወደዱ ነገሮች የግንቡ ማስዋቢያዎች ናቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛ ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም እንዲህ ማለታቸው በሐዲስ ተመልክቷል፡-

"ኢማን ከሰባ በላይ ቅርንጫፎች አሉት፡፡ ከፍተኛ ላኢላሐ ኢለላህ የሚለው ሲሆን ዝቅተኛው ከመንገድ ላይ እንቅፋትን ማስወገድ ነው፡፡"

የኢባዳ ዓላማ፡- ኢስላም ከኢባዳ የሚፈልገው ላያዊ ገጽታውን ወይም ቅርጹን ሳይሆን ዓላማውን እና አስኳሉን ነው፡፡ ሶላት ከመጥፎ ነገሮች ካላቀበች፣ ጾምም ባለቤቱን ከውድቅ ንግግርና ስራ ካልታደገ፣ ሐጅና ዘካም ለይዩልኝና ይስሙልኝ ከተፈጸሙ ፋይዳ የላቸውም፡፡ ይህ ማለት ግን እነዚህን ኢባዳዎች ፍሪያቸው ካልታየ

አናከናውናቸው ማለት ሳይሆን በኢኽላስና ዓላማቸውን በሚያሳካ አኳኋን ለመፈጸም መትጋት እንዳለብን ለማሳየት ነው፡፡

የኢማን ዘርፎች፡- ኢስላም ማለት በሐዲሱ ውስጥ የተወሱት ነገሮች ብቻ አይደሉም፡፡ ሐዲሱ በነዚህ የተወሰነው የተለየ ክብደትና ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ከንውኖች ስለሆኑ ነው፡፡ እስልምና ከነዚህ ሌላ በርካታ በጎ ምግባራትን አካቷል፡፡ የአላህ መልእክተኛ ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፡-

“ኢማን ከሰባ በላይ ዘርፎች አሉት፡፡” (ቡኻሪና ሙስሊም)

የሐዲሱ ጠቀሜታ፡- ኢስላም እምነት ብቻ ሳይሆን ተግባርም ጭምር መሆኑን ይህ ሐዲስ ያስተምራል፡፡ ስራ ያለ እምነት ጠቀሜታ እንደሌለው ሁሉ እምነትም ያለ ስራ ሕልውና የለውም፡፡

የኢማን ትርጉምና አስፈላጊነት:ምሰሶዎች

የኢማን ትርጉም

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿آمَنَ الرَّسُولُ بِمَا أُنزِلَ إِلَيْهِ مِن رَّبِّهِ وَالْمُؤْمِنُونَ كُلٌّ آمَنَ بِاللَّهِ وَمَلَائِكَتِهِ وَكُتُبِهِ وَرُسُلِهِ لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِّن رُّسُلِهِ وَقَالُوا سَمِعْنَا وَأَطَعْنَا غُفْرَانَكَ رَبَّنَا وَإِلَيْكَ الْمَصِيرُ ﴾ البقرة ٢٨٥

‘‘መልክተኛው ከጌታው ወደ ርሱ በተወረደው አመነ። ምእምኖቹም (እንደዚሁ)። ሁሉም በአላህ፣ በመላዕክቱም፣ በመጻሕፍቱም፣ በመልክተኞቹም ከመልክተኞቹ ‘በአንድም መካከል አንለይም’ (የሚሉ ሲኾኑ) አመኑ። ‘ሰማን፤ ታዘዝንም። ጌታችን ሆይ! ምሕረትህን (እንሻለን) ። መመለሻም ወዳንተ ብቻ ነው’ አሉም።’’ (አል-በቀራህ 2፤ 285)

﴿يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا آمِنُوا بِاللَّهِ وَرَسُولِهِ وَالْكِتَابِ الَّذِي نَزَّلَ عَلَىٰ رَسُولِهِ وَالْكِتَابِ الَّذِي أَنزَلَ مِن قَبْلُ وَمَن يَكْفُرْ بِاللَّهِ وَمَلَائِكَتِهِ وَكُتُبِهِ وَرُسُلِهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ فَقَدْ ضَلَّ ضَلَالًا بَعِيدًا﴾ النساء ١٣٦

‘‘እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልክተኛው በዚያም በመልክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ በዚያም ከበፊቱ

ባወረደው መጽሐፍ እመኑ። በአላህና በመላእክቱም፣ በመጽሐፎቹም፣ በመልክተኞቹም፣ በመጨረሻውም ቀን፣ የካደ ሰው (ከእውነት) የራቀን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ።" (አል-ኒሳእ 4፤ 136)

እውቅ በሆነው የጅብሪል (ዐ.ሰ) ሐዲስ ውስጥ ጅብሪል በሰው ተመስሎ ወደነቢዩ በመምጣት ስለ ኢስላም፣ ኢማንና ኢሕሳን በጠየቃቸው ጊዜ ኢማንን እንዲህ አብራርተውለታል፡-

(أن تؤمن بالله وملائكته وكتبه ورسله واليوم الآخر وتؤمن بالقدر خيره وشره)

"በአላህ፣ በመላኢኮች፣ በመጽሐፎች፣ በመልእክተኞች፣ በመጨረሻው ቀንና በቀደ ቀደር- በጎም ሆነ ክፉ- ማመንህ ነው። " (ሙስሊም)

ከላይ ከተወሱት የቁርአን አናቅጽና የሐዲስ ዘገባ እንደምንረዳው ኢማን ስድስት ጽንሰ ሐሳቦችን አካትቷል። እነርሱም

1. **አንደኛ፡-** አላህን፣ የላቁ ስሞቹንና ባህሪያቱን፣ የሕልውናውን መርሆዎች፣ የልዕልናውን መገለጫዎች ማወቅ፤

2. **ሁለተኛ**፡- በመላኢኮች መኖር ማመን፡ ከብርሃን የተፈጠሩ ንፁሃን ከወንጀል የራቁ ለአላህ ፍፁም ታዛዦች መሆናቸዉን ማመን።

3. **ሦስተኛ**፡- የእውነትንና የሐሰትን፣ የበጎና የክፋትን፣ የሐላልና የሐራምን፣ የጥሩና የመጥፎን ወሰኖች ለማበጀት አላህ ያወረዳቸውን መጽሐፍት ማወቅ፤

4. **አራተኛ**፡- የመቀናት ተምሳሌት ይሆኑ ዘንድና የሰው ልጆችን ወደ ቅን ጎዳና እንዲመሩ አላህ የመረጣቸውን ነብያትና መልእክተኞች ማወቅ፤

5. **አምስተኛ**፡- *መጭው ዓለም፣ ከሞት መቀስቀስ፣ ምንዳ ወይም ቅጣት፣ ጀነት ወይም እሳት የመኖሩን እውነታ* ማወቅ፤

6. **ስድስተኛ**፡- ዩኒቨርሱ የሚመራበት የቀዷ ቀደር ስርዓት መኖሩን ማወቅ። (*ሸይኽ ሰይድ ሳቢቅ፣ አልዓቃኢዱ-ል-ኢስላሚያህ*)

ኢማን ማለት እውቀት ወይም የልቦና እምነት ብቻ ሳይሆን የአንደበት ምስክርነትንና ተግባርን ያካትታል። ይህን ሁለንተናዊ የኢማን ይዘት የሚያብራሩ የቁርአን አናቅጽና የሐዲስ ዘገባዎች በርካታ ናቸው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ الَّذِينَ آمَنُوا بِاللَّهِ وَرَسُولِهِ ثُمَّ لَمْ يَرْتَابُوا وَجَاهَدُوا بِأَمْوَالِهِمْ وَأَنفُسِهِمْ فِي سَبِيلِ اللَّهِ أُولَٰئِكَ هُمُ الصَّادِقُونَ ﴾ الحجرات ١٥

"(እውነተኞዎቹ) ምእምናን እነዚያ በአላህና በመልእክተኛው ያመኑት ከዚያም ያልተጠራጠሩት በገንዘቦቻቸውና በነፍሶ ቻቸውም በአላህ መንገድ የታገሉት ብቻ ናቸው። እነዚያ እነሱ እውነተኞቹ ናቸው።" (አል-ሁጁራት 49፤ 15)

﴿إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ الَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ اللَّهُ وَجِلَتْ قُلُوبُهُمْ وَإِذَا تُلِيَتْ عَلَيْهِمْ آيَاتُهُ زَادَتْهُمْ إِيمَانًا وَعَلَىٰ رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ﴾ الأنفال ٢

"ፍጹም ምእምናን እነዚያ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩት፣ በነሱም ላይ አንቀጾቹን በተነበቡ ጊዜ እምነትን የሚጨምሩላቸው፣ በጌታቸውም ላይ ብቻ የሚመኩት ናቸው።" (አል-አንፋል 8፤ 2)

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ!" ተብሎ ሙእሚን የተጠራባቸው እና "ሙእሚን ማለት" በሚል ቃል ተወጥነው የኢማንን መስፈርት የሚያብራሩ የቁርአን መልእክቶች ብዙዎች ሲሆኑ እነርሱን ማስተንተንና ማስተዋል ተገቢ ነው። ይህን የኢማን ይዘት ከሚያብራሩ ሐዲሶች መካከል ኢብን ዑመር (ረ.ዐ) ያስተላለፉት ይገኝበታል፣ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

من سرته حسناته وساءته سيئاته فهو مؤمن

‘‘ደግ ስራው ያስደሰተውና መጥፎ ስራው ያስከፋው ሰው ሙእሚን ነው።’’ (አህመድ ዘግበውታል)

ኡባደት ኢቢን ሷሚት (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

(إن أفضل الإيمان أن تعلم ان الله معك حيثما كنت)

‘‘በላጩ ኢማን የትም ቦታ ብትሆን አላህ ካንተ ጋር እንዳለ ማወቅህ ነው።’’ (ጦበራኒ ዘግበውታል)

ዐብደላህ ኢቢን ዑመር (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

(الحياء شعبة من الإيمان)

‘‘ሐያእ የኢማን ዘርፍ ነው።’’ (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

አነስ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

(لا يؤمن أحدكم حتى يحب لأخيه ما يحب لنفسه)

“ከናንተ አንዳችሁ ለራሱ የሚወደውን ለወንድሙ እስካልወደደ ድረስ አላመነም።” (ቡኻሪና ሙስሊም)

አቡ ሹረይሕ አል ካዕቢ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ነቢዩ ﷺ :-

(والله لا يؤمن والله لا يؤمن والله لا يؤمن . قالوا : من ذلك يا رسول الله صلى الله عليه وسلم؟ قال : من لا يأمن جاره بوائقه)

“በአላህ እምላለሁ አለመነም።” በማለት ሦስት ጊዜ ተናገሩ። “ይህ ሰው ማን ነው?” ተብለው ሲጠየቁ፡- “ጎረቤቱ ተንኮሉን የማያምነው ሰው” በማለት መለሱ። (ቡኻሪ ዘግበውታል)

ቁርኣንና ሐዲስ ያስተማሩት ኢማን፣ መንገድ የሳቱ ሐይማኖቶች፤ “እውር ሆነህ እመን”፣ “አእምሮህን ዝጋና ተከተለኝ” እንደሚሉት ዓይነት አእምሯችንን ቆልፈን የምንቀበለው እውር እምነት አይደለም። ይልቁንም ግዙፉን ዩኒቨርስ እና በውስጡ ያካተታቸውን ወደ እምነት የሚጠሩ ጥበቦች በጥልቀት ከማጤንና ከማስተንተን የሚመነጭ ነው።

የኢማን አስፈላጊነት

- **አላህን ማወቅ፡-** በርካታ በጎ ስሜቶችን ያሰርጻል። ሕሊናን ለደግ ስራ ያነቃቃል። ራስን የመቆጣጠርን ክህሎት ያጎናጽፋል። ለላቁ ዓላማዎች ያነሳሳል። ከአጓጉል ድርጊቶችም ያርቃል።
- **መላኢኮችን ማወቅ፡-** ከነርሱ ጋር ለመመሳሰል መጣርን፣ ለሐቅና ለሰናይ መተባበርን ይጋብዛል። ጥንቁቅና ንቁም ያደርጋል። መላኢኮች ካጠገቡ እንዳሉ የታሰበው ሰው መልካም ነገር እንጅ ከርሱ አይመነጭም። ለላቀ ዓላማ እንጅ አይንቀሳቀስም።
- **መለኮታዊ መጽሐፍትን ማወቅ፡-** የሰው ልጅ ውጫዊና ውስጣዊ ምሉእነትን ይጎናጽፍ ዘንድ እንዲጓዝበት አላህ ያሰመረለትን ቅን ጎዳና ማወቅ ነው።
- **መልእክተኞችን ማወቅ፡-** ፈለጋቸውን መከተል፣ ባህሪያቸውን መውረስ፣ እነርሱን አርአያ (Role Model/ ቁድዋ) ማድረግ ማለት ነው። ምክንያቱም እነርሱ የመልካም እሴትና አላህ ለሰው ልጅ ያለመለት ጻእድ ሕይወት ተምሳሌቶች ናቸውና።
- **የመጭውን ዓለም ሕልውና ማወቅ፡-** በጎ ነገር ለመስራት እና ከክፉት ለመታቀብ ግፊት በማሳደር ወደር አይገኝለትም።

- **በቀጁ ቀደር ማመን**፡- ችግሮችንና እንቅፋቶችን ለማለፍ የሚያስችል ወሰን አልባ ጉልበት ይለግሳል። ይህ እምነት በልቦና ውስጥ ካለና ከሰረጸ ግዙፍ ክስተቶች ሁሉ ኢምንት ሆነው ይታያሉ።

ከላይ የሰፈረው ገለጻ በጉልህ እንደሚያመለክተው ኢማን ዓላማው ስብእናን ማስተካከል፣ ነፍስን ማጽዳትና ፊትን ወደ ላቀ አርአያ ማዞር ነው። ይህ ዓይነቱ ኢማን ለግለሰቦች ሕይወት ነው። እርሱ ካለ መልካም ሕይወት ይኖራሉ። እርሱ ከሌለ ደግሞ መንፈሳቸው ይሞታል። ኢማን መንገድ አመላካች ብርሃን ሲሆን፣ ያለርሱ የሰው ልጅ እውር ነው። መንገድ ስቶ በሕይወት ጥሻዎች ውስጥ ይወሸቃል፣ በጥመት ሸለቆዎች ውስጥ ይጠፋል፣

﴿أَوَمَن كَانَ مَيْتًا فَأَحْيَيْنَاهُ وَجَعَلْنَا لَهُ نُورًا يَمْشِي بِهِ فِي النَّاسِ كَمَن مَّثَلُهُ فِي الظُّلُمَاتِ لَيْسَ بِخَارِجٍ مِّنْهَا كَذَٰلِكَ زُيِّنَ لِلْكَافِرِينَ مَا كَانُوا يَعْمَلُونَ﴾ الأنعام ١٢٢

‘‘ሙት የነበረና ሕያው ያደረግነው ለእርሱም በሰዎች መካከል በእርሱ የሚኼድበትን ብርሃን ያደረግንለት ሰው በጨለማዎች ውስጥ ከርሷ የማይወጣ ኾኖ እንዳልለ ሰው ብጤ ነውን? እንደዚሁ ለከሓዲዎች ይሠሩት የነበሩት ነገር ተጌጠላቸው።’’ (አል-አንዓም 6፤ 122)

ይህም ብቻ አይደለም። ኢማን ማለት ከመላ የዩኒቨርሱ አካላት፣ ከአላህና እንዲሁም ዩኒቨርሱን ከሚገዛው ሕግና ስርዓት ጋር መገናኘት ማለት ነው። ከአላህ ጋር የተሳሰረ፣ በርሱ ያመነ፣ ትእዛዙን የተከተለ፣ ከዩኒቨርሱ ጋር በመገናኛ፣ በጎ ተጽእኖውን በማስተናገድና ተጽእኖ በማሳደር በዚህችም በቀጣዩም ዓለማት በደስታ ይኖራል።

﴿فَمَنِ اتَّبَعَ هُدَايَ فَلَا يَضِلُّ وَلَا يَشْقَىٰ﴾ طه ١٢٣

“መሪየን የተከተለ ኣይሳሳትም ኣይቸገርምም።” (ጧሃ 20፤ 123)

ሰውየው ከአላህ ጋር ካልተሳሰረ ከዩኒቨርሱ ጋር ያለው ግንኙነትም ይቋረጣል። ነፍሱም ለርሱ እና ከርሱ ለሚመነጩት ነሮች ሁሉ ባይተዋር ትሆናለች። ይህም ሲሆን በዚህችም በመጭውም ዓለም ደስታ ቢስ ይሆናል።

﴿وَمَنْ أَعْرَضَ عَن ذِكْرِي فَإِنَّ لَهُ مَعِيشَةً ضَنكًا وَنَحْشُرُهُ يَوْمَ الْقِيَامَةِ أَعْمَىٰ﴾ طه ١٢٤

“ከግሣጼዬም የዞረ ሰው ለእርሱ ጠባብ ኑሮ አለው። በትንሣኤም ቀን ዕውር ኾኖ እንቀሰቅሰዋለን።” (ጧሃ 20፤ 124)

የኢህሳን ትርጉም

አል-ኢህሳን ኢህሳን (ስምረት) ማለት: በልቦናህና በተግባርህ አላህን እንደምታየው አድርገህ ማምለክ ነው:: አንተ ባታየው እርሱ ያየሃልና! ይህንን በልቦና በማሳደር በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሱና (ፈለግ) መሠረት ሚባዳን መፈፀም ፈለጋቸውን አለመፃረር ኢህሳን ነው::

ነብዩ መሐመድ (ሰ. ዐ. ወ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ መልካም ስራ (ኢህሳን) ምንድን ነው ብሎ ለጠየቃቸው መልስ ሲመልሱ:

((الإحسان أن تعبد الله كأنك تراه، فإن لم تكن تراه فإنه يراك))

(አላህን እንደምታየው ሁነህ መገዛት ነው:: አንተ ባታየው እሱ ያይሃል) ብለዋል:: እሱም ከኢስላም ሃይማኖት ከሶስቱ ደረጃዎች ከፍተኛው ደረጃ ነው ::

የላኢላህ ኢለላህ ትርጉም እና መስፈርቶች

ከአላህ በስተቀር በሃቅ ሊመለክ የሚገባው አምላክ የለም፤ (ላኢላሃ ኢለላህ) የሚለው ቃል ያለአንዳች ጥርጥር የኢስላም ሃይማኖት ዋንኛው ምሰሶ ነው። ከዚህ ላኢላሃ ኢለላህ ከሚለው ቃል ጋር መሐመዱን ረሱሉላህ የሚለው ቃል ሲቆራኝ ከኢስላም መሰረቶች ውስጥ የመጀመርያው ይሆናል።

የላኢላሃ ኢለላህ አላማ ለመተግበር መሟላት የሚገባቸው ስምንቱ ቅድመ ሁኔታዎችን (ሹሩጥ) ዝርዝር:

1. የመሀይምነት ተፃራሪ የሆነው እውቀት

ይህም ማለት የዚህ ቃል መልዕክት እና ቃሉ ዉድቅ የሚያደርጋቸዉንና እና የሚያፀድቃቸውን ነገሮች ማወቅ ማለት ነው፡፡ ማለትም አላህ በእውነት ሊያመልኩት የሚገባ እና ብቻውን የሚመለክ አምላክ መሆኑን ከእርሱ ውጭ ያሉ ሁሉ አምልኮ የማይገባቸው ባጢል አማልክት መሆናቸውን ማወቅ ሲሆን ካለ እዉቀት የሚሰጥ ምስክርነት ተቀባይነት የለዉም። ለዚህም ማስረጃው ቀጣዩ የአላህ ቃል ነው፡፡

﴿إِلا مَن شَهِدَ بِالْحَقِّ وَهُمْ يَعْلَمُون﴾ [الزخرف:٨٦]

(እነዚያም ከአላህ ሌላ የሚያመልኳቸዉ እነሱ የሚያውቁ ሆነው በእውነትከመሰከሩት በስተቀር ምልጃን አይችሉም) (አል-ዙኽሩፍ 86)

2. የጥርጥር ተፃራሪ የሆነው እርግጠኝነት

ይህ መስፈርት የሚያመለክተው (ላ ኢላህ ኢለላህ) የሚለውን ምስክርነት ከልቡ በመቀበል አላህ ብቻውን የሚመለክ አምላክ መሆኑን እና ከእርሱ ውጭ ያሉ አማልክት በሙሉ ከንቱ መሆናቸውን በአንደበት እንደሚናገረው ሁሉ በልቡም ማረጋገጥ እንዳለበት ነው። እርግጥኝነት ከሌለ ጥርጥር ዉስጥ ነዉና እምነቱ ከመናፍቃን እምነት አይለይም። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ الَّذِينَ آمَنُوا بِاللَّهِ وَرَسُولِهِ ثُمَّ لَمْ يَرْتَابُوا وَجَاهَدُوا بِأَمْوَالِهِمْ وَأَنفُسِهِمْ فِي سَبِيلِ اللَّهِ ۚ أُولَٰئِكَ هُمُ الصَّادِقُونَ﴾ الحجرات ١٥

(እውነተኞዎቹ) ምእምናን እነዚያ በአላህና በመልእከተኛው ያመኑት ከዚያም ያልተጠራጠሩት በገንዘቦቻቸውና በነፍሶ ቻቸውም በአላህ መንገድ የታገሉት ብቻ ናቸው፡፡ እነዚያ እነሱ እውነተኞቹ ናቸው፡፡ (አል-ሑጁራት 15)

3. የማጋራት ተፃራሪ የሆነው ማጥራት (ኢኽላስ)

የላኢላህ ኢለላህን የምስክርነት ቃል የሰጠ ሰው ስራውን ከሽርክ ማጥራት አለበት፣ የሚያከናውናቸውን ተግባራቶችም ሆነ የሚናገራቸውን ንግግሮች በሙሉ ለአላህ ብቻ ብሎ መፈጸም አለበት። በዚህ የምስክርነት ቃል የዱንያ ጥቅማጥቅሞችንና ዝናን ከመከጀል ለይዩልኝ እና ይስሙልኝ ከመስራት መጥራት አለበት። ለዝና ወይም ለዱንያዊ ጥቅም ተብሎ የሚፈፀም ተግባር ከአላህ ጋር ሌሎችን በአምልኮ ማጋራት በመሆኑ ምንዳን አያስገኝም። የሚያስከትለውም ቅጣት ብርቱ ነው።

የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል ‹‹የቂያማ ዕለት የኔን ምልጃ በማግኘት ዕድለኛ የሚሆነው ከልቡ ጥርት አድርጎ ላ ኢላህ ኢለላህ ያለ ሰው ነው።›› ቡኻሪ ዘግበዉታል።

4. የውሸት ተፃራሪ የሆነው እውነተኛነት

ላ ኢላህ ኢለላህ ብሎ የሚመሰክረው ግለሰብ በልቡ የሚያምንበት እምነትም ሆነ በአንደበቱ የሚናገረው ንግግር እውነትን የተላበሰ መሆን አለበት። ይህ ካልሆነ ውሸትን የሚያራምድ አታላይ እንጂ እዉነተኛ መስካሪ አይሆንም። የአላህ መልእክተኛ (ﷺ) እንዲህ ይላሉ

<<ማንኛውም ከልቡ በእውነተኛነት በአላህ ብቸኛ አምላክነትና በሙሐመድ (ﷺ) መልዕክተኝነት የሚመሰክር ሰው አላህ ከእሳት እርም ይለዋል›› (ቡኻሪ ዘግበዉታል)

5. የመጥላት ተፃራሪ የሆነው መውደድ

ላ ኢላህ ኢለላህ ብሎ የሚመሰክረው ግለሰብ ይህ ምስክርነቱ ግዴታ የሚያደርጋ ቸውን ነገሮች ሁሉ መውደድ ይገባዋል። ወዶ እና ፈቅዶ ካልመሰከረ ተገዶ ነዉና ምስክርነቱ ተቀባይነት የለዉም። ላኢላህ ኢለላህ የሚለውን የምስክርነት ቃል ፣ አላህን እንዲሁም አላህን በብቸኝነት የሚያመልኩትን የተውሂድ ሰዎችን መውደድ ነው:: አላህ እንዲህ ይላል :-

﴿وَمِنَ النَّاسِ مَن يَتَّخِذُ مِن دُونِ اللَّهِ أَندَادًا يُحِبُّونَهُمْ كَحُبِّ اللَّهِ ۖ وَالَّذِينَ آمَنُوا أَشَدُّ حُبًّا لِّلَّهِ ۗ﴾ البقرة ١٦٥

(ከሰዎችም ከአላህ ሌላ ባለንጣዎችን (ጣዖታትን) አላህን እንደሚወዱ የሚወዷቸው ኾነው የሚይዙ አልሉ:: እነዚያ ያመኑትም አላህን በመውደድ (ከነርሱ) ይበልጥ የበረቱ ናቸው::) አል በቀራህ 165

6. የመተው ተፃራሪ የሆነው መታዘዝ

ይህ ማለት ‹‹ላ ኢላህ ኢለላህ›› የሚለው የምስክርነት ቃል ለሚያመላክታቸው ትዕዛዛትና ክልከላዎች ሙሉ ታዛዥ ተከታይና ተናናሽ መሆን ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿۞ وَمَن يُسْلِمْ وَجْهَهُ إِلَى اللَّهِ وَهُوَ مُحْسِنٌ فَقَدِ اسْتَمْسَكَ بِالْعُرْوَةِ الْوُثْقَىٰ ۗ وَإِلَى اللَّهِ عَاقِبَةُ الْأُمُورِ﴾ لقمان ٢٢

(እርሱ መልካም ሠሪ ሆኖ ፊቱን ወደ አላህ የሚሰጥም ሰው ጠንካራን ገመድ በእርግጥ ጨበጠ፡፡ የነገሩም ሁሉ ፍጻሜ ወደ አላህ ነው፡፡) ሉቅማን 22

7. የተቃውሞ ተፃራሪ የሆነው መቀበል

ላ ኢላህ ኢለላህ ብሎ የሚመሰክረው ሰው ቃሉ ግዴታ የሚያደርጋቸዉን ነገሮች በሙሉ (አላህን በብቸኝነት ማምለክን እና ለሌላ ለፍጡራን የሚከናወኑ አምልኮቶችን መተው) ከልቡ አምኖ በአንደበቱ መስክሮ መቀበል አለበት።ይህንን መስፈርት ያላሟላ እምቢተኛ ነዉና መሰከረ አይባልም።አላህ ኩራተኛነታቸውን እና አለመቀበላቸውን እንዲህ በማለት ከገለፃቸው ሙሽሪኮችይሆናል፡፡

﴿إِنَّهُمْ كَانُوا إِذَا قِيلَ لَهُمْ لَا إِلَٰهَ إِلَّا اللَّهُ يَسْتَكْبِرُونَ(٣٥) وَيَقُولُونَ أَئِنَّا لَتَارِكُو آلِهَتِنَا لِشَاعِرٍ مَّجْنُونٍ﴾ الصافات ٣٥-٣٦

(እነርሱ፤ ‹ከአላህ ሌላ አምልኮ የሚገባው ሆኖ የሚመለክ አምላክ የለም› በተባሉ ጊዜ ይኮሩ ነበር። እኛ ለእብድ ባለቅኔ ብለን አማልክቶቻችንን የምንተው? ነን ይሉም ነበር።)
(አልሷፋት 35-36)

8. ከአላህ ውጪ የሚመለኩ አማልክትን መካድ (ማስተባበል) ናቸው።
ከላይ እንደተመለከትነው ከአላህ ሌላ አምልኮ የሚገባው እንደሌለ የምናረጋግጥበት ቃለ ተውሂድ ይህንን መስፈርት በዉስጡ ያካትታል። ከባዕድ አምልኮ ያልተላቀቀ ሰው በአላህ አላመነም።
አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-
﴿فَمَن يَكْفُرْ بِالطَّاغُوتِ وَيُؤْمِن بِاللَّهِ فَقَدِ اسْتَمْسَكَ بِالْعُرْوَةِ الْوُثْقَىٰ لَا انفِصَامَ لَهَا﴾ البقرة ٢٥٦
(በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው ለርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ።) አል በቀራ 256

ሶላት በእስልምና ውስጥ ያለው ደረጃ

1 - ሶላት ከእስላም ማእዘናት ሁለተኛው ማእዘን ነው።

ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹እስላም በአምስት (ማእዘኖች) ላይ ነው የተመሰረተው። (እነሱም) ፡- ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩንና ሙሐመድ የርሱ አገልጋይና መልእክተኛው መሆናቸውን መመስከር፣ሶላትን ደንቡን ጠብቆ አዘውትሮ መስገድ፣ . . . ናቸው።›› [በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ]

2 - ሶላት ከሥራዎች ሁሉ በላጩ ነው።

የአላህ መልእክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ከሥራዎች ሁሉ በላጩ ሶላትን በወቅቱ መጀመሪያ ላይ መስገድ ነው።›› [በትርምዚ የተዘገበ]

3 - ሶላት የእስላምና የኩፍር መለያ ነው።

ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹በአንድ ሰውና በማጋራትና በክህደት (በሽርክና በኩፍር) መካከል ያለው መለያ ሶላትን መተው ነው።›› [በሙስሊም የተዘገበ]

4 - ሶላት - ከተውሒድ በኋላ - እስላም የሚገነባበት ምሶሶ ነው።

ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹የዚህ ጉዳይ ራስ እስላም ነው፣ ምሰሶው ደግሞ ሶላት ነው።›› [በአሕመድ የተዘገበ]

የሶላት ትሩፋት

1 - ሶላት ለሰጋጁ ብርሃን ነው፣ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ሶላት ብርሃን ነው፡፡›› [በሙስሊም የተዘገበ]

2 - ሶላት የኃጢአቶች ማበሻ ነው፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡- ‹‹ሶላትንም በቀን ጫፎች (ጧትና ከቀትር በኋላ) ከሌሊትም ክፍሎች ፈጽም፤መልካም ሥራዎች ኃጢአቶችን ያስወግዳሉና፤ይህ ለተገሳጮች ግሳጼ ነው፡፡›› [ሁድ፡114]

ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹አንዳችሁ ከደጃፉ ወንዝ ቢኖረውና በየቀኑ አምስት ጊዜ ገላውን ቢታጠብበት ከእድፉ አንዳች ነገር ገላው ላይ ይቀራልን? ንገሩኝ ሲሉ፣ (ሶሓባ) ምንም እድፍ አይቀርበትም አሏቸው፤ነቢዩ ﷺ :- ይህ እንግዲህ አላህ ኃጢአቶችን የሚያብስባቸው የአምስቱ ሶላቶች ምሳሌ ነው፡፡ ›› [በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ]

3 - ሶላት ጀነት ለመግባት ምክንያት ነው፤ነቢዩ ﷺ ለረቢዓ ብን ከዕብ በጀነት አብሯቸው ለመሆን ሲጠይቁ፡- ‹‹ሱጁድን በማብዛት በራስህ ላይ አግዘኝ፡፡›› [በሙስሊም የተዘገበ] ብለዋል፡፡

ሶላትን የሚመለከት ድንጋጌ

የአምስቱ ወቅት ሶላቶች በኪታብ (በቁርአን) በሱንና እና በእጅማዕ ግዴታ (ዋጅብ) ናቸው፡-

1 - ኪታብ (ቁርአን)፡- ‹‹ሶላትንም ደንቡን ጠብቃችሁ ስገዱ፤ ዘካንም (ግዴታ ምጽዋትን) ስጡ፤(ለጌታችሁ) ከአጎንባሾች ጋርም አጎንብሱ፡፡›› [አል-በቀራህ፡43]

2 - ሱንና፡- ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹እስላም በአምስት (ማእዘኖች) ላይ ነው የተመሰረተው፡፡ (እነሱም) ፡- ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩንና ሙሐመድ የርሱ አገልጋይና መልእክተኛው መሆናቸውን መመስከር፣ሶላትን ደንቡን ጠብቆ አዘውትሮ መስገድ፣ዘካን መስጠት፣የሐጅ ሥርዐተ ጸሎት መፈጸምና ረመዷንን መጾም ናቸው፡፡›› [በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ]

- ከጠልሓ ብን ዑበይዱላህ (ረዐ) በተላለፈው መሰረት አንድ ሰውየ ነቢዩን ﷺ ስለ እስላም ሲጠይቃቸው ፡- ‹‹በአንድ ቀንና ሌሊት አምስት ሶላቶችን መስገድ ነው አሉ፤ከነሱ ሌላ አለብኝ ወይ? ሲላቸው በፍላጎትህ የምታደርገው (ተጠው’ዑዕ) ካልሆነ ሌላ የለብህም፡፡›› [በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ] አሉት፡፡

3 - እጅማዕ፡- በአንድ ቀንና ሌሊት አምስት ሶላቶችን መስገድ ግዴታ መሆኑን ኡመቱ (ሕዝበ ሙስሊሙ) በአንድ ድምጽ ተስማምቶበታል፡፡

ሶላት በማን ላይ ግዴታ ይሆናል?

ሶላት ለአቅመ አዳም/ሔዋን በደረሰና አእምሮው ጤነኛ በሆነ በያንዳንዱ ሙስሊም ወንድና ሴት ላይ ግዴታ ነው፡፡

የሶላት ማእዘናት ግዴታዎችና ሱንናዎች

አንደኛ - የሶላት ማእዘናት (አርካን)

የሶላት ማእዘናት

ሶላትን የሚመሰርቱ፣ለማድረግ ያለመቻል ሁኔታ ብቻ ሲቀር በምንም ሁኔታ ሊተው የማይችሉ፣በማወቅም ሆነ በመዘንጋት ውድቅ የማይሆኑ የሶላት መሰረታዊ ክፍሎች ናቸው፡፡

1 - ችሎታ ያለው ሰው መቆም

2 - የመግቢያ ተክቢራ (ተክቢረተል ኢህራም)

3 - ፋቲሓን መቅራት፡፡

4.ማጎንበስ (ሩኩዕ)

5 - ከአጎነበሱበት ቀጥ ብሎ መቆም (ኢዕቲዳል)

6 - በሰባት የሰውነት አካላት ሱጁድ ማድረግ (ከመሬት ላይ ግንባርን ማሳረፍ)

7 - ከእሱም መነሳት

8 - በሁለቱ ሱጁዶች መካከል መቀመጥ።

9 - በማንኛውም የሰላት ተግባራትና እንቅስቃሴ ውስጥ መረጋጋት

10 - በየማዕዘናቱ መካከል ያሉትን ቅደም ተከተል መጠበቅ

11 - በመጨረሻውን አተህያቱ (ተሸሁድ) መቅራት

12 - ለእሱም መቀመጥ

13 - በነብዩ ሙሀመድ (ሰዐወ) ላይ ሰለዋት ማውረድ እና

14 - በሁለቱም ጎን ሰላምታ (አሰላሙ አለይኩም ወራህመቱላህ) ማለት ናቸው።

ሁለተኛ - የሶላት ግዴታዎች (ዋጅባት)

የሶላት ግዴታዎች

በመርሳት ሱጁድ የሚካካስና ከተረሳ የሚቀር።

1 - በሶላት ክፍሎች መካከል የሚደረጉ የመሸጋገሪያ ተክቢራዎች።

2 - ሩኩዕ ላይ ‹‹ሱብሓነ ረብ'ቢየል ዐዚም›› ማለት።

3 - ‹‹ሰምዐል'ኂሁ ልመንሐምደህ›› ማለት፡፡ ለኢማምና ለብቻው ለሚሰግድ ሰው፡፡ ለመእሙም የተደነገገ አይደለም፡፡

4 - ከሩኩዕ ቀና ሲባል ‹‹ረብ'በና ወለከል ሐምዱ›› ማለት፡፡

5 - ሱጁድ ውስጥ ‹‹ሱብሓነ ረብ'ቢየል አዕላ›› ማለት፡፡

6 - በሁለቱ ሱጁዶች መካከል ‹‹ረብብ እግፍርሊ›› ማለት፡፡

7 - ለመጀመሪያው ተሸሁድ መቀመጥ፡፡

8 -የመጀመሪያው ተሸሁድ፡፡

ከሶላት ዋጅቦች ውስጥ አንዱን ዋጅብ የተወ ሰው ምን ያደርጋል?

1 - ሆን ብሎ የተወ ሰው ሶላቱ ስለሚበላሽ መድገም ግዴታ ይሆንበታል፡፡

2 - ረስቶት የተወው ሰው ሶላቱ ትክክለኛ ሲሆን፣በመጨረሻ ሁለት የማካካሻ ሱጁድ ይወርዳል፡፡

ሦስተኛ - የሶላት ሱንናዎች

ከሶላት ሸርጥ፣ከማእዘናቱና ከግዴታዎቹ ውጭ ያሉና በሶላት አሰጋገድ ውስጥ የተጠቀሱ ነገሮች ሁሉ የሶላት ሱንናዎች ናቸው፡፡

ቢተው በሶላቱ ትክክለኛነት ላይ የሚያሳድሩት ተጽእኖ የለም፡፡ በመተውም የማካካሻ ሱጁድ ማድረግ ግዴታ አይሆንም፡፡

የሶላት ሱንናዎች ሁለት ዓይነት ሲሆኑ በቁጥርም ብዙ ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከል የሚከተሉትን እናገኛለን ፡-

አንደኛ - አንደበታዊ ሱንናዎች

1 - የመክፈቻው ዱዓእ ፡- ይህ ከፋቲሓ በፊት የሚቀራው ዱዓእ ነው፡፡

2 - ተዐው'ዉዝ ፡- ‹‹አዑዙ ብል'ላሂ ምነሽ'ሸይጣንር'ረጂም›› ማለት፡፡

3 - በስመላህ ፡- ‹‹ብስምል'ላህር'ረሕማንር'ረሒም›› ማለት፡፡

4 - በሩኩዕና በሱጁድ ውስጥ ከአንድ ጊዜ በላይ ተስቢሕ ማለት፡፡

5 - በሁለቱ ሱጁዶች መካከል ከአንድ ጊዜ በላይ ‹‹ረብ'ብ እግፍርሊ›› ማለት፡፡

6- ከሩኩዕ ቀና ካሉ በኋላ ‹‹ረብ'በና ወለከል ሐምዱ›› በሚለው ላይ የሚጨመር ዝክር፡፡

7 - ከፋቲሓ በኋላ የሚቀራ ተጨማሪ ቁርኣን፡፡

ሁለተኛ - ተግባራዊ ሱንናዎች

ተግባራዊ ሱንናዎች ብዙ ሲሆኑ የሚከተሉት ከፊሎቹ ናቸው ፡-

1 - ከእሕራም ተክቢራ ጋር፣ሩኩዕ ሲወርዱ፣ከሩኩዕ ቀና ሲሉ፣ ለሦስተኛ ረከዓ ለመቆም ሲነሱ ሁለት እጆችን ከፍ ማድረግ፡፡

2 - ከሩኩዕ በፊትና በኋላም በሚቆሙበት ጊዜ ቀኝ እጅን በግራው ላይ ማድረግ፡፡

3 - የሱጁድ ቦታን መመልከት፡፡

4 - በሱጁድ ላይ ሁለት እጆችን ከሆድና ከጎድን ማራራቅ፡፡

5 - እፍትራሽ ማለትም ግራው ላይ ተቀምጦ ጣቶቹን ወደ ቅብላ በማድረግ ቀኙን ተረከዝ ማቆም፡፡ ይህ አቀማመጥ ከሁለት ረከዓ በሚበልጡ ሶላቶች የመጨረሻው ተሸሁድ ብቻ ሲቀር በሁሉም ሶላቶች ውስጥ ሱንና ነው፡፡

6 - ተወርሩክ ማለትም መቀመጫን ከመሬት አድርሶ በመቀመጥ የግራ እግርን በቀኝ በኩል አውጥቶ መሬት ላይ በማስተኛት ቀኝ ተረከዝን ማቆም፡፡ ይህ አቀማመጥ ከሁለት ረከዓ ለሚበልጡ ሶላቶች በመጨረሻው ተሸሁድ ሱንና ነው፡፡

በሶላት ውስጥ የተፈቀዱ የተጠሉና ሶላትን የሚያበላሹ ነገሮች

አንደኛ - በሶላት ውስጥ የሚፈቀዱ ነገሮች

1 - ከቅብላ ፊትን ካለማዞር ግዴታ ጋር የሆነ ችግር ሲያጋጥም በቅብላ በኩል ያለውን በር መክፈትን ለመሳሰለ ነገር መራመድ።

2 - ሶላት ውስጥ ሕጻናትን መሸከም።

3 - ሶላት ውስጥ እባብና ጊንጥን መግደል።

4 - የሆነ ጉዳይ ሲያጋጥም አንገትን ማዞር።

5 - ሶላት ውስጥ ማልቀስ።

6 - ለወንዶች ‹‹ሰብሐነል'ሏህ›› ማለት፣ለሴቶች ማጨብጨብ ኢማሙ ሲሳሳት

7 - ኢማሙ ሲሳሳት ማረም።

8 - ሶላት ውስጥ ለሌለው ሰው ሰላምታ በእጅ ምልክት ምላሽ መስጠት (የመዳፍ የውስጥ ክፍል ወደ መሬት የውጭውን ክፍል ወደ ላይ በማድረግ) ።

9 - የሆነ ጉዳይ ሲያጋጥም ግልጽና አስረጅ የሆነ ምልክት መስጠት፡፡

11 - ሶላት ውስጥ ምራቅና አክታን በግራ በኩል መትፋት፡፡

12 - ከሰጋጅ ፊት አቋርጦ የሚያልፍን ሰው ማገድ፡፡

ሁለተኛ - በሶላት ውስጥ የሚጠሉ ነገሮች

1 - በተበታተነ ሃሳብ፣ከራሱ ጋር ወይም ከፊት ለፊቱ ከሶላት የሚወሰውሰው ነገር እያለ ወደ ሶላት መግባት፡፡ በሽንት፣በዓይነ ምድር ወይም በአየር ሆዱ እየተወጠረ መስገድ፡፡ በጣም እየራበውና እየጠማው፣የሚያስጎምጅ ምግብ ቀርቦ እያለ ወይም ከሶላቱ ትኩረቱን የሚሻማ ነገር እየተመለከተ መስገድ፡፡

2 - ትርጉም የለሽ እንቅስቃሴ ማድረግ፣ማለትም ኹሹዕና እርጋታን የሚጻረር ሁኔታ ሶለት ውስጥ መፈጸም፡፡ ያለ ምክንያት መንቀሳቀስ፣ጺምን፣ልብስና የራስ መሸፈኛን፣የእጅ ሰዓትን መነካካት፤ጣቶችን ያዝ ለቀቅ ማድረግና ማቆላለፍን የመሳሰሉ ነገሮችን መፈጸም፡፡

3 - ያለ ምክንያት ሶላት ውስጥ ፊትን ማዞር፡፡ ይህም ሙሉ በሙሉ አካልን ከቅብላ ካለማዞር ግዴታ ጋር ሲሆን፣ይህን ማድረግ ሶላት ያበላሻል፡፡

4 - ሶላት ውስጥ ወገብን መያዝ፣ይህ የአይሁድ ሥራ ነው፡፡

5 - ሶላት ውስጥ አፍና አፍንጫን መሸፈን፡፡

6 - ልብስን እጅጌንና የመሳሰሉትን መሰብሰብና ማጠፍ፡፡

7 - ለወንዶች ጸጉርን ሰብስቦ ወደ ኋላ መጎንጎን፣በዚህም እጁን የፍጥኝ የታሰረ ይመስል ጸጉሩ አብሮት ሱጁድ እንዳይወርድ ያደርጋል፡፡

8 - ወደ ቅብላ አቅጣጫ ወይም በስተቀኝ መትፋት፡፡

9 - ወደ ሰማይ አንጋጦ ማየት፡፡

10 - ያለ ምክንት ዓይኖችን መጨፈን፡፡

11 - በሱጁድ ጊዜ ሁለቱን ክንዶች መሬት ላይ ማሳረፍ፡፡

ሦስተኛ - ሶላትን የሚያበላሹ ነገሮች

1 - ከሶላት ቅድመ ሁኔታዎች (ሸርጦች) ውስጥ አንዱን የሚጻረር፣ ጦሃራን የሚያበላሽ ነገር መከሰትን፣ወይም ሆን ብሎ ሐፍረተ ገላ መግለጥን፣በሙሉ ሰውነት ከቅብላ መዞርንና ንይ'ያ ማቋረጥን የመሳሰለ ሁኔታ መፈጠር፡፡

2 - ሆን ብሎ አንድን የሶላት ሩክን ወይም ዋጅብ መተው፡፡

3 - ከሶላት ተግባራት ውጭ የሆነ መሄድና ብዙ እንቅስቃሴ ማድረግን የመሳሰለ ምክንያት የሌለው ብዙ ሥራ መስራት፡፡

4 - መሳቅና መንሰቅሰቅ፡፡

5 - ሆን ብሎ መናገር፡፡

6 - ሆን ብሎ መብላትና መጠጣት፡፡

7 - አንድ ረክዓ ወይም ማእዘን ሆን ብሎ መጨመር፡፡

8 - ሆን ብሎ ከኢማሙ አስቀድሞ ሰላምታ ማለት፡፡

ያመለጠ ሶላትን ሰግዶ መክፈል

እስላም ከበፊቱ የነበረውን ነገር ስለሚያብስ አንድ ካፍር ከመስለሙ በፊት ያመለጠውን ሶላት ሰግዶ እንዲከፍል አይታዘዝም፡፡

ሶላትን የተወ ሰው የሚመለከት ድንጋጌ

1 - ሶላት ግዴታ መሆኑን የሚክድ ሶላት የተወ ሰው

የማያውቅ ከሆነ እንዲያውቅ ይደረጋል፡፡ ግዴታነቱን ማስተባበል ከቀጠለበት በአላህ በመልእክተኛውና በሙስሊሞች የጋራ ስምምነት እስላምን ያስተባበለ ካፍር ነው፡፡

2 - በስንፍና ሶላትን የተወ ሰው

ሶላትን ሆን ብሎ በስንፍና የተወ ሰው ከሐዲ ሆኗል፡፡ በመሆኑም ወሊዩል አምር እንዲሰግድና ተጸጽቶ ተውበት እንዲያደርግ ለሦስት ቀናት ጊዜ ጥሪ ሊያድርግለት ይገባል፡፡ ተጸጽቶ ከተመለሰ ተመለሰ ካልተመለሰ ግን ተቀልባሽ (ሙርተድ) በመሆኑ ይገድለዋል፡፡ ይህም ነቢዩ ﷺ :-

(العهد الذي بيننا وبينهم الصلاة، فمن تركها فقد كفر)

‹‹በኛና በነሱ መካከል ያለው መለያ ቃል ሶላት ነው፣ሶላቱን የተወ ሰውም ከሃዲ ሆኗል፡፡›› [በትርምዚ የተዘገበ]

ባሉት መሰረት ነው፡፡ በተጨማሪም ነቢዩ ﷺ :- ‹‹በአንድ ሰውና በማጋራትና በክህደት (በሽርክና በኩፍር) መካከል ያለው መለያ ሶላትን መተው ነው፡፡›› [በሙስሊም የተዘገበ] ብለዋል፡፡

የትንሽ ልጅ ሶላት

ልጆች ሰባት ዓመት ሲሞላቸው እንዲለማመዱት ሶላት እንዲሰግዱ ይታዘዛሉ፡፡ አስር ዓመት ሲሞላቸው ካልሰገዱ በማያሳምም ሁኔታ እንዲሰግዱ ይመታሉ፡፡ ነቢዩ ﷺ :-

((مُرُوا أَوْلاَدَكُمْ بِالصَّلاَةِ وَهُمْ أَبْنَاءُ سَبْعِ سِنِينَ، وَاضْرِبُوهُمْ عَلَيْهَا وَهُمْ أَبْنَاءُ عَشْرٍ))

‹‹ልጆቻችሁን ሰባት ዓመት ሲሞሉ እንዲሰግዱ እዘዟቸው፡፡ ዐስር ዓመት ሲሞሉ (ካልሰገዱ) እንዲሰግዱ ምቷቸው፡፡›› [በአቡ ዳውድ የተዘገበ] ብለዋል፡፡

❋ ۞ ❋

ተፈፀመ

